# ገድለ ተክለ ሃይማኖት



ተኀትመ ዝንቱ መጽሐፍ በኀምስ ዓመተ ሢመተ ጵጵስናሁ
ለብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ ወዕጨጌ
ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት

አንደኛ በ፲፱፻፵፮ ዓ. ም.
ሁለተኛ በ፲፱፻፷፰ ዓ. ም.
ሦስተኛ በ፲፱፻፸፫ ዓ. ም.
ለአራተኛ ጊዜ በ፲፱፻፹፱ ዓ.ም.
ታ ተ መ ፤


በ መ ጽ ሐ ፉ ው ስ ጥ የ ተ ካ ተ ቱ

፩· ገድለተክለ ሃይማኖት
፪· ፷፰ ተአምረ ተክለ ሃይማኖት
፫· መልክአ ተክለ ሃይማኖት
፬· ባጭሩ የደብረ ሊባኖስ ገዳም ታሪክ



ነሐሴ ፲፱፻፹፱ ዓ. ም.
አዲስ አበባ




ጻድቁ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጳውሎስ ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ
ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወእጨጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት

# መግለጫ ፤

ቅዱስ አባታችን አቡነ ተክለ ሃይማኖት እግዚአብሔር በመራቸው መሠረት የሐዋርያትን እሠረ ፍኖት በመከተል ዘር ልዝራ ትዳር ልያዝ ሳይሉ ከአባታቸው ከጸጋ ዘአብና ከእናታቸው ከእግዚአ ኃረያ በመለየት ።

ቀደስኩከ እምከርሠ እምከ ማለት በሆድ ሳልሠራህ አውቄሃለሁ ከማሕፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ ለአሕዛብ ነቢይ አድርጌሃለሁ እኔም ወዮ ጌታ እግዚአብሔር እነሆ ብላቴና ነኝና እናገር ዘንድ አላውቅም አልሁ እግዚአብሔር ግን እንዲህ አለኝ ወደ ምሰድህ ሁሉ ዘንድ ትሄዳለህና የማዝዝህን ሁሉ ትናገራለህና ብላቴና ነኝ አትበል እኔ አድንህ ዘንድ ከአንተ ጋር ነኝና ከፊታቸው አትፍራ ይላል። እግዚአብሔር ትንቢተ ኤርምያስ ምዕ ፩ ቁጥር ፭ በተባለው መሠረት በኢትዮጵያ በረሃዎችና አውራጃዎች እየተዘዋወሩ በልዩ ልዩ አምልኮት የነበረውን ሕዝብ የክርስቶስ ወንጌል መንግሥትን አስተምረውና አጥምቀው የክርስቶስ መንግሥትን እንዲወርሱ ያደረጉ ታላቅ ጻድቅ ናቸው ከዚህም በላይ ረኃቡንና ጽሙን ታግሠው በጾምና በጸሎት እንዲሁም በስግደት ተጋድሎ በማድረግ ለኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን የሠሩት ሥራ ኢትዮጵያ ትኮራባቸዋለች ከዚህም በላይ በእኒህ ታላቅ ጻድቅ ልመናና አማላጅነት ትጠቀማለች ።

ጌታ በወንጌለ ማቴዎስ በምዕራፍ ፲ ቁጥር ፵ እናንተን የሚቀበል እኔን ይቀበላል እኔንም የሚቀበል የላከኝን ይቀበላል ነቢዩን በነቢይ ስም የሚቀበል የነቢይን ዋጋ ይወስዳል ጻድቅንም በጻድቅ ስም የሚቀበል የጻድቁን ዋጋ ይወስዳል ማንም ከእነዚህ ከታናናሾቹ ለአንዱ ቀዝቃዛ ጽዋ ውኃ ብቻ በደቀ መዝሙር ስም የሚያጠጣ እውነት እላችኋለሁ ዋጋው አይጠፋበትም ይላል ።

እነሆ አሁን የቅዱስ አባታችን ተክለ ሃይማኖት ገድል ከአንድ እስከ ሦስት ጊዜ ታትሞ ሲሠራበት ከቆየ በኋላ ለአራተኛ ጊዜ በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ፳፰ ተአምር ፣ መልክአ ተክለ ሃይማኖት እንዲሁም ከገድለ ተክለ ሃይማኖት ጋር ተጽፎ የተገኘ የደብረ ሊባኖስ ታሪክ በጥራት ታትሞ ለሕዝበ ክርስቲያኑ ቀርቧል ።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

አሜን

# መግቢያ ፤

ገድል ፡ ማለት ፡ ዘረከባ ፡ ለነፍሱ ፡ ለይግድፋ ፡ ወዘሰ ፡ ገደፋ ፡ ለነፍሱ ፡ በእንቲአየ ፡ ወበእንተ ፡ ወንጌልየ ፡ ይረከባ ።

ሰውነቱን ፡ በሕይወት ፡ ያገኛት ፡ በመከራ ፡ ይጣላት ፡ ስለእኔና ፡ ስለወንጌል ፡ በመከራ ፡ የጣላት ሰው ፡ በክብር ፡ በሕይወት ፡ ያገኛታል ፡ የተባለላቸው ፡ ጻድቃንና ፡ ኢትፍርህዎሙኬ ፡ ለእለ ፡ ይቀትሉ ፡ ሥጋክሙ ፡ ወለነፍስክሙሰ ፡ ኢይክሉ ፡ ቀቲሎታ ።

ሥጋችሁን ፡ የሚገድሏትን ፡ አትፍሩ ፡ ነፍሳችሁን ፡ መግደል ፡ አይቻላቸውምና ፤ የተባለላቸው ፡ ሰማዕታት ፡ በውድም ፡ ሆነ ፡ በግድ ፡ በአምላካቸው ጥሪ ፡ የፍኖተ ፡ መስቀልን ፡ ጉዞ ፡ ከጀመሩበት ፡ እስከ ፡ ዕለተ ፡ ሞታቸው ፡ ድረስ ፡ የተጋደሉትን ፡ ገድል ፡ የታገሉትን ፡ ትግል ፡ የፈጸሙትን ፡ ሥራ ፡ የተቀበሉትን ፡ መከራ ፡ አጠቃሎ ፡ የሚያስረዳ ፡ ቃል ፡ ነው ።

መሠረቱ ፡ ወንጌል ፡ ሲሆን ፡ አጻጻፉ ፡ የሐዋርያትን ፡ ሥራ ፡ ይመስላል ፡ ቅዱሳን ፡ የተቀበሉትን መከራ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ ለማክበር ፡ የፈጸሙትን ፡ ሥራ ፡ እግዚአብሔርም ፡ የሃይማኖታቸውን ፡ ጽናት ፡ እውነተኛነት ፡ ለመግለጥ ፡ ያደረገላቸውን ፡ ተአምራት ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ለስማቸው፡የተሰጠውን ፡ ክብር ፡ ለአስተማርዋቸው ፡ የደረሰውን ፡ ትምህርት ፡ እየዘረዘረ ፡ ይገልጣል ። ዓላማው ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ከዚህ ፡ ውጭ ፡ አይሔድም ።
የአጻጻፉን ፡ ሥርዓት ፡ ወንጌላዊ ፡ ሉቃስ ፡ ዜና ፡ ሐዋርያትን ፡ በጻፈበት ፡ ግብረ ፡ ሐዋርያት ፡ (የሐዋርያት ሥራ ፡) ፡ በተባለው ፡ መጽሐፉ ፡ ገልጾታል ፤ በየጊዜው ፡ የተነሡ ፡ መምህራን ፡ ሊቃውንት ፡ ሉቃስን መሪ ፡ አድርገው ፡ የእሱን ፡ መምሪያ ፡ ተከትለው፡ የነቢያትን ፤ የሐዋርያትን ፤ የጻድቃንን ፡ የሰማዕታትን ፡ ዜና ፡ የሚገልጽ ፡ መጽሐፍ ፡ ጽፈዋል ።

ስሙም ፡ የጻድቁን ፤ የሰማዕቱን ፡ ስም ፡ ይዞ ፡ ይሠየማል ፡ ይኸውም ፡ ገድለ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ገድለ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ እንደማለት ፡ ነው ፡ በአጠቃላይ ፡ ግን ፡ ገድለ ፡ ቅዱሳን ፡ ይባላል ።

ይህን ፡ የቅዱሳን ፡ ገድል ፡ ለመጻፍም ፡ መሠረቱ ፡ ወንጌል ፡ ነው ። ጌታችን ፡ ማርያም ፡ እንተ፤ ዕፍረት ፡ እግሩን ፡ ሽቱ ፡ በቀባችው ፡ ጊዜ ፡ ጠቅላላ ፡ በንስሐ ፡ የፈጸመችውን ፡ ሥራ ፡ ከተመለከተ ፡ በኋላ ፡ ይህች ፡ ሴት ፡ የአደረገችውን ፡ ወንጌል በተነበበችበት ቦታ ፡ ሁሉ ፡ ይነገሩላት ፡ አለ ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ወንጌላውያን ፡ የዚችን ፡ ሴት ዜና ፡ በወንጌል ፡ ውስጥ ፡ ጽፈው ፡ ለዓለም ፡ አስተላልፈዋል ።

እንግዲህ ፡ የቅዱሳንን ፡ ዜና ፡ ለመጻፍና ፡ ለትውልድ ፡ ለማስተላለፍ ፡ መሠረቱ ፡ የጌታ ፡ ትእዛዝ ፤ የወንጌላውያንም ፡ መታዘዝ ፡ ነው ።

አባቶቻችን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ሊቃውንት ፡ ቀደም ፡ ብለን ፡ በጠቀስነው ፡ አንጻር ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍትን ፡ ጽፈው ፤ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰጥተዋል ፡ ከነዚህም ፡ አንዱ ፡ ይህ ፡ ገድለ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የተባለው ፡ መጽሐፍ ፡ ነው ። አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ከኢትዮጵያውያን ፡ አበው መካከል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ በኋላ ፡ ዘመን ተነሥተው ፡ ከሐዋርያት ፡ ማዕርግ ፡ የደረሱ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተስፋ ፡ ያደሱ ፡ ታላቅ አባት ፡ ናቸው ። በሃያ ፡ ዓመት ፡ ዕድሜያቸው ጨለማ ፡ ለሠለጠነበት ፡ ክፍል ፡ ብርሃን ፡ እንድትሆን ፡ አዲስ ፡ ሐዋርያ ፡ አድርጌ ፡ ሾሜሃለሁ ፡ ሲል ፡ ላከበራቸው ፡ ለሾማቸው ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ብሎ ፡ ለሠየማቸው ፡ ለፈጣሪያቸው ፡ ሕይወታቸውን ፡ አሳልፈው ፡ ከሰጡበት ፡ ጊዜ ፡ ጀምሮ ፡ ያለ ፡ ጽልሁት ፤ ያለ ፡ ሐኬት ፤ በርዳታ ፡ በማስተማር ፤ በሰማዕትነት ፤ በድንግልና ፤ በምንኩስና ፤ በተባሕትዎ ፤ በልዩ ልዩ ፡ የተጋድሎ ፡ ዘርፍ ፡ ሰማንያ ፡ ዘመን ፡ ፈጣሪያቸውን ፡ አገልግለዋል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ረድተዋል ። ሃይማኖታቸውን ፡ ከጠበቁ ፡ ገድላቸውን ፡ ካጠናቀቁ ፡ በኋላ ፡ በመቶ ፡ ዘመን ፡ ዕድሜያቸው ፡ በደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ገዳም ፡ ዐርፈዋል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ሊቃውንት ፡ በዓፄ ፡ ይስሐቅ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በማዕርገ ፡ ቅድስና ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዲታሰቡ ፤ መታሰቢያ ፡ እንዲደረግላቸው ፤ በዓል ፡ እንዲከበርላቸው ፡ በስማቸው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዲሠራላቸው ፤ ገዳም ፡ እንዲቆረቆርላቸው ፤ መጽሐፍ ፡ እንዲጻፍላቸው ፤ ፈቅደው ፡ ይኸው ፡ በቤተ ክርስቲያን ፡ ጉባኤ ፡ ስለተወሰነ ፡ ሰባተኛ ፡ ዕጨጌ፡ ዮሐንስ ፡ ከማ ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ጻፉ ።

የጉባኤውም ፡ ውሳኔ ፡ በልብ ፡ ወለድ ፡ የተፈፈጸመ ፡ አይደለም ። እግዚአብሔርን ፡ በሚገባ ፡ ያገለገሉ ፡ ሁሉ ፡ ከሴት ፡ ልጅ ፡ ከወንድ ፡ ልጅ ፡ የተሻለ ፡ መታሰቢያ ፡ በቤቱ ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ እንዲኖራቸው ፡ ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈቅዶ ፡

ለቅዱሳን ፡ ሁሉ ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ የዘለዓለም ፡ ስም ፡ እንደሚሰጣቸው ፡ በትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፡ ዐውጅዋል ። ይህም ፡ በትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ፡ በሃምሳ ፡ ስድስት ፡ ምዕራፍ ፡ ይገኛል ።

ስለዚህም ፡ ኢትዮጵያዊው ፡ ጉባኤ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስለ ፡ **አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡** የአስተላለፈው ፡ ውሳኔ ፡ **በእግዚአብሔር ፡** ቃል ፡ መሠረትነት ፡ ነው ።

**ልዑል ፡ እግዘአብሔር ፡** የቅዱሳንን ፡ ሥራ ፡ ትምህርታቸውን ፤ እምነታቸውን ፤ በተአምራት ፡ እንደሚያስረዳላቸው፤ እንደሚመሰክርላቸው ፤ ሐዋርያው ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ገልጦአል ። ይህ ፡ ተአምራት ፡ በሕይወታቸው ፡ ብቻ ፡ ሳይወሰን ፡ ከሞቱም ፡ በኋላ ፡ ዐፅማቸው ፡ በተከሰከሰበት ፤ ወዛቸው ፡ ደማቸው ፡ በፈሰሰበት ፡ ስማቸው ፡ በሚጠራበት ፤ መታሰቢያቸው ፡ በሚደረግበት ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ ሳይቋረጥ ፡ እየቀጠለ ፡ የሚኖር ፡ በመሆኑ በኢትዮጵያ ፡ በልዩ ልዩ ቦታ ፡ **ልዑል ፡ እግዚአብሔር ፡** በቅዱሳኑ ፡ ስም ፡ የሚያደርገው ፡ ተአምራት እስከዛሬ ፡ አልተቋረጠም ፤ ይህ ፡ ጸጋ ፡ ከተሰጣቸው ፡ ቅዱሳን ፡ አንዱ ፡ አባታችን ፡ **አቡነ ፡ ተክለ ሃይማኖት ፡** በመሆናቸውም ፡ ዐፅማቸው ፡ በዐረፈበት በደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ገዳምና ፡ ስማቸው ፡ በተጠራበት ፤ መታሰበያቸው ፡ በሚደረግበት ፤ ዜና ፡ ገድላቸው ፡ በሚነበብበት ፡ ቦታና ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡ የሚደረገው ፡ ተአምራት ፡ ከጊዜ ፡ ወደ ፡ ጊዜ ፡ እየጨመረ ፡ በመሔድ ፡ ላይ ፡ ነው ። ብዙ ፡ ድውያን ፡ ይፈውሳሉ ፤ አጋንንት ፡ ይወጣሉ ፤ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ታምራት ይደረጋል ፡ ይህም ፡ ምልክት ፡ የወንጌልና ፡ የወንጌላውያን ፡ መመሪያ ፡ ነው ፡ አባታችን ፡ **አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡** የኢትዮጵያ ፡ ቅዱሳን ፡ አንጋፋ ታላቅ ፡ ሐዋርያ ፡ ቅዱስ ፡ አባት ፡ በመሆናቸው ፡ **አምላከ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡** ብለን ፡ ስሙንና ፡ ስማቸውን ፡ በመጥራት ፡ በጸሎታቸው ፡ እንማፀናለን። ለቅድስናቸው ፡ መታሰቢያ ፡ እናደርጋለን ።

ምእመናን ፡ ዜና ፡ ትሩፋታቸውን ፡ በመስማት ፡ እንዲጠቀሙበት ፤ መጽናናትም ፡ እንዲያገኙበት ፡ እንሆ ፡ ገድላቸው ፡ ታትሞ ፡ ለንባብ ፡ ቀርቦአል ።

**አምላከ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡** ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ፡ የኢትዮጵያን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ ምእመናንዋን ፡ በረድኤቱ ፡ ይጠብቅ ፡ አሜን ።

፩፡ በስመ ፡ አብ ወወልድ ፤ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ
፩ ፡ አምላክ ።
፪ ፤ በስመ ፡ አብ አውሎግሶን ።
፫ ፤ በስመ ፡ ወልድ ፡ አአምን ።
፬ ፤ ወበስመ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አመልክ ፡
፭ ፤ በስመ ፡ አብ ፡ አውሎግሶን ፡ አብኖተ ፡ ነገር ፡ ውእቱ ።
፮ ፤ በሉኬ ፡ አብሑኒ ፡ ፍ ቁራኒሁ ፡ ለአብ ።
፯ ጌራን ፡ ወመተንብላን ።
፰ ፤ ከመ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ያብርህ ፡ አዕይንተ ፡ ልብየ ።
፱ ፤ ከመ ፡ እዜኑክሙ ፡ ንስቲተ ፡ እምትሩፋተ ፡ ገድሉ ፡ ለቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።
፲ ፤ ክቡር ፡ ወኄር ። ተክለ ፡ አብ ፡ ተክለ ፡ ወልድ ፡ ተክለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ።
፲፩ ፤ እወ ፡ እብለከ ፡ አ ፍቁረ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ።
፲፪ ፤ ለሰማይ ፡ ዘሰቀሎ ፡ ከመ ፡ ቀመር ፤ አሪት፡ ዘፍ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ,፩ ።
፲፫ ፤ ዘሣረራ ፡ ለምድር ፡ ዲበ ፡ ማይ ፡ ከሙ ፡ ሰፍንጊ ፡ በመልዕልተ ፡ ባሕር ።
፲፬ ፤ ያብርህ ፡ አዕይንተ ፡ ልብከ ።
፲፭ ፤ ከመ ፡ ትትናገር ፡ ዲበ ፡ ምሥጢረ ፡ መለኮቱ ስውር ፡ ወመንክር ።
፲፮ ፤ ትዜንወነ ፡ ወታረውየነ ፡ ቀዲሐከ ፡ እምባሕረ ፡ መለኮት ፡ ዘኢይቀብል ።
፲፯ ፤ በእንተ ፡ ዜናሁ ፡ ለክቡር ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መስተጋድል ።
፲፰ ፤ ያብርህ ፡ ልበከ ፡ በብርሃነ ፡ መለኮቱ ፡ ጽዱል ።
፲፱ ፤ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

፩ ፤ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፩ ፡ አምላክ ፡ አአምን ፡ ብሂል ፤
፪ ፤ አአምን ፡ ወእጤይቅ ፡ ከመ ፡ ወልደ ፡ አብ፡ እምቅድመ ፡ ዓለም ።
፫ ፤ ወእምቅድመ ፡ አየራት ፡ ያስተርኢ ።
፬ ፤ ወእምቅድመ ፡ ይትኖለቍ ፡ አዝማን ፡ ዘወልደ ፡ አብ ፡ ክቡር ።
፭ ፤ እምጽንዓ ፡ መለኮቱ ።
፮ ፤ ወእኮ ፡ እምካልዕ ፡ ኃይል ፡
፯ ፤ በሉኬ ፡ ሰአሉ ፡ ወባርኩኒ፡ አ፡ምእመናኑ ፡ ለወልድ ።
፰ ፤ ከመ ፡ ያርትዕ ፡ እምነትየ ፡ በስሙ ።
፱ ፤ ወይንድፈኒ ፡ በሐጸ ፡ መለኮቱ ።
፲ ፤ ወያንሰሐስሐኒ ፡ ልብየ ።

፩/ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆኑ ፡ በአብ ፡ በወልድ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ አምኜ ።
፪ ፤ በአብ ፡ ስም ፡ እናገራለሁ ።
፫ ፤ በወልድ ስም ፡ አምናለሁ ።
፬ ፤ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ አመልካለሁ ።
፭ ፤ በስመ ፡ አብ ፡ አውሎግሶን ፡ ማለት ፡ ለመናገር ፡ አሰናብቱኝ ፡ ማለት ፡ ነውና ።
፮ ፤ የእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ባለሚሎች ፡ ወዳጆች ፡ በሉ ፡ አሰናብቱኝ ።
፯ ፤ ቸሮች ፡ አማላጆች ፡ የምትሆኑ
፰ ፤ እግዚአብሔር ፡ የልቡናዬን ፡ ዓይኖች ፡ ብርሃን ፡ ያደርግልኝ ፡ ዘንድ ።
፱ ፤ እግዚአብሔር ፡ ያከበረው ፡ ክቡር ፡ ቸር ። አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
፲ ፤ የአብ ፡ የወልድ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተክል የሚሆን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ከሠራው ፡ ከብዙ ፡ ሥራው ፡ ጥቂት ፡ እነግራችሁ፡ ዘንድ።
፲፩ ፤ የእግዚአብሔር ፡ ወዳጅ ፡ አወን ፡ እንዲህ ፡ እልሃለሁ ።
፲፪ ፤ ሰማይን ፡ እንደጣሪያ ፡ (እንደ ፡ መጋረጃ ።)
፲፫ ፤ ምድርን ፡ በውኃ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ሥጋጃ ፡ እንደዳውጃ ፡) ፡ የዘረጋት ፡ እሱ ።
፲፬ ፤ ዓይነ ፡ ልቡናህን ፡ ብሩህ ፡ ያድርግልህ ፡ እልሀለሁ ።
፲፭ ፤ ድንቅ ፡ ረቂቅ ፡ የሚሆን ፡ የጌትነቱን ፡ ምሥጢር ፡ ትናገር ፡ ዘንድ ።
፲፮ ፤ መጉደል ፡ ከሌለበት ፡ ከጌትነቱ ፡ ባሕር ፡ ቀድተህ ፡ ታረካን ፡ ዘንድ ፡ ማለት ፡ ፈጽመህ ፡ ትነግረን ፡ (ታስረዳን ፡) ዘንድ ።
፲፯/ በበጎ ፡ ሥራ ፡ የሚጋደል ፡ የክቡር ፡ አባታችን ፡ የተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ነገር ፡ ትነግረን ፡ ዘንድ ።
፲፰ ፤ ብሩህ ፡ በሚሆን ፡ በጌትነቱ ፡ ዕውቀት ፡ ልቡናህን ፡ ብሩህ ፡ ያድርግልህ ።
፲፱ ፤ ለዘለዓለሙ ፡ በውነት ።

፩ ፤ በባሕርይ ፡ በሕልውና ፡ አንድ ፡ በሚሆኑ፡ በሦስቱ ፡ ስም ፡ አምናለሁ ፡ ማለት ።
፪ ፤ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ ከአብ ፡ ያለናት ፡ መወለዱን ፡ አምናለሁ ፡ እረዳለሁ ፡ ማለት ፡ ነው ፤
፫ ፤ ሰማያት ፡ ሳይፈጠሩ ።
፬ ፤ ክቡር ፡ የሚሆን ፡ የአብ ፡ የባሕርይ ፡ ልጁ. ዘመን ፡ ሳይፈቈጠር ።
፭ ፤ ከጌትነቱ ፡ ጽናት ፡ የተነሣ ።
፮ ፤ ከሌላ ፡ ባሕርዩ ፡ ያልተገኘ ።
፯ ፤ በወልድ ፡ ያመናችሁ ፡ በሉ ፡ አክብራችሁ፡ ለምኑልኝ ።
፰ ፤ በስሙ ፡ ማመንን ፡ ያጸናልኝ ፡ ዘንድ ።
፱ ፤ በፍቅሩ ፡ ጽናት ፡ ያነቃቃኝ ፡ ዘንድ ።
፲ ፤ ልበ ናዬን ፡ ያነሣሣው ፡ ዘንድ ።

፲፩ ፤ ከመ ፡ እዜኑ ፡ ምስትጉቡአ ፡ ገድሎ ፡ ለአቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።
፲፪ ፤ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።
፲፫ ፤ ወያርትዕ ፡ እምነተከ ፡ ወልደ ፡ አብ ፡ እምቅድመ ፡ ዓለም ።
፲፬ ፤ ወኢቀደሞ ፡ ዘርዕ ፡ ለልደቱ ፡ እማርያም ።
፲፭ ፤ ውእቱኬ ፡ ዘተሰብከ ፡ በነቢያት ።
፲፮ ፤ ወተነግረ ፡ በሐዋርያት ።
፲፯ ፤ ውእቱ ፡ ይዝብጦ ፡ ለአንቀጸ ፡ ልብከ ፡ ድንዙዝ ።
፲፰ ፤ በአውታረ ፡ መሰናቍት ፡ ዘመንፈስ ፡ ቅዱስ
፲፱ ፤ ከመ ፡ ትዜንወነ ፡ ዜናሁ ፡ ለአቡነ ፡ ብፁዕ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።
፳ ፤ ወይሁቱ ፡ ለመሠረተ ፡ ሕሊናከ ፡ በፍቅረ ፡ መለኮቱ ፡ አምላካዊ ፡ አሜን ።
፳፩ ፤ በስመ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አመልክ ።
፳፪ ፤ አመልክ ፡ ብሂል ።
፳፫ ፤ እሰግድ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለአብ ፡ ወወልድ ።
፳፬ ፤ እምቅድመ ፡ ሠለስቲሆሙ ፡ ዘበ ፩ ፡ አካል ፡ ወአልቦ ፡ ዘአእመሮሙ ። ለሥሉስ ፡ ቅዱስ
፳፭ ፤ ዘእንበለ ፡ እምድኅረ ፡ ተሠገወ ፡ ወልድ ፡ ዋሕድ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
፳፮ ፤ ከመዝ ፡ ውእቱ ፡ እምነተ ፡ ሥላሴ ፡ በዋሕድ ።
፳፯ ፤ በሉኬ ፡ ቀድሱ ፡ አምልኮትየ ፡ ኦማኅበረ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።
፳፰ ፤ እለ ፡ እቱባን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ።
፳፱ ፤ ወእትናገር ፡ በልሳነ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ።
፴ ፤ ወይክሥት ፡ አምልኮትየ ፡ በመጽሔተ ። መንፈስ ፡ ቅዱስ ።
፴፩ ፤ እንብብ ፡ ወእንግር ፡ እምትዕግሥተ ፡ ገድሉ ፡ ለቅዱስ ፡ ወቡሩክ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ተክለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ።
፴፪ ፤ በአማን ፡ ያጽንዕ ፡ አምልኮተከ ፡ ወአስተንፋሰከ ።
፴፫ ፤ ወይትናገር ፡ በላዕሌከ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
፴፬ ፤ ውእቱ ፡ ጰራቅሊጦስ ፡ ዘከፈለ ፡ በጽርሐ ፡ ጽዮን ፸ ወ፪ ልሳናተ ።
፴፭ ፤ ግብ ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፫ ፡ ወውእቱ ፡ ጰራቅሊጦስ ፡ ዘወረደ ፡ ላዕለ ፡ ሐዋርያት ፡ በጽርሐ ፡ ጽዮን ፡ ወአንበልበለ ፡ ውስተ ፡ አፉሆሙ ።
፴፮ ፤ ወተቀድሐ ፡ እሳት ፡ ውስተ ፡ ልቦሙ ፡

፲፩ ፤ የክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በብዙ ፡ ዘመን ፡ የተሠራ ፡ ሥራውን ፡ ፡ እናገር ዘንድ ።
፲፪ ፤ ለዘላለሙ ፡ በውነት ።
፲፫ ፤ ቅድመ ፡ ዓለም ፡ ከአብ ፡ ያለናት ፡ የተወለደ ፡ የባሕርይ ፡ ልጁ ፡ ሃይማኖትህን ፡ ያጽናልህ ።
፲፬ ፤ ከእመቤታችን ፡ ለመወለዱ ፡ ዘርዓ ፡ ብእሲ ተቀድሞት ፡ አልተገኘም ። ዘርዓ ፡ ብእሲ ፡ ምክንያት ፡ አልሆነውም ።
፲፭ ፤ በነቢያት ፡ (ይወርዳል ፡ ይወለዳል ፡ ተብሎ) የተነገረ ፡ እሱ ።
፲፮ ፤ ሐዋርያት ፡ ወረደ ፡ ተወለደ ፡ ብለው ፡ ያስተማሩት ፡ እሱ ።
፲፯ ፤ የተዘጋ ፡ የልቡናህን ፡ በር ፡ ይክፈትልህ ።
፲፰ ፤ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መሰንቆ ፡ ቃኝነት ።
፲፱ ፤ የብፁዕ ፡ አባታችን ፡ የተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ሥራ ፡ ትነግረን ፡ ዘንድ ።
፳ ፤ በአምላክነት ፡ በምትሠራ ፡ በጌትነቱ ፡ ፍቅር ፡ የልቡናህን ፡ መሠረት ፡ ያናውጸው ። በውነት ፡ ያለሐሰት ።
፳፩ ፤ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ አመልካለሁ ።
፳፪ ፤ አመልካለሁ ፡ ማለት ።
፳፫ ፤ ለመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለአብ ፡ ለወልድ ፡ እሰግዳለሁ ፡ ማለት ፡ ነው ።
፳፬ ፤ ሦስትነታቸው ፡ ሳይታወቅ ፡ አስቀድሞ ። የሥላሴ ፡ ሦስትነታቸው ፡ ፩ነታቸው ፡ ወልድ ሰው ፡ እስከሆነ ፡ ድረስ ፡ አይታወቅም ፡ ነበር ።
፳፭ ፤ በባሕርይ ፡ አንድ ፡ በሚሆን ፡ አካል ፡ ሦስትነታቸው ፡ ከታወቀም ፡ በኋላ ።
፳፮ ፤ በባሕርይ ፡ በህልውና ፡ አንድ ፡ በማድረግ ፡ ሦስቱን ፡ አካላት ፡ ማመን ፡ እንዲዚህ ፡ ነው
፳፯ ፤ የክርስቲያን ፡ ወገኖች ፡ በሉ ፡ እስኪ ፡ ሃይማኖቴን ፡ አጽኑልኝ ።
፳፰ ፤ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የከበራችሁ ።
፳፱ ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በገለጸልኝ ፡ አንደበት ፡ እናገር ፡ ዘንድ ።
፴ ፤ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መሥታወትነት ፡ ሃይማኖቴን ፡ ይገልጽልኝ ፡ ዘንድ ።
፴፩ ፤ ክቡር ፡ የሚሆን ፡ ተክለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሚባል ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ መከራውን ፡ ሁሉ ፡ እየተቀበለ ፡ ከሠራው ሥራ ፡ ፊጽሜ ፡ እናገር ፡ ዘንድ ።
፴፪ ፤ በውነት ፡ ሃይማኖትክን ፡ ያጽናልህ ፡ አንደበትህን ፡ ይግለጽልህ ።
፴፫ ፤ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ባንተ ፡ አድሮ ፡ ይናገር ።
፴፬ ፤ በጽርሐ ፡ ጽዮን ፡ አዳራሽ ፡ ሰባ ፡ ሁለት ፡ ቋንቋ ፡ የገለጸ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነውና ።
፴፭ ፤ በሐዋርያት ፡ ላይ ፡ አድሮ ፡ በሰባ ፡ ሁለት ፡ ቋንቋ ፡ ያናገረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነውና ።
፴፮ ፤ በእሳት ፡ አምሳል ፡ ያደረባቸው ።

፻፶፯ ፤ ወአስተጋብአ ፡ እሎንተ ፡ ፸ወ፪ተ ፡ ልሳናተ ወከሠተ ፡ ሎሙ ።

፻፶፰ ፤ ወከማሁ ፡ ለከኒ ፡ አ ፍቁር ፡ ውእቱ ፡ ጰራቅ ሊጦስ ፡ ያንበለብል ፡ ውስተ ፡ አፉከ ፡ አሜን ።

፻፶፱ ፤ ወይክሥት ፡ ለከ ፡ ኀቡአተ ፡ ገድሉ ፤

፻፷ ፤ ወትሩፋተ ፡ ምግባሩ ።

፻፷፩ ፤ ወፍጻሜ ፡ በድሩ ፡ ዘተባደረ ፡ በአሚነ አብ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ።

፻፷፪ ፤ ወዝንቱ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ውእቱ ፡ የሃሉ ፡ ምስሌከ ።

፻፷፫ ፤ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ።

፻፷፬ ፤ ወይተርጕም ፡ ለከ ፡ ኵሎ ፡ ገድሎ ፡ ወት ዕግሥቶ ።

፻፷፭ ፤ እስከፍጻሜ ፡ ጽሒፎቱ ፡ አሜን ።

፻፷፮ ፤ ወእምድኅረ ፡ ፈጸምከኒ ፡ ጽሒፎተ ፡ ገድሉ ለብፁዕ ፡ ወለቅዱስ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይ ማኖት ።

፻፷፯ ፤ ኢይኅድግ ፡ ለዝሉፉ ፡ ኃይለ ፡ መንፈሱ ፡ ለከሂ ፡ ወለነ ።

፻፷፰ ፤ ወለጸሐፊሁኒ ፡ ኃጥእ ።

፻፷፱ ፤ በዝ ፡ ዓለም ፡ ወበዘይመጽእኒ ።

፻፸ ፤ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

፻፸፩ ፤ ወአሜን ፡ ለይኩን ፡ ለይኩን ።

፩ ፤ በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ ፡ አምላክ ።

፪ ፤ ንቀድም ፡ በረድኤተ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ንጽሕፍ ፡ እንከ ፡ ገድለ ፡ አቡነ ቅ ዱስ ፡ ተክለ ሃይማኖት ።

፫ ፤ እስመ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ብሂል ፡ ተክለ አብ ፡ ብሂል ።

፬ ፤ ዘተተክለ ፡ በአሚነ ፡ ሥላሴ ፡ አብ ፡ ወወ ልድ ፡ ወመንፈስ ፡ ቅዱስ ።

፭ ፤ ስምዕዎ ፡ በለብዎ ።

፮ ፤ ወአጽምዕዎ ፡ በኀድአት ፡ ወበአርምሞ ።

፯ ፤ ወግበሩ ፡ በዓለ ፡ መንፈሳዊተ ፤

፰ ፤ በተጋንዮ ፡ ወበማኅሌት ።

፱ ፤ ወበአስተርክቦ ።

፲ ፤ ከመ ፡ ትሳተፍዎ ፡ በሕማሙ ፡ አመ ፡ ዕለተ መርዓ ፡ እግዚኡ ።

፲፩ ፤ ወትጸርሑ ፡ ወትብሉ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ አበ ፡ መንፈስነ ።

፻፶፯ ፤ ሰባ ፡ ሁለት ፡ ቋንቋ ፡ የገለጸላቸው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነውና ፡

፻፶፰ ፤ አንተ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወዳጅ ፡ ላንተም እንደነሱ ፡ እርሱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይግ ለጽልህ ፡ በውነት ፡ ያለሐሰት ።

፻፶፱ ፤ የተሰወረ ፡ ሥራውን ፡ ይገለጽልህ ።

፻፷ ፤ ፍጹም ፡ ሥራውን ፡ ይግለጽልህ ።

፻፷፩ ፤ በሦስቱ ፡ ስም ፡ አምኖ ፡ እየተቀዳደመ ፡ የሠራውን ፡ የሥራውን ፡ ፍጹምነት ፡ ይግ ለጽልህ ።

፻፷፪ ፤ ይህ ፡ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማ ኖትም ፡ ካንተ ፡ ጋር ፡ ይኑር ፡ (በረድኤት አይለይህ ።)

፻፷፫ ፡ በመዓልትም ፡ በሌሊትም ።

፻፷፬ ፤ መከራውን ፡ እየታገሰ ፡ የሠራውን ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ይተርጕምልህ ።

፻፷፭ ፤ ጽፈሕ ፡ እስክትፈጽም ፡ ድረስ ፡ በውነት ፡ ያለሐሰት ።

፻፷፮ ፤ የብፁዕ ፡ ቅዱስ ፡ አባታችን የተክለ ፡ ሃይ ማኖትን ፡ ገድል ፡ ጽፈሕ ፡ ከጨረስክም ፡ በኋላ ።

፻፷፯ ፤ አንተንም ፡ እኛንም ፡ አይለየን ።

፻፷፰ ፤ ኃጥእ ፡ የሚሆን ፡ ጸሐፊውንም ።

፻፷፱ ፤ በዚህ ፡ ዓለም ። በሚመጣውም ፡ ዓለም ፡ አይለየን ።

፻፸ ፤ ለዘለዓለሙ ፡ በውነት ።

፻፸፩ ፤ በውነት ፡ ይሁን ፡ ይደረግልን ።

፩ ፤ አብን ፡ ወላዲ ፡ ወልድን ፡ ተወላዲ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ሠራጺ ፡ ብለን ፡ ምንም ፡ ለአጠይቆ ፡ አካላት ፡ ሦስት ፡ ስላልን ፡ በአካል ፡ ሦስት ፡ በባሕርይ ፡ በህልውና ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ ብለን ፡ አምነን ።

፪ ፤ በጌታችን ፡ በኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አጋዥ ነት ፡ ንጹሕ ፡ ክቡር ፡ የሚሆን ፡ ያባታችን ፡ የተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ገድል ፡ መጻፍን ፡ እንጀምራለን ።

፫ ፤ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ማለት ፡ የአብ ፡ ተክል ፡ ማለት ፡ ነውና ።

፬ ፤ እናት ፡ አባቱ ፡ በሦስቱ ፡ ስም ፡ አምነው ፡ ጸንተው ፡ ቢለምኑ ፡ የተገኘ ።

፭ ፤ ልብ ፡ አድርጋችሁ ፡ ስሙት ።

፮ ፤ ጸጥ ፡ ብላችሁ ፡ ስሙት ።

፯ ፤ መንፈሳዊ ፡ በዓል ፡ አድርጉ ።

፰ ፤ በምስጋና ፡ በመገዛት ።

፱ ፤ ሕሊናን ፡ በመወሰን ።

፲ ፤ ጌታ ፡ ምእመናንን ፡ በሚዋሐድበት ፡ ቀን ፡ በመከራ ፡ በክብር ፡ ትመስሉት ፡ ዘንድ ።

፲፩ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ የነፍሳችን ፡ አባት ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ብላችሁ ፡ ትጠሩታላ ችሁ ።

፲፪ ፤ ወያወሥአክሙ ፡ ውእቱኒ ፡ እንዘ ፡ ይብል።
፲፫ ፤ ናሁ ፡ አነ ፡ አቡክሙ ።
፲፬ ፤ ወአንትሙኒ ፡ ደቂቅየ ።
፲፭ ፤ ወመዋርስትየ ።
፲፮ ፤ ወዘንተ ፡ አእሚረክሙ ፡ ግበሩ ፡ በዓለ ፡ መን
ፈሳዊተ ።
፲፯ ፤ እመ ፡ ዕለተ ፡ ተዝካሩ ፡ ለአቡነ ፡ ቅዱስ ፡
**ተክለ ፡ ሃይማኖት ።**
፲፰ ፤ እመ ፡ ኵሉ ፡ ዘይገብር ፡ ተዝካረ ፡ በዓሉ ፡
አምሳለ ፡
፲፱ ፤ ፋሲካ ፡ ዮም ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ።
፳ ፤ ተዝካሩ ፡ ለብፁዕ ፡ ወቅዱስ ፡ **ተክለ ፡ ሃይ
ማኖት ፡** በስብሐት ።
፳፩ ፤ ወበጸሎት ።
፳፪ ፤ በዕጣን ።
፳፫ ፤ ወበቍርባን ።
፳፬ ፤ በአልብሶ ፡ ዕሩቃን ።
፳፭ ፤ ወበአጽግቦ ፡ ርኁባን ።
፳፮ ፤ ይደልዎ ፡ ይብሎ ፡ በይእቲ ፡ ዕለት ፡ አባ ፡
**አቡየ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።**
፳፯ ፤ ውእቱ ፡ ይቤሎ ፡ ነየ ፡ አቡከ ።
፳፰ ፤ ወያረፍቆ፡ ምስሌሁ፡ በምስሐ ፡ ፲ተ፻፡ ዓመት
በደብረ ፡ **ጽዮን ፡ ቅድስት ።**
፳፱ ፤ ይክፍለነ ፡ ለኵልነ ፡ ኪያሃ ።

፴ ፤ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።
፴፩ ፤ ወዘያስተትስ ፡ ወኢይገብር ፡ በዓለ ፡ መን
ፈሳዊተ ፡ ከመ ፡ በዓለ ፡ ፋሲካ ።
፴፪ ፤ በዕለተ ፡ ተዝካሩ ፡ ለብእሲ ፡ **እግዚአብ
ሔር ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።**
፴፫ ፤ በኵሉ ፡ አድያመ ፡ ሸዋ ፡ ወበሐውርቲሃ ።
፴፬ ፤ ለእመቦ ፡ ብእሲ ፡ ዘይገብር ፡ ግብረ ፡ ሥጋ፡
ለእመ ፡ አስተተ ፡ በሕሊናሁ ።
፴፭ ፤ በገቢረ ፡ ተዝካሩ ፡ በፍሥሐ ፡ ወበአክብሮ
ኢይደልዎ ፡ ይቤሎ ፡ በይእቲ ፡ ዕለተ ፡
**አቡየ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።**
፴፮ ፤ ውእቱኒ ፡ ኢይቤሎ ፡ ነየ ፡ አቡከ ።
፴፯ ፤ ወይቤሎ ፡ ኢየአምረከ ።
፴፰ ፤ ወኢአቀብከ ፡ ቃልየ ።
፴፱ ፤ ወኢገበርከ ፡ ተዝካርየ ።
፵ ፤ ወዘሰ ፡ ይቤሎ ፡ አቡየ ።
፵፩ ፤ ወይገብር ፡ ተዝካሮ ።
፵፪ ፤ ወዘጸውዓ ፡ ስሞ ። የሐዩ ፡ ሕይወተ ፡ ዘለ
ዓለም ፡ ምስሌሁ ።
፵፫ ፤ ወይከውን ፡ ብእሲ ፡ ውፁአ ፡ እምርስተ ፡
ዚአሁ ፡ ዘኢዐቀበ ፡ ቃሎ ፡ ወኢገብረ ፡ ተዝ
ካሮ ።
፵፬ ፤ እስመ ፡ ኵሎሙ ፡ ዘአዕረፉ ፡ ነፍሳት ።
ዘይሰመዩ ፡ ሃይማኖታውያን ።
፵፭ ፤ እመኒ ፡ ጻድቅ ፡ ወእመኒ ፡ ኃጥእ ፡ ዘሞቱ ።
፵፮ ፤ ኢያበውዕዎሙ ፡ ዘእንበለ ፡ ያብጽሕዎሙ
ኀበ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ **ተክለ ፡ ሃይማኖት ።**

፲፪ ፤ እሱም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ይመልስላችኋል።
፲፫ ፤ እነሆ ፡ እኔ ፡ አባታችሁ ፡ አለሁ ።
፲፬ ፤ እናንተም ፡ ልጆቼ ፡ ናችሁ ።
፲፭ ፤ ተወራራሾቼ ፡ ናችሁ ፡ ይላችኋል ።
፲፮ ፤ ይህንን ፡ አውቃችሁ ፡ መንፈሳዊ ፡ በዓል ፡
አድርጉ ።
፲፯ ፡ በክብር ፡ በአባታችን ፡ **በተክለ ፡ ሃይማኖት፡**
መታሰቢያ ፡ ቀን ።
፲፰ ፤ ዛሬ ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ እንደትንሣኤ፡ አድርጉ።

፲፱ ፤ ዝክሩን ፡ የሚያዘክር ፡ ሰው ፡ ሁሉ ።
፳ ፤ በምስጋና ።

፳፩ ፤ ጸሎት ፡ በማድረግ ።
፳፪ ፤ (ጧፍ) ፡ ዕጣን ፡ በመስጠት ።
፳፫ ፤ መሥዋዕት ፡ በማቅረብ ።
፳፬ ፤ የታረዘ ፡ በማልበስ ።
፳፭ ፤ የተራበ ፡ በማብላት ።
፳፮ ፤ አባቴ ፡ **ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡** ይለው ፡ ይገ
ባዋል ።
፳፯ ፤ እሱም ፡ እኔ ፡ አባትህ ፡ አለሁ ፡ ይለዋል ።
፳፰ ፤ ምእመናን ፡ በሚወርሷት ፡ በመንግሥተ ፡
ሰማያት ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ያኖረዋል ።
፳፱ ፤ ለሁላችንም ፡ እሷን ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያ
ትን ፡ ያድለን ።
፴ ፤ ለዘላለሙ ፡ በውነት ።
፴፩ ፤ ንቆ ፡ አቃሎ ፡ እንደትንሣኤ ፡ አድርጎ ፡
መንፈሳዊ ። በዓል ፡ የማያደርግ ፡ ግን ።
፴፪ ፤ **የእግዚአብሔር** ፡ባለሟል ፡ በሚሆን ፡ **በተ
ክለ ፡ ሃይማኖት ፡** መታሰቢያ ፡ ቀን ።
፴፫ ፤ በሸዋ ፡ አውራጃ ፡ ሀገር ፡ ሁሉ ።
፴፬ ፤ በልቡናው ፡ ንቆ ፡ አቃሎ ፡ ሥጋዊ ፡ ሥራ ፡
የሚሠራ ፡ ሰው ፡ ቢኖር ፡ ግን ።
፴፭ ፤ አክብሮ ፡ ደስ ፡ ብሎት ፡ ተዝካሩን ፡ በሚ
ያዘክርበት ፡ በዚያች ፡ ቀን ፡ አባቴ ፡ **ተክለ
ሃይማኖት ፡** ሊለው ፡ አይገባውም ።
፴፮ ፤ እሱም ፡ እኔ ፡ አባትህ ፡ አለሁ ፡ አይለውም።
፴፯ ፤ አላውቅህም ፡ ይለዋል ።
፴፰ ፤ ቃሌን ፡ አልጠበክምና ።
፴፱ ፤ ዝክሬን ፡ አላዘከርክምና ።
፵ ፤ አባቴ ፡ የሚለው ፡ ግን ።
፵፩ ፤ ዝክሩን ፡ የሚዘክር
፵፪ ፤ ስሙን ፡ የሚጠራ ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ የዘላለም፡
ሕይወት ፡ ያገኛል
፵፫ ፤ ዝክሩን ፡ ያልዘከረ ፡ ቃሉን ፡ ያልጠበቀ ፡
ከርስቱ ፡ ከመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የተለየ፡
ይሆናል ።
፵፬ ፤ የሞቱ ፡ ሰዎችን ፡ ነፍስ ፡ ሁሉ
ክርስቲያን ፡ የሚባሉ
፵፭ ፤ ጻድቅም ፡ ኃጥእም ፡ ቢሆን ፡ የሞቱትን ።
፵፮ ፤ ከክቡር ፡ አባታችን ፡ **ከተክለ ፡ ሃይማኖት**
ዘንድ ፡ ሳያደርሱ ፡ አይወስዷቸውምና ።

፹፯ ፡ ወሶበ ፡ ርእዮ ፡ ይቤሎ ፡ ውእቱ ።
፹፰ ፡ በከመ ፡ ሕፃን ፡ ዘይጼውዕ ፡ ኀበ ፡ አቡሁ ፡
በጊዜ ፡ ምንዳቤሁ ።
፹፱ ፡ ይጸርሕ ፡ ወይብል ፡ አባ ፡ ወአቡየ ፡ ተክለ ፡
ሃይማኖት ።
፺ ፡ ወያወሥእ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ነየ ፡ አቡከ ።
፺፩ ፡ ትሠርር ፡ ይእቲ ፡ ነፍስ ፡ ወትረፍቅ ፡ ውስተ
ሕፅኑ ፡ ኀበ ፡ አቡሃ ።
፺፪ ፡ ወለኃጥዕኒ ፡ ኢይወስድዎ ፡ ውስተ ፡ ሲኦል፡
ዘእንበለ ፡ ያብጽሕዎ ፡ ኀበ ፡ አቡነ ፡ ተክለ
ሃይማኖት ።
፺፫ ፡ ወሶበ ፡ ርእየቶ ፡ ነፍስ ፡ ኃጥእት ፡ ለክቡር ።
፺፬ ፡ ትጸርሕ ፡ ወትብል ፡ አባ ፡ ወአቡየ ፡ ተክለ
ሃይማኖት ።
፺፭ ፡ ወሶበ ፡ ርእየ ፡ አብ ፡ ክቡር ፡ ውስተ ፡ ነፍስ
ንስቲተ ፡ ምግባረ ፡ ሠናይ ።
፺፮ ፡ አው ፡ በጸውዖ ፡ ስሙ ።
፺፯ ፡ ወበገቢረ ፡ ተዝካሩ ።
፺፰ ፡ ይስእል ፡ ሎቱ ፡ ኀበ ፡ አምላኩ ፡ በከመ ፡
ኪዳኑ ፡ ማቴ ፡ ም ፡ ፲ ፡ ቍ ፡ ፵፪ ።
፺፱ ፡ ወይሬስያ ፡ ለዛቲ ፡ ነፍስ ፡ ውስተ ፡ ሕይ
ወት ፡ ዘለዓለም ።
፻ ፡ ወለነኒ ፡ ይርከበነ ፡ ሣህለ ፡ ትንብልናሁ።
፻፩ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።
፻፪ ፡ ወበእንተዝ ፡ እብለክሙ ፡ ኦ፡ ፍቁራንየ ።
፻፫ ፡ ክርስቶሳውያን ።
፻፬ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖታውያን ።
፻፭ ፡ ማኅበራውያን ።
፻፮ ፡ ግበሩ ፡ በዓለ ፡ መንፈሳዊተ ፡ በአምሳለ ፡
ፋሲካ ።
፻፯ ፡ ዕለተ ፡ ተዝካሩ ፡ ለአቡነ ፡ ክቡር ፡ ወቅዱስ።
፻፰ ፡ ትሩፈ ፡ ምግባር ።
፻፱ ፡ ወፍትወ ፡ ስን ።
፻፲ ፡ ብፁዓዊ ፡ ማር ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።
፻፲፩ ፡ እለ ፡ ተጋባዕክሙ ፡ ዮም ፡ ውስተ ፡ ዛቲ
ቤተ ፡ ክርስቲያን ።
፻፲፪ ፡ ካህናት ፡ ወዲያቆናት ፡ እድ ፡ ወአንስት ፡
መሃይምናን ፡ ወመሃይምንት ።
፻፲፫ ፡ አዕሩግ ፡ ወሕፃናት ።
፻፲፬ ፡ ሥዩማን ፡ ወመሳፍንት ።
፻፲፭ ፡ ወሕዝብ ።
፻፲፮ ፡ ስምዑ ፡ ዜናሁ ፡ መንፈሳዊተ ።
፻፲፯ ፡ ሕማማተ ፡ ገድሉ ፡ አምላካዊተ ።
፻፲፰ ፡ ወሩጸተ ፡ በድሩ ፡ መስተፋጥኒተ ።
፻፲፱ ፡ ፍሥሐ ፡ ለክሙ ።

፹፯ ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትንም ፡ ባየ ፡
ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ይለዋል ።
፹፰ ፡ በመከራ ፡ ጊዜ ፡ ልጅ ፡ አባቱን ፡ እንዲጠራ ።
፹፱ ፡ አባቴ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ብሎ ፡ ይጠ
ራዋል ።
፺ ፡ እሱም ፡ እኔ ፡ አባትህ ፡ አለሁ ፡ ይለዋል።
፺፩ ፡ ይች ፡ ነፍስ ፡ ፈጥና ፡ ሂዳ ፡ ካባቷ ፡ ከተክለ፡
ሃይማኖት ፡ አጠገብ ፡ ትቀመጣለች ።
፺፪ ፡ ኃጥዕም ፡ ቢሆን ፡ ከአባታችን ፡ ከተክለ ፡
ሃይማኖት ፡ ዘንድ ፡ ሳይደርስ ፡ ወደሲኦል ፡
አይወስዱትም ፡
፺፫ ፡ የኃጥኡ ፡ ነፍስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖትን ፡ ባየች
ጊዜ ።
፺፬ ፡ አባቴ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ብላ ፡ ትጠራ
ዋለች ።
፺፭ ፡ በዚች ፡ ነፍስ ፡ ክቡር ፡ አባታችንም ፡ ጥቂት
በጎ ፡ ሥራ ፡ ባገኘባት ፡ ጊዜ ።
፺፮ ፡ ስሙን ፡ በመጥራትም ፡ ቢሆንም ።
፺፯ ፡ ዝክሩን ፡ በማዘከርም ፡ ቢሆን
፺፰ ፡ ቃል ፡ ኪዳን ፡ እንደተቀበለ ፡ ወደፈጣሪው፡
ይለምንላታል ።
፺፱ ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ያገባታል ፡
ያኖራታል ።
፻ ፡ ለኛም ፡ በልመናው ፡ የምናገኘው ፡ ይቅ
ርታ ፡ ይደረግልን ።
፻፩ ፡ ለዘላለሙ ፡ በውነት ።
፻፪ ፡ ወዳጆቼ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ እንዲህ ፡ እላች
ኋለሁ ።
፻፫ ፡ የክርስቶስ ፡ ወገን ፡ የሆናችሁ ።
፻፬ ፡ የተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ወገን ፡ የሆናችሁ ።
፻፭ ፡ ፍቅር ፡ አንድነት ፡ ያላችሁ ።
፻፮ ፡ እንደ ፡ ትንሣኤ ፡ አድርጋችሁ ።
፻፯ ፡ ንጹሕ ፡ ክቡር ፡ የሚሆን ፡ ያባታችሁ ፡
የመታሰቢያውን ፡ ቀን ፡ አክብሩ ።
፻፰ ፡ በሥራ ፡ ፍጹም ፡ የሆነ ።
፻፱ ፡ ሥነ ፡ ምግባሩ ፡ የተወደደ ።
፻፲ ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።
፻፲፩ ፡ ዛሬ ፡ በዚች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተሰበሰ
ባችሁ ።
፻፲፪ ፡ ቀሳውስቱም ፡ ዲያቆናቱም ፡ በክርስቶስ ፡
ያመናችሁ ፡ ወንድም ፡ ሴትም ።
፻፲፫ ፡ ልጅም ፡ ዐዋቂም ።
፻፲፬ ፡ ሹማምንትም ፡ መሳፍንትም ።
፻፲፭ ፡ ሕዝቡም ።
፻፲፮ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እየረዳው ፡ የሠራውን ፡
ሥራ ፡ ስሙ ።
፻፲፯ ፡ አምላክነቱን ፡ ለማገልገል ፡ የተቀበለውን ፡
መከራ ።
፻፲፰ ፡ እየተፋጠነ ፡ የሠራውን ፡ ሥራ ፡ ስሙ ።
፻፲፱ ፡ ለናንተ ፡ ተድላ ፡ ደስታችሁ ፡ ነውና ።

፳ ፤ ወረብሐ ፡ ለነፍስክሙ ፡ ወመድኃኒት ፡ ለሥጋክሙ ።
፳፩ ፤ ወመንጽሔ ፡ ለርስሐትክሙ ።
፳፪ ፤ ወፍጻሜ ፡ ለውጣኒክሙ ።

፳፫ ፤ መርስ ፡ ወዛኅን ፡ ለሐመርክሙ ።
፳፬ ፤ ወዕቅበተ ፡ ለአዕሩጊክሙ ።
፳፭ ፤ ወሕጽንት ፡ ሠናይ ፡ ለሕፃናቲክሙ ።
፳፮ ፤ ወጥበብ ፡ ለወራዙቲክሙ ።
፳፯ ፤ ወሥራይ ፡ ለቍስለ ፡ ነፍስክሙ ።
፳፰ ፤ ወዓምድ ፡ ጽኑዕ ፡ ለሃይማኖትክሙ ።
፳፱ ፤ ጼወን ፡ ወኃይል ፡ ወቅጽር ፡ ለሀገርክሙ ።
፴ ፤ መምሕፃን ፡ ለግፉዓኒክሙ ፡ ዝንቱ ፡ አቡነ ።

፴፩ ፤ ዝንቱ ፡ መምህርነ ።
፴፪ ፤ ዝንቱ ፡ ፍርቃንነ ።
፴፫ ፤ ዝንቱ ፡ ተስፋነ ፤
፴፬ ፤ ዝንቱ ፡ ግዕዛንነ ።
፴፭ ፤ ዝንቱ ፡ አብ ፡ አረቦነ ፡ ርስትነ ።
፴፮ ፤ ዝንቱ ፡ አብ ፡ ክዳን ፡ ለእርቃንነ ።
፴፯ ፤ መብልዓ ፡ ጽድቅ ፡ ለረሀብነ ።
፴፰ ፤ ስቴ ፡ ሕይወት ፡ ለጽምዕነ ።
፴፱ ፤ ምርጉዝ ፡ ለድካምነ ።
፵ ፤ ሐዳሬ ፡ ሐመርነ ፡ እምነ ፡ መዋግዲሃ ፡ ለባሕረ ፡ ዓለም ፡

፵፩ ፤ ዘውእቶሙ ፡ ኃይላተ ፡ አጋንንት ።
፵፪ ፤ ወመናፍስተ ፡ ርኩሳን ።

፵፫ ፤ እመትሕተ ፡ ሰማይ ፡ ዘይመልኩ ፡ ዓለመ፡ ጽልመት ።
፵፬ ፤ እለ ፡ ይሰውቁ ፡ ሐመረ ፡ በነፋስ ፡ በዓይነ፡ ኃጢአት ፡ ዘጽልመት ።
፵፭ ፤ ወዘንተ ፡ አእምሮ ፡ ጳውሎስ ፡ ላዕከ ፡ ይቤ።
ኤፌሶን ፡ም ፮ ቍ ፡ ፲፪ ።
፵፮ ፤ እስመ ፡ ቀትልክሙ ፡ ኢኮነ ፡ ምስለ ፡ ዘሥጋ ወደም ።
፵፯ ፤ አላ ፡ ምስለ ፡ መናፍስት ፡ ርኩሳን ፡ እለ ፡ ይመልኩ ፡ ዓለመ ፡ ጽልመት ።
፵፰ ፤ ወንሥኡ ፡ ንዋየ ፡ ሐቅሉ ፡ ለክርስቶስ ።

፵፱ ፤ ወሰይፈ ፡ ዘመንፈስ ፡ ቅዱስ ።

፶ ፤ በአማን ፡ ዝንቱ ፡ አቡነ ፡ ንዋየ ፡ ኃቅል ፡ ለጸብዕነ ።

፶፩ ፤ ወሰይፍ ፡ በሊህ ፡ ዘመለኮት ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ፡ ንጽሕት ።
፶፪ ፤ ከመ ፡ ይቅትሎሙ ፡ ወይዝብጠሙ ፡ ለአራዊተ ፡ ገዳም ፡ እለ ፡ የኀጕሉ ፡ ነፍሰ ፡ ሰብእ ።
፶፫ ፤ ዘወእቶሙ ፡ ሰይጣናት ፡ ማኅጕላን ፡ በእከየ ምግባሪሆሙ ።

---

፳ ፤ ለሥጋችሁ ፡ መጠበቂያ ፡ ለነፍሳችሁ ፡ መዳኛ ፡ ነውና ።
፳፩ ፤ ኃጢአታችሁን ፡ የሚያነጻ ።
፳፪ ፤ ለወጣኒነታችሁ ፡ ከፍጻምነት ፡ መድረሻ ፡ ነውና ።
፳፫ ፤ ለመርከብ ፡ ሰውነታችሁ ፡ ጸጥታ ፡ ነውና ።
፳፬ ፤ ለሽማግሎች ፡ መጠበቂያ ።
፳፭ ፤ ለልጆቻችሁ ፡ በጎ ፡ ማደጊያ ።
፳፮ ፤ ለጉልማሶቻችሁ ፡ ዕውቀት ።
፳፯ ፤ ለነፍሳችሁ ፡ መድኃኒት ።
፳፰ ፤ ለሃይማኖታችሁ ፡ መጽኛ ።
፳፱ ፤ ለሀገራችሁ ፡ አጽር፡ ቅጽር ፡ ኃይል ፡ ነውና።
፴ ፤ ይህ ፡ አባታችን ፡ ለተበደሉት ፡ መማፀኛ፡ ነውና ።
፴፩ ፤ ይህ ፡ አስተማሪያችን ።
፴፪ ፤ ይህ ፡ መድኃኒታችን ።
፴፫ ፤ ይህ ፡ አለኝታችን ።
፴፬ ፤ ይህ ፡ ነጻ ፡ አድራጊያችን ።
፴፭ ፤ ይህ ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ፊለማችን ።
፴፮ ፤ ኀታረዝን ፡ ጊዜ ፡ ልብሳችን ።
፴፯ ፤ በተራብን ፡ ጊዜ ፡ እውነተኛ ፡ ምግባችን።
፴፰ ፤ በተጠማን ፡ ጊዜ ፡ የሕይወት ፡ መጠጣችን ።
፴፱ ፤ በደከምን ፡ ጊዜ ፡ ምርኩዛችን ።
፵ ፤ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ባሕር ፡ ማዕበል ፡ መርከብ፡ ሰውነታችንን ፡ በረድኤቱ ፡ እየቀዘፈ ፡ የሚያሻግረን ።
፵፩ ፤ እነሀም ፡ የአጋንንት ፡ ጸቦች ፡ ናቸው ።
፵፪ ፤ ርኩሳን ፡ ረቂቃን ፡ የሚሆኑ ፡ አጋንንት ፡ ናቸው ።
፵፫ ፤ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ዓለመ ፡ ጽልመትን ፡ የሚገዙ ።
፵፬ ፤ በድንቁርና ፡ በሚሠራ ፡ በኃጢአት ፡ ጥፋት፡ ነፋስ ፡ መርከብ ፡ ሰውነታችንን ፡ የሚያውኩ
፵፭ ፤ ይህንም ፡ ዐውቆ ፡ ሐዋርያ ፡ ጳውሎስ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፤
፵፮ ፤ ሰልፋችሁ ፡ ከሥጋዊ ፡ ከደማዊ ፡ ሰው ፡ ጋራ አይደለምና ።
፵፯ ፤ ዓለመ ፡ ጽልመትን ፡ ከሚገዙ ፡ ከረቂቃን፡ አጋንንት ፡ ጋራ ፡ ነው ፡ እንጂ ።
፵፰ ፤ የክርስቶስ ፡ የበዳ ፡ ጸብቱን ፡ ያዙ ፡ ማለት ፡ ሃይማኖትን ።
፵፱ ፤ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ሰይፍ ፡ ታጠቁ ፡ አለ፡ (ጸሎትን ፡) ያዙ ፡ ብሎ ፡ ተናገረ ።
፶ ፤ በእውነት ፡ ይህ ፡ አባታችን ፡ ከአጋንንት ፡ ጋር ፡ በምንዋጋበት ፡ ጊዜ ፡ የበዳ ፡ ጸብታችን ፡ ነው ።
፶፩ ፤ የተሳለ ፡ የመለኮት ፡ ሰይፍ ፡ በእጁ ፡ የተያዘ ፡ ነው ።
፶፪ ፤ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ የሚጐዱ ፡ በበረኃ ፡ ያሉ ፡ አራዊትን ፡ ድል ፡ ያደርጋቸው ፡ ዘንድ ።
፶፫ ፤ እኒህም ፡ በክፉ ፡ ሥራቸው ፡ ሰውን ፡ የሚጐዱ ፡ ሰይጣናት ፡ ናቸው ።

፻፲፬ ፡ ናሁ ፡ ዝንቱ ፡ አቡነ ፡ ይትቃተል ፡ ወይትበ
አስ ፡ በእንቲአነ ፡ ወበእንተ ፡ ነፍስነ ።
፻፲፭ ፡ አልቦ ፡ ዘይብለነ ።
ሮሚ ፡ ም ፡ ፰ ፡ ቍ ፡ ፴፱ ።
፻፲፮ ፡ ወአልቦ ፡ ዘይክለነ ።
፻፲፯ ፡ እስመ ፡ ኃይለ ፡ **መንፈስ ፡ ቅዱስ** ፡ ብነ ፡
ምስሌነ ።
፻፲፰ ፡ አልቦ ፡ ዘይክለነ ።
፻፲፱ ፡ እንዘ ፡ ሀብቱ ፡ ይረድአነ ።
፻፳ ፡ ወእንዘ ፡ ጸጋሁ ፡ ይባልሐነ ።
፻፳፩ ፡ ወእንዘ ፡ ጸሎቱ ፡ ምስሌነ ።
፻፳፪ ፡ እንዘ ፡ ተንብሎቱ ፡ ያድኅነነ ።
፻፳፫ ፡ ወእንዘ ፡ ተንብሎቱ ፡ ይሰውቀነ ።
፻፳፬ ፡ እንዘ ፡ ስእለቱ ፡ ያኀሥአነ ።
፻፳፭ ፡ በዘከመዝ ፡ ወበዘይመስሎ ፡ ይረድአ ፡ ዕዘ
ይገብር ። ተዝካሮ ፡ ብፍሥሐ ፡ ወበሐሴት ።
፻፳፮ ፡ በበዓል ፡ መንፈሳዊ ፡ ከመ ፡ አምሳለ ፡ በዓለ
ወልድ ።
፻፳፯ ፡ በዓለ ፡ ተዝካሩ ፡ ለአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።
፻፳፰ ፡ ዘአዕረፈ ፡ ዮም ፡ በዛቲ ፡ ዕለት ።
፻፳፱ ፡ አመ ፡ ፳ ወ፬ ለወርኃ ፡ አሲር ፡ ዝውእቱ ፡
ወርኃ ፡ ነሐሴ ።
፻፴ ፡ ስምዑ ፡ ሰማዕያን ፡ ወአጽምዑ ፡ አ ፡ ማኅ
በረ ፡ ክርስቲያን ።
፻፴፩ ፡ ወአጽምዑ ፡ በፍርሃት ፡ ዘእንበለ ፡ ተደ
ንጽዎ ።
፻፴፪ ፡ ወለብዉ ፡ ዘእንበለ ፡ ተአንትሎ ።
፻፴፫ ፡ ወአእምሩ ፡ ዘእንበለ ፡ አስትቶ ።
፻፴፬ ፡ ኢንኩን ፡ ከመ ፡ አብዳን ፡ መናፍቃን ።
፻፴፭ ፡ እለ ፡ ኢየኀብሩ ፡ በርትዕት ፡ ሃይማኖት ፡
ኦርቶዶክሳዊት ።
፻፴፮ ፡ እሉ ፡ እሙንቱ ፡ እለ ፡ ይሬስይዎ ፡ ወያመስ
ልዎ ፡ ለቃለ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ ከመ ፡ ዝንጋዔ
፻፴፯ ፡ ወከመ ፡ ነገረ ፡ በሐውርት ።
፻፴፰ ፡ ይትፈቀድ ፡ በኀቤሆሙ ፡ ፈድፋደ ፡ እመ
ዓር ፡ ወሦከር ።
፻፴፱ ፡ እምነ ፡ ቃለ ፡ **እግዚአብሔር** ።
፻፵ ፡ እስመ ፡ አብድ ፡ ብእሲ ፡ ምንተ ፡ ተናገርከ ፡
በነገረ ፡ መላእክት ።
፻፵፩ ፡ በምሥጢረ ፡ መለኮት ፡ በቃለ ፡ **እግዚአ
ብሔር** ፡ ዘኢየአምን ።
፻፵፪ ፡ ይመስሎ ፡ ዝንቱ ፡ ዝንጋዔ ።
፻፵፫ ፡ ሶበ ፡ አህለቀ ፡ ነገሮ ፡ ምንተ ፡ ትብል ፡
ይብለከ ።
፻፵፬ ፡ ወበእንተዝ ፡ ይብል ፡ ጥበበ ፡ ሲራክ ።
፻፵፭ ፡ እመቦ ፡ ዘይነግር ፡ ቃለ ፡ **እግዚአብሔር** ፡
በኀበ ፡ ኢይሰምዖ ።
፻፵፮ ፡ ይመስል ፡ ከመ ፡ ዘያስተጣግዕ ፡ አግዕልተ ፡
ዲበ ፡ መልዕልተ ፡ ኖፃ ።

፻፲፬ ፡ እነሆ ፡ ይህ ፡ አባታችን ፡ ስለኛ ፡ ነፍስ ፡
ይዋጋልናል ።
፻፲፭ ፡ ምንድናችሁ ፡ የሚለን ፡ የለም ።
፻፲፮ ፡ ድል ፡ የሚነሣን ፡ የለም ።
፻፲፯ ፡ **የመንፈስ ፡ ቅዱስ** ፡ ኃይል ፡ አድሮብናልና ።
፻፲፰ ፡ ድል ፡ የሚነሣን ፡ የለም ።
፻፲፱ ፡ ሀብቱ ፡ ሲረዳን ።
፻፳ ፡ ቸርነቱ ፡ ሲያድነን ።
፻፳፩ ፡ ልመናው ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ ሲሆን ።
፻፳፪ ፡ ልመናው ፡ ሲያድነን ።
፻፳፫ ፡ አማላጅነቱ ፡ ሲደግፈን ።
፻፳፬ ፡ ልመናው ፡ ሲያስነሣን ።
፻፳፭ ፡ በእንዲህ ፡ ያለ ፡ ይህንም ፡ በመሰለ ፡ ሁሉ
ደስ ፡ ብሎት ፡ ዝክሩን ፡ የሚያዘክር ፡ ሰውን
ይረዳዋል ።
፻፳፮ ፡ እንደጌታ ፡ በዓል ፡ እንደትንሣኤ ፡ መንፈ
ሳዊ ፡ በዓል ፡ አድርጎ ።
፻፳፯ ፡ የክቡር ፡ አባታችን ፡ **የተክለ ፡ ሃይማኖት** ፡
የመታሰቢያውን ፡ ቀን ።
፻፳፰ ፡ ዛሬ ፡ በዚች ፡ ቀን ፡ ያረፈባት ።
፻፳፱ ፡ ይኸውም ፡ በነሐሴ ፡ በሀያ ፡ አራት ፡ ቀን
ነው ።
፻፴ ፡ እናንት ፡ የክርስቲያን ፡ ወገኖች ፡ ስሙ ።
፻፴፩ ፡ ዕዝነ ፡ ልቡናችሁን ፡ ከፍታችሁ ፡ ስሙ ።
፻፴፪ ፡ ቸል ፡ ሳትሉ ፡ አስተውሉ ።
፻፴፫ ፡ ሳትንቁ ፡ ሳታቃልሉ ፡ ዕወቁ ።
፻፴፬ ፡ እንደሰነፎች ፡ እንደመናፍቃን ፡ አንሁን ።
፻፴፭ ፡ **በክርስቶስ** ፡ ስም ፡ በምትሆን ፡ በቀናች ፡
ሃይማኖት ፡ ከኛ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ የማይሆኑ ።
፻፴፮ ፡ ወንጌልን ፡ አእምሮ ፡ ማጣት ፡ የሚያስ
መስሉት ።
፻፴፯ ፡ እንደ ፡ ቋንቋ ፡ አድርገው ።
፻፴፰ ፡ ድንቁርናው ፡ በነሱ ፡ ዘንድ ፡ እንደማርና ፡
እንደ ፡ ሦከር ፡ ይወደዳል ።
፻፴፱ ፡ ወንጌልን ፡ ከመስማት ፡ ይልቅ ።
፻፵ ፡ አንተ ፡ ሰነፍ ፡ ሰው ፡ በመላእክት ፡ ቋንቋ ፡
ምን ፡ ተናገርክ ፡ ይልሐል ።
፻፵፩ ፡ ጌታ ፡ ባስተማራት ፡ በወንጌል ፡ የማያምን ፡
ነው ።
፻፵፪ ፡ አእምሮ ፡ ማጣት ፡ ይመስለዋልና ።
፻፵፫ ፡ ነገርክን ፡ በጨረስክ ፡ ጊዜ ፡ ምንትላለህ ፡
ይልሐል ።
፻፵፬ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ሲራክ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡
ተናገረ ።
፻፵፭ ፡ ለማይሰማ ፡ ሰው ፡ ትምህርት ፡ የሚያስ
ተምር ።
፻፵፮ ፡ በአሸዋ ፡ ላይ ፡ ካብን ፡ የሚክብ ፡ ሰው ፡
ይመስላል ።

፻፵፯፤ ወዘሰ ፡ ይነግር ፡ ኀበ ፡ ይሰምዖ ፡ ዘርዓ ፡
ሠናየ ፡ ዘይዘርዕ ፡ ውስተ ፡ ዕሙቅ ፡ መሬት ።

፻፵፰፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ ጠቢብ ፡ ለጠቢብ ፡ ከመ ፡
ይወስክ ፡ ጥበበ ።

፻፵፱፤ ወለአብድሰ ፡ ለእመ ፡ ሀለፍከ ፡ ወገሠጽከ ፡
በምንትኑ ፡ ይሰምዓከ ።

፻፶፤ ወኢይትዌከፍ ፡ ቃለከ ።

፻፶፩፤ አላ፡ ይጸልዐከ ፡ ዘነበረ ፡ እንዘ ፡ ያፈቅረከ ።

፻፶፪፤ ዳዊትኒ ፡ ይቤ ።

፻፶፫፤ መዝ ፡ ፻፰ ቍ ፫ ፡ ሶበ ፡ ትረክቦ ፡ ኃጢ
አቱ ፡ ይጸልዓ ።

፻፶፬፤ ከማሁ ፡ ይጸልዓከ ።

፻፶፭፤ አንትሙሰ ፡ አፍቁራንየ ፡ ዮም ፡ ፍሥሐክሙ ።

፻፶፮፤ ዮም ፡ በዓልክሙ ።

፻፶፯፤ ዮም ፡ ፍርቃንክሙ ።

፻፶፰፤ ዮም ፡ ተስፋክሙ ።

፻፶፱፤ ዮም ፡ መሥዋዕትክሙ ።

፻፷፤ ዮም ፡ መድኃኒተ ፡ ነፍስክሙ ።

፻፷፩፤ ዮም ፡ ሰላምክሙ ።

፻፷፪፤ ስምዑ ፡ ዜናሁ ፡ ለክቡር ፡ ወጻድቅ ፡ ወን
ጹሕ ፡ አቡክሙ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።

፻፷፫፤ እስመ ፡ ይቤ ፡ መጽሐፍ ።

፻፷፬፤ በሰሚዐ ፡ ዜናሆሙ ፡ ለጻድቃን ፡ ይትፌ
ሥሑ ፡ ኃጥአን ።

፻፷፭፤ ወበሰሚዓ ፡ ዜናሆሙ ፡ ለፍሡሐን ፡ ያን
ፈርዕጹ ፡ ኅዙናን ።

፻፷፮፤ ወበሰሚዓ ፡ ዜናሆሙ ፡ ለዕጉሣን ፡ የኀ
ድኡ ፡ ምኡዓን ።

፻፷፯፤ ወበሰሚዓ ፡ ዜናሆሙ ፡ ለትሑታን ፡ ይቴ
ሐቱ ፡ ዕቡያን ።

፻፷፰፤ ወበሰሚዓ ፡ ዜናሆሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ይት
መየጡ ፡ ዝሉፋን ።

፻፷፱፤ ወበሰሚዓ ፡ ዜናሆሙ ፡ ለምእመናን ፡ ይት
መየጡ ፡ ከሐድያን ።

፻፸፤ ወዘንተ ፡ ኵሎ ፡ አእሚሮ ፡ ይቤ ፡ ነቢይ ፡
በሰሚዓ ፡ ዜናሆሙ ፡ ለቅዱሳን ፡ ይትፌ
ሥሑ ፡ አሕዛበ ፡ ምድር ።

፻፸፩፤ ወበእንተዝ ፡ እብለክሙ ፡ ስምዑኒ ።

፻፸፪፤ ስምዑ ፤ ዜናሁ ፡ ለክቡር፡ወብፁዕ፡አቡን
ማር ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ።

፻፸፫፤ ዘይጥዕም ፡ እመዓር ፡ ወሦከር ።

፻፸፬፤ ወይትፌተው ፡ እምወርቅ ፡ ወእምብሩር ፡
ወእምጳዝዮን ወሰንፔር ።

፻፸፭፤ ስምዑ ፡ ዜናሁ ፡ ለቅዱስ ፡ ወክቡር ።

፻፸፮፤ ፍትወ ፡ ምግባር ።

፻፸፯፤ ወሠናይ ፡ በአምሳሉ ።

፻፸፰፤ ወያስተፌሥሕ ፡ ልበ ።

፻፵፯፤ ለሚሰማ ፡ ሰው ፡ የሚያስተምር ፡ ግን ፡
የተበጠረ ፡ ዘርን ፡ በጥልቅ ፡ መሬት ፡ የሚ
ዘራ ፡ ሰውን ፡ ይመስላል ፡ ብሏል ።

፻፵፰፤ ብልህን ፡ ምከረው ፡ (አስተምረው ፡ ዕው
ቀትን ፡ ይጨምር ፡ ዘንድ ።

፻፵፱፤ ሰነፍ ፡ ሰውን ፡ ግን ፡ ብትመክረው ፡ ብታ
ስተምረው ፡ በምን ፡ ይሰማሃል ።

፻፶፤ ነገርክን ፡ አይቀበለውምና ።

፻፶፩፤ ሲወድህ ፡ የነበረው ፡ ይጠላሃል ፡ እንጂ ።

፻፶፪፤ ዳዊትም ፡ እንዲህ ፡ ብሏል ።

፻፶፫፤ ኃጢአቱ ፡ ፍዳ ፡ ይዛ ፡ በተገናኘችው ፡
ጊዜ ፡ ይጠላታል ።

፻፶፬፤ አንተ ፡ ሰነፍ ፡ ሰውንም ፡ ብትመክረው ፡
ይጠላሃል ።

፻፶፭፤ ወዳጆቼ ፡ እናንተ ፡ ግን ፡ ዛሬ ፡ ተድላ ፡
ደስታ ፡ የምታደርጉበት ፡ ቀን ፡ ነው ።

፻፶፮፤ ዛሬ ፡ የምታርፉበት ፡ ቀን ፡ ነው ።

፻፶፯፤ ድኅነት ፡ የምታገኙበት ፡ ነው ።

፻፶፰፤ ተስፋችሁን ፡ የምታገኙበት ፡ ነው ።

፻፶፱፤ መሥዋዕት ፡ የምታቀርቡበት ፡ ነው ።

፻፷፤ ድኅነተ ፡ ነፍስ ፡ የምታገኙበት ፡ ነው ።

፻፷፩፤ ፍቅር ፡ አንድነት ፡ የምታደርጉበት፡ ነውና።

፻፷፪፤ የንጹሕ ፡ የክቡር ፡ አባታችሁ ፡ የተክለ ፡
ሃይማኖትን ፡ ነገር ፡ ስሙ ።

፻፷፫፤ መጽሐፍ ፡ እንዲህ ፡ ብሏልና ።

፻፷፬፤ የጻድቃንን ፡ ነገር ፡ በመስማት ፡ ኃጥአን ፡
ደስ ፡ ይላቸዋል ።

፻፷፭፤ ደስ ፡ ያላቸው ፡ የምእመናንን ፡ ነገር ፡ በመ
ስማት ፡ ያዘኑ ፡ ሰዎች ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ።

፻፷፮፤ መከራውን ፡ የሚታገሡ ፡ ሰዎች ፡ ነገር ፡
በመስማት ፡ ድል ፡ የሚሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ይበ
ረታሉ ።

፻፷፯፤ ራሳቸውን ፡ የሚያዋርዱን ፡ ሰዎች ፡ ነገር ፡
በመስማት ፡ ትቢተኞች ፡ ይዋረዳሉ ።

፻፷፰፤ የቅዱሳንን ፡ ነገር ፡ በመስማት ፡ ኃጢአት ፡
የሚሠሩ ፡ ሰዎች ፡ ወደንስሐ ፡ ይመለሳሉ ።

፻፷፱፤ የምእመናንን ፡ ነገር ፡ በመስማት ፡ የሚ
ክዱ ፡ ሰዎች ፡ ወደሃይማኖት ፡ ይመለሳሉ ።

፻፸፤ ነቢይ ፡ ይኽን ፡ ሁሉ ፡ ዐውቆ ፡ የቅዱሳ
ንን ፡ ነገር ፡ በመስማት ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ደስ ፡ ይላቸዋል ፡ ብሎ ፡ ተና
ግሯልና ።

፻፸፩፤ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ስሙኝ ፡ እላችኋለሁ ።

፻፸፪፤ የክቡር ፡ የብፁዕ ፡ አባታችን ፡ የተክለ ፡
ሃይማኖትን ፡ ነገር ፡ ስሙ ።

፻፸፫፤ ከመዓር ፡ ከሦከር ፡ ይልቅ ፡ የሚጣፍጥ ።

፻፸፬፤ ከወርቅ ፡ ከብር ፡ ከዕንቍ ፡ ይልቅ ፡ የሚ
ወደድ ።

፻፸፭፤ የክቡር ፡ አባታችን ፡ ነገር ፡ ስሙ ።

፻፸፮፤ ሥራው ፡ ያማረ ፡ የተወደደ ፡ በሥራው ፡
ሁሉ ፡ ፍጹም ፡ የሆነ ።

፻፸፯፤ መልኩ ፡ ያማረ ።

፻፸፰፤ ልቡና ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ።

፻፸፱ ፤ ወያጠልል ፡ አዕፅምተ ፡ ለዘይሰምዖ ፡ ወዘ
ያነብብ ፡ ብእርትዖ ፡፡

፻፹ ፤ ስምዕዎ ፡ ወአጽምዕዎ ፡ ለገድለ ፡ ጻማሁ ፡
**ለአቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡፡**

፻፹፩ ፤ ብፁዓዊ ፡ እንዘ ፡ ይጽሕፍ ፡ ወይብል ፡፡

፻፹፪ ፤ ወእንዘ ፡ ይርዕድ ፡ ይነግር ፡፡

፻፹፫ ፤ ወእንዘ ፡ ይደነግፅ ፡ ይፌክር ፡፡

፻፹፬ ፤ እንዘ ፡ ያወሥኢ ፡ ወይብል ፡፡

፻፹፭ ፤ ወእንዘ ፡ ያከብር ፡ ወያልዕል ፡፡

፻፹፮ ፤ ስምዕዎ ፡ ወአጽምዕዎ ፡ በልብክሙ ፤

፻፹፯ ፤ ዘይትነበብ ፡ **በስመ ፡ አብ ፡ ወወልድ ፡ ወመ
ንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፩ ፡ አምላክ ፡፡**

፻፹፰ ፤ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡፡ ወስግደት ፡፡

፻፹፱ ፤ ወአኰቴት ፡፡

፻፺ ፤ ዘእንበለ ፡ ፍልጠት ፡፡

፻፺፩ ፤ ወወልጦት ፡፡

፻፺፪ ፤ ዕሩያን ፡ በመለኮት ፡፡

፻፺፫ ፤ ወይኩን ፡ ሣህል ፡ ወምሕረት ፡ ላዕለ ፡
ኵልነ ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያን ፡ ወላዕለ ፡ ሀገ
ሪትነ ፡ ኢትዮጵያ ፤

፻፺፬ ፤ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ፡፡

፻፺፭ ፤ ንዑ ፡ ተጋብኡ ፡ ከመ ፡ ትስምዑ ፡ ዜና ፡
ሠናየ ፡፡

፻፺፮ ፤ ንዑ ፡ ተጋብኡ ፡ በጕጕዓ ፡፡

፻፺፯ ፤ ከመ ፡ ይጌጉዑ ፡ ጽሙዕ ፡ ኀበ ፡ ሙሒዘ ፡
ማይ ፡፡

፻፺፰ ፤ ከመ ፡ ይስተይ ፡ ዕገነ ፡ ልብክሙ ፡ ወከመ፡
ትሰምዑ ፡ ገድለ ፡ አቡክሙ ፡፡

፻፺፱ ፤ ክሥት ፡ አፉየ ፡ እግዚኦ ፡ ከመ ፡ እንብብ ፡
ወእፌክር ፡ ዘከመ ፡ ተጋደለ ፡፡

፪፻ ፤ ወዘከመ ፡ ገብረ ፡ ተአምረ ፡ ወመንክረ ፡
በእደዊሁ ፡፡

፪፻፩ ፤ ምላዕ ፡ አፉየ ፡ አእምሮ ፡ ጥበብከ ፡፡

፪፻፪ ፤ ከመ ፡ እዜኑ ፡ ለአግብርቲከ ፡ ክርስቲያን ፡፡

፪፻፫ ፤ ተራድአኒ ፡ ለፈጽሞቱ ፡ ዘገብረ ፡ አቡነ ፡
ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ በትዕግሥቱ ፡፡

፪፻፬ ፤ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ፡፡

፩ ፤ **በስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሥሉስ ፡** በኢተ
ሌልዮ ፡፡

፪ ፤ ዋሕድ ፡ በኢተሬልዮ ፡፡

፫ ፤ ከዱነ ፡ መለኮት ፡ እምተህልዮ፤፡፡

፬ ፤ ወኀሩመ ፡ ሥልጣነ ፡ እምተሞክስዮ ፡፡

፻፸፱ ፤ አቃንቶ ፡ ለሚያነብና ፡ ለሚሰማው ፡ ሰው ፡
አጥንት ፡ የሚያለመልም ፡፡

፻፹ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ **ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡**
ደክሞ ፡ የሠራውን ፡ ገድል ፡ ስሙ ፡፡

፻፹፩ ፤ **የተክለ ፡ ሃይማኖት ፡** ወገን ፡ የሆነ ፡ እየ
ጻፈ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡፡

፻፹፪ እየፈራ ፡ እየተንቀጠቀጠ ፡ ይናገራል ፡፡

፻፹፫ ፤ እየደነገፀ ፡ ይተረጕማል ፡፡

፻፹፬ ፤ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ይመልሳል ፡፡

፻፹፭ ፤ እያከበረ ፡ ያመሰግናል ፡፡

፻፹፮ ፤ ልቡናችሁን ፡ ጸጥ ፡ አድርጋችሁ ፡ ስሙት ፡፡

፻፹፯ ፤ (በአካል ፡ ሦስት ፡ በባሕርይ ፡ በህልውና) ፡
አንድ ፡ **አምላክ ፡** በሚሆን ፡ **በአብ ፡ በወ
ልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡** ስም ፡ ተጀምሮ ፡
የሚነበብ ፡፡

፻፹፰ ፤ ጌትነት ፡፡ መስገድ ፡፡

፻፹፱ ፤ ምስጋና ፡ ገንዘቡ ፡ የሚሆን ፡፡

፻፺ ፤ ያለመለየት ፡፡

፻፺፩ ፤ ያለመለወጥ ፡፡

፻፺፪ ፤ በመለኮት ፡ አንድ ፡ የሚሆኑ ፡፡

፻፺፫ ፤ ለኛ ፡ ለክርስቲያኖች ፡ ሁሉና ፡ ለሀገራችን ፡
ለኢትዮጵያ ፡ ይቅርታው ፡ ቸርነቱ ፡ ይደ
ረግልን ፡፡

፻፺፬ ፤ ለዘላለሙ ፡ በውነት ፡፡

፻፺፭ ፤ በጎ ፡ ነገር ፡ ትሰሙ ፡ ዘንድ ፡ ኑ ፡ ተሰብሰቡ፡፡

፻፺፮ ፤ ኑ ፡ ፈጥናችሁ ፡ ተሰብሰቡ ፡፡

፻፺፯ ፤ የተጸማ ፡ ወደፈሳሽ ፡ ውኃ ፡ ፈጥኖ ፡ እንዲሄድ፡፡

፻፺፰ ፤ ያባታችሁን ፡ ገድል ፡ ሰምታችሁ ፡ ልቡ
ናችሁ ፡ ይረዳ ፡ ዘንድ ፡፡

፻፺፱ ፤ አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡ የሠራውን ፡ ሥራ ፡ ፈጽሜ፡
እናገር ፡ ዘንድ ፡ አፌን ፡ መልቼ ፡ እንድ
ናገር ፡ አድርገኝ ፡፡

፪፻ ፤ በሥልጣኑ ፡ ያደረገውን ፡ ተአምራት ፡
እናገር ፡ ዘንድ ፡፡

፪፻፩ ፤ ፍጹም ፡ ዕውቀትህን ፡ አሳድርብኝ ፡፡

፪፻፪ ፤ ለአገልጋዮችህ ፡ ለምእመናን ፡ እናገር ፡
ዘንድ ፡፡

፪፻፫ ፤ ክቡር ፡ አባታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
መከራውን ፡ እየተቀበለ ፡ የሥራውን ፡
ሥራ ፡ እንድናገር ፡ አድርገኝ ፡፡

፪፻፬ ፤ ለዘለዓለሙ ፡ በዕውነት ፡፡

፩ ፤ በአካል ፡ ሦስት ፡ በባሕርይ ፡ በህልውና ፡
አንድ ፡ በሚሆን ፡ **በእግዚአብሔር ፡** ስም ፡
አምነን ፡ (ባለመለያየት ፡ ሦስት ፡ የሚሆን፡፡)

፪ ፤ ባለመፋለስ ፡ አንድ ፡ የሚሆን ፡፡

፫ ፤ ከመታሰብ ፡ መለኮትነቱ ፡ የማይመረመር ፡፡

፬ ፤ መኩሸ ፡ ከመሆን ፡ በሥልጣን ፡ አንድ ፡
የሚሆን ፡፡

፭ ፤ ኅብረ ፡ መንግሥት ፡ በኢተባርዮ ።
፮ ፤ ወዕሩየ ፡ አካል ፡ ዘበተአደዮ ።
፯ ፤ ዘሎቱ ፡ ለባሕቲቱ ፡ ይደሉ ፡ ስጊድ ፡ ወተ
ጋንዮ ።
፰ ፤ ንጽሕፍ ፡ ገድለ ፡ ጻማሁ ፡ ለአቡነ ፡ ቅዱስ ፡
ብፁዓዊ ።

፱ ፤ ዘውእቱ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ብፁዓዊ ፡ ተክለ ፡
ሃይማኖት ።
፲ ፤ ጸዋሬ ፡ ስመ ፡ ሥላሴ ።

፲፩ ፤ ዘይትነበብ ፡ አመ፳ወ፬ ፡ ለነሐሴ ።

፲፪ ፤ ኃያለ ፡ ጸሎቱ ፡ ያድኅነነ ፡ እምዝልጋሴ ።
፲፫ ፤ ዉያሰስል ፡ ድምሳሴ ፡ እምሀገሪትነ ፡ ኢት
ዮጵያ ።
፲፬ ፤ እምነ ፡ ብሉይ ፡ ብእሲ ፡ ያልብሶ ፡ ሐዲስ ፡
ብእሴ ፡ ኤፌ ፡ ም ፡ ፬ ቍ ፡ ፳፬ ፡
፲፭ ፤ ወበከመ ፡ ኮነ ፡ በዝ ፡ ዓለም ፡ ተሰምዮተ ፡
ወልዱ ፡ ወራሴ ፡

ሮሜ ፡ ም ፡ ፲፫ ፡ ቍ ፡ ፲፮

፲፮ ፤ ከመ ፡ እምኔሁ ፡ ኢይኩን ፡ ነግደ ፡ ወፈላሴ ።

፲፯ ፤ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩ ፤ ንቀድም ፡ በረድኤተ ፡ እግዚአብሔር ፡
መጽሐፈ ፡ ልደቱ ፡ ለአቡነ ፡ ተክለ፡ ሃይ
ማኖት ።
፪ ፤ ወልደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጸጋ ፤ ወልደ ፡
አዳም ፡ በሥጋ ።
ሉቃስ ፡ ም ፡ ፫ ፡ ቍ ፡ ፴፰ ፡
፫ ፤ አዳም ፡ ወለዶ ፡ ለሴት ። ወሴት ፡
ወለዶ ፡ ለሄኖስ ።
፬/ ወሄኖስ ፡ ወለዶ ፡ ለቃይናን ።
፭ ፤ ወቃይናን ፡ ወለዶ ፡ ለመላልኤል ።
፮ ፤ ወመላልኤል ፡ ወለዶ ፡ ለያሬድ ።
፯ ፤ ወያሬድ ፡ ወለዶ ፡ ለሄኖክ ።
፰ ፤ ወሄኖክ ፡ ወለዶ ፡ ለማቱሳላ ።
፱ ፤ ወማቱሳላ ፡ ወለዶ ፡ ለላሜህ ።
፲ ፤ ወላሜህ ፡ ወለዶ ፡ ለኖኅ ።
፲፩ ፤ ትውልድ ፡ ፲ ።
፲፪ ፤ ወኖኅ ፡ ወለዶ ፡ ለሴም ።
፲፫ ፤ ወሴም ፡ ወለዶ ፡ ለአርፋስክድ ።
፲፬ ፤ ወአርፋስክድ ፡ ወለዶ ፡ ለቃይናም ።
፲፭ ፤ ወቃይናም ፡ ወለዶ ፡ ለሳላ ።
፲፮ ፤ ወሳላ ፡ ወለዶ ፡ ለኤቦር ።
፲፯ ፤ ወኤቦር ፡ ወለዶ ፡ ለፋሌቅ ።
፲፰ ፤ ወፋሌቅ ፡ ወለዶ ፡ ለራግው ።

፭ ፤ ባለመፈራረቅ ፡ በግዛት ፡ አንድ ፡ የሚሆን ።
፮ ፤ በመመሳሰል ፡ በአካል ፡ የተካከለ ።
፯ ፤ ለሱ ፡ ብቻ ፡ ስግደት ፡ መገዛት ፡ የሚገባው ።

፰ ፤ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ የሚሆን ተክለ ፡ አብ ፡
ተክለ ፡ ወልድ ፡ ተክለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
የሚባል ፡ አባታችን ፡ ደግሞ ፡ የሠራውን ፡
ሥራ ፡ እንጽፋለን ።
፱ ፤ ይኸውም ፡ ንዑድ ፡ ክቡር ፡ የሚሆን፡ አባ
ታችን ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ።
፲ ፤ በሦስቱ ፡ ስም ፡ ተክለ ፡ አብ ፡ ተክለ ፡ወልድ፡
ተክለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተብሎ ፡ የሚ
ጠራ ።
፲፩ ፤ በነሐሴ ፡ በሀያ ፡ አራት ፡ ቀን ፡ የሚነበብ ፡
ገድሉን ፡ እንጽፋለን ።
፲፪ ፤ የልመናው ፡ ኃይል ፡ ከደዌ ፡ ያድነን ፡ዘንድ።
፲፫ ፤ ከኢትዮጵያ ፡ ሀገራችን ፡ ጥፋትን ፡ ያርቅ
ልን ፡ ዘንድ ፤
፲፬ ፤ ከብሉይ ፡ ሰውነት ፡ ለይቶ ፡ በልጅነት ፡
የታደሰ ፡ ሰውን ፡ ያስመሰለው ፡ ዘንድ ።
፲፭ ፤ በዚህ ፡ ዓለም ፡ የክርስቶስን ፡ ስም ፡ ወራሽ ፡
እንደሆነ ፡ በሚመጣው ፡ ዓለም ፡ በመንግ
ሥተ ፡ ሰማያት ፡ ክብሩን ፡ የሚወርስ ፡ያድ
ርገው ።
፲፮ ፤ ከመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ እንግዳ ፡ መጻተኛ ፡
እንዳይሆን ።
፲፯ ፤ ለዘለዓለሙ ፡ በእውነት ።

ምዕራፍ ፡ ፩ ።

፩ ፤ በእግዚአብሔር ፡ አጋዥነት ፡ ያባታችንን ፡
የተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ የልደቱን ፡ ቊጥር ፡
እንጀምራለን ፡ እንናገራለን ።
፪ ፤ በሥጋ ፡ ያዳም ፡ ልጅ ፡ በልጅነት ፡ የእግ
ዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ የሚሆን ።

፫ ፤ አዳም ፡ ሴትን ፡ ወለደ ።
ሴትም ፡ ሄኖስን ፡ ወለደ ።
፬ ፤ ሄኖስም ፡ ቃይናንን ፡ ወለደ ።
፭ ፤ ቃይናንም ፡ መላልኤልን ፡ ወለደ ።
፮ ፤ መላልኤልም ፡ ያሬድን ፡ ወለደ ።
፯ ፤ ያሬድም ፡ ሄኖክን ፡ ወለደ ።
፰ ፤ ሄኖክም ፡ ማቱሳላን ፡ ወለደ ።
፱ ፤ ማቱሳላም ፡ ላሜህን ፡ ወለደ ።
፲ ፤ ላሜህም ፡ ኖህን ፡ ወለደ ።
፲፩ ፤ ዐሥር ፡ ትውልድ ፡ ይሆናል ።
፲፪ ፤ ኖኅም ፡ ሴምን ፡ ወለደ ።
፲፫ ፤ ሴምም ፡ አርፋስክድን ፡ ወለደ ።
፲፬ ፤ አርፋስክድም ፡ ቃይናምን ፡ ወለደ ።
፲፭ ፤ ቃይናምም ፡ ሳላን ፡ ወለደ ።
፲፮ ፤ ሳላም ፡ ኤቦርን ፡ ወለደ ።
፲፯ ፤ ኤቦርም ፡ ፋሌቅን ፡ ወለደ ።
፲፰ ፤ ፋሌቅም ፡ ራግውን ፡ ወለደ ።

፲፱ ፤ ወራግው ፡ ወለዶ ፡ ለሴሩኅ ።
፳ ፤ ወሴሩኅ ፡ ወለዶ ፡ ለናኮር ።
፳፩ ፤ ወናኮር ፡ ወለዶ ፡ ለታራ ።
፳፪ ፤ ትውልድ ፡ ፳ ።
፳፫ ፤ ወታራ ፡ ወለዶ ፡ ለአብርሃም ።
፳፬ ፤ ወአብርሃም ፡ ወለዶ ፡ ለይስሐቅ ።
፳፭ ፤ ወይስሐቅ ፡ ወለዶ ፡ ለያዕቆብ ።
፳፮ ፤ ወያዕቆብ ፡ ወለዶ ፡ ለሌዊ ፡ ወለ፲ ፡ ወ፩ ፡ አኃዊሁ ።
፳፯ ፤ ዘውእቶሙ ፡ አርእስተ ፡ አበው ።
፳፰ ፤ ወሌዊ ፡ ወለዶ ፡ ለቃዓት ።
፳፱ ፤ ወቃዓት ፤ ወለዶ ፡ ለእንበረም ።
፴ ፤ ወእንበረም ፡ ወለዶሙ ፡ ለሙሴ ፡ መስፍን ።
፴፩ ፤ ወለአሮን ፡ ካህን ።
፴፪ ፤ ወበመዋዕሊሆሙ ፡ ወፅአ ፡ እስራኤል ፡ እምግብጽ ።
፴፫ ፤ ወአሮን ፡ ወለዶ ፡ ለይታምር ።
፴፬ ፤ ወይታምር ፡ ወለዶ ፡ ለጌዴዎን ።
፴፭ ፤ ወጌዴዎን ፡ ወለዶ ፡ ለአልዓዛር ።
፴፮ ፤ ትውልድ ፴ ።
፴፯ ፤ ወአልዓዛር ፡ ወለዶ ፡ ለአበሜሌክ ።
፴፰ ፤ ወአበሜሌክ ፡ ወለዶ ፡ ለናታን ።
፴፱ ፤ ወናታን ፡ ወለዶ ፡ ለአብያታር ።
፵ ፤ ወአብያታር ፡ ወለዶ ፡ ለሳዶቅ ።
፵፩ ፤ ምዕራፍ ፡ ፪ ፡ ወ፲ነ ፡ ጥንተ ፡ ሙላዱ ፡ ለዝንቱ ፡ ቅዱስ ፡ አቡነ ፡ **ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡** ሀገረ ፡ ኢየሩሳሌም ።
፵፪ ፤ እምደወለ ፡ ፍልስጥኤም ።
፵፫ ፤ ዘፈለጣ ፡ ኢያሱ ፡ መስፍን ፡ ከመ ፡ ትኩን ፡ ክፍለ ፡ ለሌዋውያን ።
፵፬ ፤ ወይእቲ ፡ ክፍሉ ፡ ለሳዶቅ ፡ ካህን ፡ ወለደ ፡ አብያታር ።
፵፭ ፤ በመዋዕለ ፡ ሰሎሞን ፡ ንጉሥ ።
፵፮ ፤ ወሳዶቅ ፡ ወለዶ ፡ ለአዛርያስ ።
፵፯ ፤ ዘውእቱ ፡ ፴ ፡ ወ፭ ፡ ትውልድ ፡ እምአዳም ።
፵፰ ፤ አዳም ፡ ወለዶ ፡ ለሴት ። ወሴት ፡ ወለዶ ፡ ለሄኖስ ፡ ወሄኖስ ፡ ወለዶ ፡ ለቃይናን ። ወቃይናን ፡ ወለዶ ፡ ለመላልኤል ። ወመላልኤል ፡ ወለዶ ፡ ለያሬድ ።
ወያሬድ ወለዶ ፡ ለሄኖክ ። ወሄኖክ ፡ወለዶ ፡ ለማቱሳላ ። ወማቱሳላ ፡ ወለዶ ፡ ለላሜህ ። ወላሜህ ፡ ወለዶ ፡ ለኖህ ።
፵፱ ፤ ትውልድ ፡ ፲ ። ወኖኅ ፡ ወለዶ ፡ ለሴም ። ወሴም ፡ ወለዶ ፡ ለአርፋክስድ ።
፶ ፤ ወአርፋክስድ ፡ ወለዶ ፡ ለቃይናም ።
፶፩ ፤ ወቃይናም ፡ ወለዶ ፡ ለሳላ ።
፶፪ ፤ ወሳላ ፡ ወለዶ ፡ ለኤቦር ። ወኤቦር ፡ ወለዶ ፡ ለፋሌቅ ። ወፋሌቅ ፡ ወለዶ ፡ ለራግው ፡ ወለዶ ፡ ለሴሮኅ ። ወሴሮኅ ፡ ወለዶ ፡ ለናኮር ፡ ወናኮር ፡ ወለዶ ፡ ለታራ ። ትውልድ ፡ ፳

፲፱ ፤ ራግውም ፡ ሴሩኅን ፡ ወለደ ።
፳ ፤ ሴሩህም ፡ ናኮርን ፡ ወለደ ።
፳፩ ፤ ናኮርም ፡ ታራን ፡ ወለደ ፡
፳፪ ፤ ሀያ ፡ ትውልድ ፡ ይሆናል ።
፳፫ ፤ ታራም ፡ አብርሃምን ፡ ወለደ ።
፳፬ ፤ አብርሃምም ፡ ይስሐቅን ፡ ወለደ ።
፳፭ ፤ ይስሐቅም ፡ ያዕቆብን ፡ ወለደ ።
፳፮ ፤ ያዕቆብም ፡ ሌዊን ፡ አሥራ ፡ አንዱን ፡ ወንድሞቹንም ፡ ወለደ ።
፳፯ ፤ ያባቶች ፡ መገኛ ፡ የሚሆኑ ።
፳፰ ፤ ሌዊም ፡ ቃዓትን ፡ ወለደ ።
፳፱ ፤ ቃዓትም ፡ እንበረምን ፡ ወለደ ።
፴ ፤ እንበረምም ፡ መስፍኑ ፡ ሙሴን ።
፴፩ ፤ ካህኑ ፡ አሮንን ፡ ወለደ ።
፴፪ ፤ በነሱም ፡ ዘመን ፡ እስራኤል ፡ ከግብጽ ፡ ወጡ ።
፴፫ ፤ አሮንም ፡ ይታምርን ፡ ወለደ ።
፴፬ ፤ ይታምርም ፡ ጌዴዎንን ፡ ወለደ ።
፴፭ ፤ ጌዴዎንም ፡ አልዓዛርን ፡ ወለደ ፡
፴፮ ፤ ሠላሳ ፡ ትውልድ ፡ ይሆናል ።
፴፯ ፤ አልዓዛርም ፡ አቤሜሌክን ፡ ወለደ ።
፴፰ ፤ አቤሜሌክም ፡ ናታንን ፡ ወለደ ።
፴፱ ፤ ናታንም ፡ አብያታርን ፡ ወለደ ።
፵ ፤ አብያታርም ፡ ሳዶቅን ፡ ወለደ ።
፵፩ ፤ የዚህ ፡ ክቡር ፡ አባታችን ፡ **ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡** ጥንተ ፡ ትውልዱ ፡ ኢየሩሳሌም ፡ ነው ።
፵፪ ፤ ከፍልስጥኤም ፡ አውራጃ ።
፵፫ ፤ መስፍኑ ፡ ኢያሱ ፡ ለካህናት ፡ እርስት ፡ ትሁን ፡ ብሎ ፡ የለያት ።
፵፬ ፤ ይችውም ፡ የአብያታር ፡ ልጅ ፡ የካህኑ ፡ የሳዶቅ ፡ ዕፃ ፡ ናት ፡
፵፭ ፤ ሰሎሞን ፡ በነገሠበት ፡ ዘመን ።
፵፮ ፤ ሳዶቅም ፡ አዛርያስን ፡ ወለደ ።
፵፯ ፤ ከአዳም ፡ ጀምሮ ፡ ሠላሳ ፡ አምስት ፡ ትውልድ ፡ ይሆናል ።
፵፰ ፤ አዳምም ፡ ሴትን ፡ ወለደ ። ሴትም ፡ ሄኖስን ። ወለደ ። ሄኖስም ፡ ቃይናን ፡ ወለደ ። ቃይናንም ፡ መላልኤልን ፡ ወለደ ። መላልኤልም ፡ ያሬድን ፡ ወለደ ፡ ያሬድም ፡ ሄኖክን ፡ ወለደ ። ሄኖክም ፡ ማቱሳላን ፡ ወለደ ። ማቱሳላም ፡ ላሜህን ፡ ወለደ ። ላሜህም ፡ ኖህን ፡ ወለደ ።
፵፱ ፤ ዐሥር ፡ ትውልድ ፡ ይሆናል ።
ኖኅም ፡ ሴምን ፡ ወለደ ። ሴምም ፡ አርፋክስድን ፡ ወለደ ።
፶ ፤ አርፋክስድም ፡ ቃይናምን ፡ ወለደ ።
፶፩ ፤ ቃይናምም ፡ ሳላን ፡ ወለደ ።
፶፪ ፤ ሳላም ፡ ኤቦርን ፡ ወለደ ። ኤቦርም ፡ ፋሌቅን ፡ ወለደ ፡ ፋሌቅም ፡ ራግውን ፡ ወለደ ። ራግውም ፡ ሴሮኅን ፡ ወለደ ። ሴሮኅም ፡ ናኮርን ፡ ወለደ ። ናኮርም ፡ ታራን ፡ ወለደ ። ሃያ ፡ ትውልድ ።

፶፫ ፤ ወታራ ፡ ወለዶ ፡ ለአብርሃም ።
፶፬ ፤ ወአብርሃም ፡ ወለዶ ፡ ለይስሐቅ ።
፶፭ ፤ ወይስሐቅ ፡ ወለዶ ፡ ለያዕቆብ ።
፶፮ ፤ ወያዕቆብ ፡ ወለዶ ፡ ለይሁዳ ።
ወይሁዳ ፡ ወለዶ ፡ ለፋሬስ ። ወፋሬስ ፡
ወለዶ ፡ ለኤስሮም ። ወኤስሮም ፡ ወለዶ ፡
ለአራም ። ወአራም ፡ ወለዶ ፡ ለአሚናዳብ ።
፶፯ ፤ ወአሚናዳብ ፡ ወለዶ ፡ ለነአሶን ።
፶፰ ፤ ወነአሶን ፡ ወለዶ ፡ ለሰልሞን ።
ትውልድ ፡ ፴ ።
፶፱ ፤ ወሰልሞን ፡ ወለዶ ፡ ለቦዔዝ ።
፷ ፤ ወቡዔዝ ፡ ወለዶ ፡ ለኢዮቤድ ።
፷፩ ፤ ወኢዮቤድ ፡ ወለዶ ፡ ለዕሤይ ።
፷፪ ፤ ወዕሤይ ፡ ወለዶ ፡ ለዳዊት ፡ ንጉሥ ።
፷፫ ፤ ወዳዊት ፡ ወለዶ ፡ ለሰሎሞን ።
፷፬ ፤ ወሰሎሞን ፡ ወለዶ ፡ ለዕብነ ፡ ሐኪም ።
ትውልድ ፡ ፴ወ፺ቱ ፡ እምአዳም ።

## ምዕራፍ ፡ ፫ ።

፩ ፤ ወአንገሦ ፡ ሰሎሞን ፡ ለወልዱ ፡ ዕብነ ፡
ሐኪም ፡ ወፈነዎ ፡ ብሔረ ፡ ኢትዮጵያ ።
፪ ፤ ከመ ፡ ይንግሥ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ በሐውርቲሃ ።
፫ ፤ ወለወልደ ፡ ሳዶቅሂ ፡ አዛርያስ ፡ ፈነዎ ፡
ምስሌሁ ።
፬ ፤ ከመ ፡ ይኩን ፡ ካህነ ፡ ከመ ፡ አቡሁ ።
፭ ፤ ወወፅኡ ፡ ፪ሆሙ ፡ ኅቡረ ፡ እምኢየሩሳ
ሌም ፡ ምስለ ፡ ብዙኅ ፡ ሕግ ፡ ወሥርዓት ።
፮ ፤ ወጽዮንሂ ፡ ታቦተ ፡ አምላከ ፡ እስራኤል ፡
ወፅአት ፡ ምስሌሆሙ ፡ ብሔረ ፡ ኢትዮጵያ ።

፯ ፤ ወዲበ ፡ ኵሉ ፡ ንዋየ ፡ ወመናብርቲሃ ፡
ሥሉጥ ፡ ውእቱ ፡ አዛርያስ ፡ በከመ ፡ሕጎሙ፡
ለአበዊሁ ፡ ሌዋውያን ።
፰ ፤ ወበጽሑ ፡ ፪ሆሙ ፡ ምድረ ፡ ትግሬ ፡እንተ ፡
ይእቲ ፡ አክሱም ።

፱ ፤ ወነቢሮ ፡ ውስቴታ ፡ ኅዳጠ ፡ መዋዕለ ።
፲ ፤ አውሰበ፡ አዛርያስ ፡ ወለተ ፡ እምክቡራነ ፡
ሀገር ። እለ ፡ ይብልዎሙ ፡ ደቂቀ ፡ መደ
ባይ ፡ ወወለደ ፡ ወልደ ።
፲፩ ፤ ወሰመየ ፡ ስሞ ፡ ሳዶቅሃ ፡ በስመ ፡ አቡሁ ።
፲፪ ፤ ወካልዕ ፡ ስሙ ፡ እግዚእ ፡ መሐር ።
ወሳዶቅ ፡ ወለዶ ፡ ለሌዊ ። ወሌዊ ፡ ወለዶ ፡
ለሕዝበ ፡ ረዓይ ፡ ውእቱ ፡ በግዑ ። ወሕ
ዝበ ፡ ራዕይ ፡ ወለዶ ፡ ለሕዝበ ፡ ዋሂ ። ዘው
እቱ ፡ ነገደ ፡ ሌዊ ። ወሕዝበ ፡ ዋሂ ፡ ወለዶ ፡
ለአኪን ። ትውልድ ፡ ፴ ።
፲፫ ፤ ወነበሩ ፡ እሉ ፡ ካህናት ፡ እንዘ ፡ ይሜህሩ ፡
ሕገ ፡ ኦሪቶሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ሰብአ ፡ ኢት
ዮጵያ ፡ እለ ፡ ይትጋብኡ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ።
፲፬ ፤ በከመ ፡ ሕጎሙ ፡ ለካህናተ ፡ ደብተራ ፤

፶፫ ፤ ታራም ፡ አብርሃምን ፡ ወለደ ።
፶፬ ፤ አብርሃም ፡ ይስሐቅን ፡ ወለደ ።
፶፭ ፤ ይስሐቅም ፡ ያዕቆብን ፡ ወለደ ።
፶፮ ፤ ያዕቆብም ፡ ይሁዳን ፡ ወለደ ።
ይሁዳም ፡ ፋሬስን ፡ ወለደ ። ፋሬስም ፡ ኤስ
ሮምን ፡ ወለደ ። ኤስሮምም ፡ አራምን ፡
ወለደ ፡ አራምም ፡ አሚናዳብን ፡ ወለደ ።
፶፯ ፤ አሚናዳብም ፡ ነአሶንን ፡ ወለደ ።
፶፰ ፤ ነአሶንም ፡ ሰልሞንን ፡ ወለደ ።
ሠላሳ፡ ትውልድ ፡ ይሆናል ።
፶፱ ፤ ሰልሞንም ፡ ቡዔዝን ፡ ወለደ ።
፷ ፤ ቡዔዝም ፡ ኢዮቤድን ፡ ወለደ ።
፷፩ ፤ ኢዮቤድም ፡ ዕሤይን ፡ ወለደ ።
፷፪ ፤ ዕሤይም ፡ ንጉሥ ፡ ዳዊትን ፡ ወለደ ።
፷፫ ፤ ዳዊትም ፡ ሰሎሞንን ፡ ወለደ ።
፷፬ ፤ ሰሎሞንም ፡ ዕብነ ፡ ሐኪምን ፡ ወለደ ።
ይኸውም ፡ ምኒልክ ፡ ነው ። ከአዳም ፡
ሠላሳ ፡ ሰባት ፡ ትውልድ ፡ ይሆናል ።

## ሦስት ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ሰሎሞን ፡ ልጁ ፡ ምኒልክን ፡ አንግሦ፡ ወደ
ኢትዮጵያ ፡ ሰደደው ።
፪ ፤ በመለዋ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነግሦ ፡ ይኖር ፡ዘንድ ።
፫ ፤ የሳዶቅን ፡ ልጅ ፡ አዛርያስንም ፡ ከልጁ ፡
ጋራ ፡ ሹሞ ፡ ሰደደው ።
፬ ፤ እንደ ፡ አባቱ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ አድርጎ ።
፭ ፤ ሁለቱም ፡ አንድነት ፡ ከኢየሩሳሌም ፡
ብዙ ፡ ሕግ ፡ ብዙ ፡ ሥርዓት ፡ ይዘው ፡መጡ።
፮ ፤ የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ ማደሪያዋ ፡ ታቦተ ፡
ጽዮንንም ፡ ከነሱ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ኢትዮ
ጵያ ፡ ይዘዋት ፡ መጡ ።
፯ ፤ በንዋየ ፡ ቅድሳቱ ፡ በመሳሪዋም ፡ ሁሉ ፡
እንደ ፡ አባቶቹ ፡ ሥርዓት ፡ አዛርያስ ፡ያዝ
በት ፡ ነበር ።
፰ ፤ ሁለቱም ፡ አንድነት ፡ የትግሬ ፡ አውራጃ ፡
የምትሆን ፡ አክሱም ፡ ከምትባለው ፡ ቦታ ፡
ገብተው ፡ ተቀመጡ ።
፱ ፤ ጥቂት ፡ ዘመን ፡ ከተቀመጡ ፡ በኋላ ።
፲ ፤ አዛርያስ ፡ ከደጋጎቹ ፡ ወገን ፡ ያንዱን ፡
ልጅ ፡ አግብቶ ፡ የመደባይ ፡ ልጆች ፡ከሚ
ባሉ ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ ወለደ ።
፲፩ ፤ ስሙንም ፡ በአባቱ ፡ ስም ፡ ሳዶቅ ፡ አለው ።
፲፪ ፤ ሁለተኛ ፡ ስሙ ፡ እግዚእ ፡ መሐር ፡ ነው ።
ሳዶቅም ፡ ሌዊን ፡ ወለደ ። ይኸውም ፡
በግዑ ፡ ይባላል ። ሕዝበ ፡ ረዓይም ፡ ሕዝበ ፡
ዋሂን ፡ ወለደ ። ይኸውም ፡ ነገደ ፡ ሌዊ ፡
ይባላል ። ሕዝበ ፡ ዋሂም ፡ አኪንን ፡ ወለደ ።
አርባ ፡ ትውልድ ፡ ይሆናል ።
፲፫ ፤ እሊህም ፡ ካህናት ፡ ሕገ ፡ ኦሪትን ፡ እያስ
ተማሩ ፡ ኖሩ ፡ ወደንጉሡ ፡ ለሚመጡ ፡
ለኢትዮጵያ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ።
፲፬ ፤ በደብተራ ፡ ኦሪት ፡ የተሾሙ ፡ ካህናት ፡
እንደ ፡ ሚያስተምሩ ።

፲፭ ፤ ወእስከ ፡ አሜሃ ፡ ኢተወልደ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
፲፮ ፤ ወበ፲ቱ ፡ ፳፻ወ፳፻ወ፭ ፡ ዓመት ፡ እምፀአተ ፡ እስራኤል ፡ እምግብጽ ፤
፲፯ ፤ እንዘ ፡ ጢባርዮስ ፡ ንጉሠ ፡ ሮሜ ።
፲፰ ፤ ወእንዘ ፡ ሄሮድስ ፡ ንጉሠ ፡ ገሊላ ።
፲፱ ፤ ወእንዘ ፡ ባዜን ፡ ንጉሠ ፡ ኢትዮጵያ ።
፳ ፤ ወአኪን ፡ ካህን ፡ በውስተ ፡ አሜሃ ፡ ተወልደ ፡ ንጉሥነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለዘ ዘክሮቱ ፡ ይደሉ ፡ ሰጊድ ።

፳፩ ፤ ልደተ ፡ ሥጋዊተ ፡ እምቅድስት ፡ ድንግል ፡ በ፪ ፡ ማርያም ።

፳፪ ፤ በቤተ ፡ ልሔም ፡ ዘይሁዳ ።
፳፫ ፤ ንግባዕኬ ፡ ኀበ ፡ ነገርነ ፡ ዘቀዳሚ ።
፳፬ ፤ ወኪን ፡ ካህን ፡ ወለዶ ፡ ለስምዖን ።
፳፭ ፤ ወስምዖን ፡ ወለዶ ፤ ለዕንበረም ።
፳፮ ፤ ዘበመዋዕሊሁ ፡ ወፅአ ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ ከሣቴ ፡ ብርሃን ።
፳፯ ፤ አመ ፡ መንግሥተ ፡ አብርሃ ፡ ወአጽብሃ ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

፩ ፤ ወዝውእቱ ፡ ዜናሁ ፡ ለአባ ፡ ሰላማ ።

፪ ፤ ተብህለ ፡ እምድኅረ ፡ ዓርገ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በ፫፻፶ወ፯ ፡ ዓመት ።
፫ ፤ መጽአ ፡ ፩ ፡ ነጋዲ ፡ እምኢየሩሳሌም ።
፬ ፤ ወምስሌሁ ፡ ፪ቱ ፡ ደቂቅ ።
፭ ፤ ስሙ ፡ ለ፩ ፡ ፍሬምናጦስ ።
፮ ፤ ወለካልኡ ፡ ሲድራኮስ ።
፯ ፤ ወኃደሩ ፡ ውስተ ፡ ቤቱ ፡ ለእንበረም ፡ ካህን ።
፰ ፤ ወበይእቲ ፡ ሌሊት ፡ ሐመ ፡ ውእቱ ፡ ነጋዲ ።
፱ ፤ ወእምድኅረ ፡ ኅዳጥ ፡ መዋዕል ፡ ሞተ ፤
፲ ፤ ወእሙንቱሰ ፡ ደቂቅ ፡ ልሕቁ ፡ በቤቱ ፡ ለእንበረም ።

፲፩ ፤ ወአሐተ ፡ ዕለተ ፡ ይቤሎ ፡ ፍሬምናጦስ ፡ ለእንበረም ።
፲፪ ፤ ኦ ፡ እግዚእየ ፡ አንሰ ፡ አነክር ፡ ግዕዘክሙ ፡ ለሰብአ ፡ ኢትዮጵያ ።
፲፫ ፤ ግዝረት ፡ ወእምነተ ፡ ክርስቶስ ፡ ሀሎ ፡ ኀቤክሙ ።
፲፬ ፤ ጥምቀት ፡ ወቈሪበ ፡ ቍርባን ፡ ኢሀሎ ።

፲፭ ፤ ወይቤሎ ፡ እንበረም ፡ ለፍሬምናጦስ ፤

፲፮ ፤ ግዝረተሰ ፡ አምጽኡ ፡ አበውየ ፡ ሌዋውያን ፡ ወሥርዓተ ።
፲፯ ፤ ወእምነተሰ ፡ አምጽአ ፡ ሕጽዋ ፡ ለህንደኬ ፡ ንግሥት ።
፲፰ ፤ ለጥምቀትሰ ፡ ወቈሪበ ፡ ቍርባን ፡ ኢተፈነወ ፡ ሐዋርያ ፡ ኀቤነ ።

፲፭ ፤ እስከዚያ ፡ ድረስ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አልተወለደም ፡ ነበር ።
፲፮ ፤ እስራኤል ፡ ከግብጽ ፡ በወጡ ፡ በሽህ ፡ ፳፻፭ ፡ ዘመን ።
፲፯ ፤ ጢባርዮስም ፡ በሮም ፡ ነግሦ ፡ ሳለ ።
፲፰ ፤ ሄድሮስም ፡ በገሊላ ፡ ነግሦ ፡ ሳለ ።
፲፱ ፤ ባዜንም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ነግሦ ፡ ሳለ ።
፳ ፤ አኪንም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ። ያን ፡ ጊዜ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ተወለደ ። ለስሙ ፡ ሰጊድ ፡ የሚገባው ።
፳፩ ፤ በድንግልና ፡ በንጽሐ ፡ ሥጋ ፡ በንጽሐ ፡ ነፍስ ፡ ድንግል ፡ ከምትሆን ፡ ከመቤታችን ፡ በሥጋ ፡ ተወለደ ።
፳፪ ፤ የይሁዳ ፡ ዕፃ ፡ በምትሆን ፡ በቤተ ፡ ልሔም ፤
፳፫ ፤ ወደ ፡ ቀደመ ፡ ነገራችን ፡ እንመለስ ።
፳፬ ፤ ካህኑ ፡ ኪንም ፡ ስምዖንን ፡ ወለደ ።
፳፭ ፤ ስምዖንም ፡ እንበረምን ፡ ወለደ ።
፳፮ ፤ ከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ የተባለ ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ በዘመኑ ፡ የወጣ ።
፳፯ ፤ አብርሃና ፡ አጽብሃ ፡ በነገሡበት ፡ ዘመን ።

## ምዕራፍ ፡ ፬ ።

፩ ፤ የአባ ፡ ሰላማንም ፡ ነገር ፡ ወደፊት ፡ የምንናገረው ፡ ነው ።
፪ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ባረገ ፡ በሦስት ፡ መቶ ፡ አምሳ ፡ ሰባት ፡ ዘመን ።
፫ ፤ አንድ ፡ ነጋዴ ፡ ከኢየሩሳሌም ፡ መጣ ።
፬ ፤ ሁለት ፡ ልጆች ፡ ይዞ ።
፭ ፤ አንዱ ፡ ፍሬምናጦስ ፡ ይባላል ።
፮ ፤ ሁለተኛው ፡ ሲድራኮስ ፡ ይባላል ።
፯ ፤ ከእንበረም ፡ ቤት ፡ ገብተው ፡ አደሩ ።
፰ ፤ በዚያች ፡ ቀን ፡ ያ ፡ ነጋዴ ፡ ታሞ ፡ አደረ ።
፱ ፤ ከጥቂት ፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ ሞተ ።
፲ ፤ እሊህም ፡ ልጆች ፡ በእንበረም ፡ ቤት ፡ አደጉ ።

፲፩ ፤ ከዕለታት ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ፍሬምናጦስ ፡ እንበረምን ፡ እንዲህ ፡ አለው ።
፲፪ ፤ ጌታዬ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ሰዎች ፡ ባህል ፡ እኔ ፡ አደንቃለሁ ፡ አለው ።
፲፫ ፤ ትገዘራላችሁ ፡ በክርስቶስም ፡ ታምናላችሁ ።

፲፬ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ጥምቀት ፡ አትጠመቁም ፡ ሥጋ ፡ ወደሙንም ፡ አትቀበሉም ፡ አለው ።
፲፭ ፤ እንበረምም ፡ ፍሬምናጦስን ፡ እንዲህ ፡ አለው ።
፲፮ ፤ ግዝረትን ፡ አባቶቼ ፡ ሌዋውያን ፡ አመጡልን ።
፲፯ ፤ ሃይማኖትንም ፡ የንግሥት ፡ የህንደኬ ፡ ባለሟሏ ፡ አመጣልን ።
፲፰ ፤ ሥጋ ፡ ወደሙ ፡ ለመቀበልና ፡ ለመጠመቅ ፡ ግን ፡ የሚያስተምር ፡ አስተማሪ ፡ አልመጣልንም ።

፲፱ ፡ ወባሕቱ ፡ ነዓ ፡ አንተ ፡ ሑር ፡ ኀበ ፡ ሊቀ ፡
ጳጳሳት ።
፳ ፡ ወንሣእ ፡ መባሕተ ፡ እምኔሁ ።
፳፩ ፡ ከመ ፡ ትኩንነ ፡ ሐዋርያ ።
፳፪ ፡ ወይቤሎ ፡ ፍሬምናጦስ ፡ ለእንበረም ፡ እሆ ፡
ለቃልከ ፡ እግዚእየ ።
፳፫ ፡ ወወሀቦ ፡ እንበረም ፡ ለፍሬምናጦስ ፡ ወርቀ ፡
ወብሩረ ፡ ከመ ፡ ይኩኖ ፡ ስንቀ ፡ ለፍኖት ።
፳፬ ፡ ወሖረ ፡ ፍሬምናጦስ ፡ ኀበ ፡ እስክንድርያ ፡
፳፭ ፡ ወበጽሐ ፡ ኀበ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አባ ፡ አት
ናቴዎስ ።
፳፮ ፡ ወነገሮ ፡ ኵሎ ፡ ግእዘ ፡ ብሔሩ ።
፳፯ ፡ ወሰሚዖ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳት ፡ አትናቴዎስ ፡
ተፈሥሐ ፡ ጥቀ ።
፳፰ ፡ ወሤሞ ፡ ሎቱ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ጳጳሰ ፡ በኵሉ ፡
ብሔረ ፡ ኢትዮጵያ ።
፳፱ ፡ ወሰመዮ ፡ ስሞ ፡ ሰላማ ።
፴ ፡ ዘበትርጓሜሁ ፡ ሰላማዊ ፡ ማእከለ ፡ **እግዚ
አብሔር** ፡ ወሰብእ ፡ ብሂል ።
፴፩ ፡ ወአስተፋነውዎ ፡ በሰላም ።

## ምዕራፍ ፡ ፰ ።

፩ ፡ ወእምዝ ፡ መጽአ ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ ብሔረ ፡
አግዓዚት ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡ ሀገረ ፡ ኢት
ዮጵያ ፤
፪ ፡ በ፫፻፴ወ፭ ፡ ዓመት ፡ እምዕርገተ ፡ እግእ
ዚእነ ፡ **ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ** ።
፫ ፡ በመዋዕሊሆሙ ፡ ለአብርሃ ፡ ወአጽብሐ ፡
ነገሥት ።
፬ ፡ ወበጽሐ ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ ኀበ ፡ እንበረም ፡
ቅድመ ።
፭ ፡ ወአጥመቆ ፡ ወሤሞ ፡ ሢመተ ፡ ዲቁና ።
፮ ፡ ወበሳኒታ ፡ ረሰዮ ፡ ቀሲሰ ።
፯ ፡ ወወለጠ ፡ ስሞ ፡ ወሰመዮ ፡ ሕዝበ ፡ ቀድስ ።
፰ ፡ ወይቤሎ ፡ አጥምቅ ፡ ኵሎ ፡ ሰብአ ።
፱ ፡ ወእምታሕቴየ ፡ ይኩን ፡ ሥልጣንከ ።
፲ ፡ ወይበሉከ ፡ ኤጲስቆጶስ ።
፲፩ ፡ ወነሢአ ፡ እንበረም ፡ ሥልጣነ ፡ መባሕት ፡
እምኔሁ ።
፲፪ ፡ አጥመቀ ፡ ኵሎ ፡ ሰብአ ።
፲፫ ፡ ወመሐሮሙ ፡ ሃይማኖተ ፡ **ክርስቶስ** ።
፲፬ ፡ ወአሜሃ ፡ ተጠምቁ ፡ ሰብአ ፡ ኖባ ።
፲፭ ፡ ወሰብአ ፡ ናግራን ፡ ወትግሬ ።
፲፮ ፡ ሰብአ ፡ አንጐት ፡ ወአምሐራ ።
፲፯ ፡ ሰብአ ፡ ጿቷ ፡ ወዘባጉድር ።
፲፰ ፡ ወኮኑ ፡ ኵሎሙ ፡ ዓቢያተ ፡ ክርስቲያና
ውያነ ፡ በእደዊሁ ፡ ለሕዝበ ፡ ቀድስ ።
፲፱ ፡ በመዋዕሊሆሙ ፡ ለነገሥት ፡ ኄራን ፡ አብ
ርሃ ፡ ወአጽብሐ ።
፳ ፡ ወሕዝበ ፡ ቀድስ ፡ ወለዶሙ ፡ ለንግሥት ፡
ሕዝባ ፡ ወለያሬድ ፡ ካህን ።

፲፱ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አንተ ፡ ከሊቀ ፡ ጳጳሱ ፡ ሂደህ ።
፳ ፡ ከሱ ፡ ሥልጣን ፡ ተቀብለህ ፡ ና ።
፳፩ ፡ መምር ፡ ትሆነን ፡ ዘንድ ።
፳፪ ፡ ጌታዬ ፡ እሺ ፡ እንዳዘዝከኝ ፡ አደርጋለሁ ፡
አለው ።
፳፫ ፡ እንበረምም ፡ ለፍሬምናጦስ ፡ ስንቅ ፡ ይሁ
ንህ ፡ ብሎ ፡ ብዙ ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ሰጠው ።
፳፬ ፡ ፍሬምናጦስም ፡ ወደ ፡ እስክንርያ ፡ ሂዶ ፤
፳፭ ፡ ከሊቀ ፡ ጳጳሱ ፡ ከአባ ፡ አትናቴዎስ ፡ደረሰ ።
፳፮ ፡ የኢትዮጵያን ፡ ባሕል ፡ ሁሉ ፡ ነገረው ።
፳፯ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳቱም ፡ ሰምቶ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡
አለው ።
፳፰ ፡ በመላዋ ፡ በኢትዮጵያ ፡ አንተው ፡ ጳጳስ ፡
ሁን ፡ ብሎ ፡ ሾመው ።
፳፱ ፡ ስሙንም ፡ ሰላማ ፡ አለው ።
፴ ፡ ይኸውም ፡ ሰውን ፡ **ከእግዚአብሔር** ፡ ጋር ፡
የሚያስታርቅ ፡ ማለት ፡ ነው ።
፴፩ ፡ በፍቅር ፡ ተቀብለው ፡ በፍቅር ፡ ሸኙት ።

## ምዕራፍ ፡ ፰ ።

፩ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ ተመልሶ ፡
ወደኢትዮጵያ ፡ መጣ ።
፪ ፡ ጌታችን ፡ **ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ** ፡ ባረገ ፡ በ፫፻
፴፭ ፡ ዘመን ።
፫ ፡ አብርሃና ፡ አጽብሃ ፡ በነገሡበት ፡ ዘመን ።
፬ ፡ አባ ፡ ሰላማም ፡ አስቀድሞ ፡ ከእንበረም ፡
ዘንድ ፡ ደረሰ ።
፭ ፡ አጥምቆ ፡ ዲቁና ፡ ሾመው ።
፮ ፡ በነጋውም ፡ ቅስና ፡ ሾመው ።
፯ ፡ ስሙንም ፡ ለውጦ ፡ ሕዝበ ፡ ቀድስ ፡ አለው ።
፰ ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ አጥምቅ ፡ አለው ።
፱ ፡ ሹመትህም ፡ ከኔ ፡ በታች ፡ ይሁን ፡ አለው ፤
፲ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ተባል ፡ አለው ።
፲፩ ፡ እንበረምም ፡ የሥልጣን ፡ ሹመት ፡ ከሱ ፡
ተሾሞ ።
፲፪ ፡ ሰውን ፡ ሁሉ ፡ አጠመቀ ።
፲፫ ፡ ወንጌልን ፡ አስተማረ ።
፲፬ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የኖባ ፡ ሰዎች ፡ አምነው ፡
ተጠመቁ ።
፲፭ ፡ የትግሬንና ፡ የናግራንንም ፡ ሰዎች ።
፲፮ ፡ የአምሐራና ፡ የአንጎት ፡ ሰዎች ።
፲፯ ፡ የዛባጉድርና ፡ የቋታም ፡ ሰዎች ።
፲፰ ፡ በሕዝበ ፡ ቀድስ ፡ ቃል ፡ አምነው ፡ ፍጹ
ማን ፡ ክርስቲያኖች ፡ ሆኑ ።
፲፱ ፡ ደጋጎቹ ፡ ነገሥታት ፡ አብርሃና ፡ አጽብሐ ፡
በነገሡበት ፡ ዘመን ።
፳ ፡ ሕዝበ፡ ቀድስም፡ ካህኑ ፡ ያሬድንና፡ ንጉሥት ፡
ሕዝባን ፡ ወለደ ።

፳፩ ፤ ንግሥት ፡ ሕዝባ ፡ ወለደቶ ፡ ለሕዝበ፡ባርክ።
፳፪ ፤ ዘውእቱ ፡ ልብ ፡ ደኃሪ ።
፳፫ ፤ እምንጉሥ ፡ ግርማ ፡ አስፈሪ ።
፳፬ ፤ ወውእቱ ፡ ሕዝበ ፡ ባርክ ፡ መጽአ ፡ እም
ትግሬ ፡ ነበረ ፡ ብሔረ ፡ ዳውንት ፡ እንተ ፡
ትሰመይ ፡ ባሕር ፡ ቀጋ ።
፳፭ ፤ ወነሥአ ፡ ብእሲተ ፡ እምህየ ፡ ወወለደ ፡
ተክለ ፡ ቀዓት ።
፳፮ ፤ ወተክለ ፡ ቀዓት ፡ ነሥአ ፡ ብእሲተ ፡ እም
እምሐራ ፡ እንተ ፡ ትሰመይ ፡ መቅደላ ፡
ወወለደ ፡ ፯ተ ፡ ደቂቀ ።
፳፯ ፤ ወልህቁ ፡ ውስቴታ ።
፳፰ ፤ ወእስከ ፡ ይእዜ ፡ ርስቶሙ ፡ ይእቲ ።
፳፱ ፤ ወይትበሐሉ ፡ ፯ቱ ፡ አብያተ ፡ ዝቋናት ።
፴ ፤ ካህናተ ፡ ደብተራ ፡ እሙንቱ ፡ ዘሀገረ ፡
ጽዮን ።
፴፩ ፤ ወኦሐዱ ፡ እምኔሆሙ ፡ ዘስሙ ፡ አጽቀ ፡
ሌዊ ።
፴፪ ፤ ዘአጥመቆሙ ፡ ለሰብአ ፡ ወለቃ ።
፴፫ ፤ ወለሰብአ ፡ አምሐራ ።
፴፬ ፤ ለሰብአ ፡ መርሐቤቴ ፡ ወለመንዝ ።
፴፭ ፤ ወውእቱ ፡ ዓጽቀ ፡ ሌዊ ፡ ነሥአ ፡ ብእሲተ ፡
እምሀርበ ፡ ግሼ ፡ ወወለዶ ፡ ለኀርበ ፡ ጐሽ ።
፴፮ ፤ ወኀርበ ፡ ጐሽ ፡ ወለዶ ፡ ለይግናህ ፡ መስ
ቀል ።
፴፯ ፤ ወይግናህ መስቀል ፡ ወለዶ ፤ ለይቅናዕ
ዳዊት ።
፴፰ ፤ ወይቅናዕ ፡ ዳዊት ፡ ወለዶ ፡ ለዘልዑል ።
፴፱ ፤ ወዘልዑል ፡ ወለዶ ፡ ለሚናስ ፡ ትው
ልድ ፡ ፶ ።
፵ ፤ ወሚናስ ፡ ወለዶ ፡ ለአበይድላ ።
፵፩ ፡ ዘበትርጓሜሁ ፡ ይሑር ፤ ኪመ ፡ ይኩን ፡ አበ
ለብሔረ ፡ ሸዋ ፡ ብሂል ።
፵፪ ፤ እስመ ፡ መንፈስ ፡ ትንቢት ፡ ይነብብ ፡
ውስተ ፡ አፉሆሙ ፡ ለሰብአ ፡ አምሐራ ።
፵፫ ፤ ወዘተናገሩ ፡ ነገር ፡ ይከውን ፡ በጊዜሁ ።
፵፬ ፤ ወለአበድላ ፡ ፈነዎ ፡ ድንግዘን ፡ ንጉሥ
ብሔረ ፡ ሸዋ ።
፵፭ ፤ ምስለ ፡ ፻ወ፶ ፡ ክቡራን ፡ ካህናት ፡ ሌዋው
ያን ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ በመናብርት ።
፵፮ ፤ ከመ ፡ ያጥምቁ ፡ ኵሎ ፡ ሰብአ ፡ እለ ፡ ይነ
ብሩ ፡ ውስቴታ ።
፵፯ ፤ ወሊቆሙሰ ፡ አበይድላ ፡ ውእቱ ።
፵፰ ፤ ወበጺሐሙ ፡ ሸዋ ፡ ነበረ ፡ አበይድላ ፡
ብሔረ ፡ ጽላልሽ ፡
፵፱ ፤ ወአጥመቀ ፡ ብዙኃነ ፡ ሰብአ ፡ በውስቴታ ።

፳፩ ፤ ንግሥት ፡ ሕዝባም ፡ ሕዝበ ፡ ባርክን
ወለደች ።
፳፪ ፤ ይኸውም ፡ ልብ ፡ ደኃሪ ፡ ይባላል ።
፳፫ ፤ ከንጉሥ ፡ ግርማ ፡ አስፈሪ ፡ ወለደች ።
፳፬ ፤ ሕዝበ ፡ ባርክም ፡ ከትግሬ ፡ መጥቶ ፡ ባሕር
ቃጋ ፡ ከምትባል ፡ አገር ፡ ዳውንት ፡ ገብቶ ፡
ተቀመጠ ።
፳፭ ፤ ከዚያ ፡ አንድ ፡ ሴት ፡ አግብቶ ፡ ተክለ ፡
ቀዓትን ፡ ወለደ ።
፳፮ ፤ ተክለ ፡ ቀዓትም ፡ መቅደላ ፡ ከምትባል፡
ከሳይንት ፡ አውራጃ ፡ አጠገብ ፡ አንዲት ፡
ሴት ፡ አግብቶ ፡ ፯ ፡ ልጆች ፡ ወለደ ።
፳፯ ፡ በውስጧ ፡ አደጉ ።
፳፰ ፤ እስከዛሬ ፡ ድረስ ፡ እርስታቸው ፡ ሆና ፡
ትኖራለች ።
፳፱ ፤ ሰባቱ ፡ አብያተ ፡ ዝቋናት ፡ ይባላሉ ።
፴ ፤ እሊህም ፡ በአኵሱም ፡ ተሠርተው ፡ ታቦተ፡
ጽዮን ፡ የሚያገለግሉ ፡ ናቸው ።
፴፩ ፤ ከነሱም ፡ አንዱ ፡ አጽቀ ፡ ሌዊ ፡ ይባላል።
፴፪ ፤ የወለቃን ፡ ሰዎች ።
፴፫ ፤ የአምሐራን ሰዎች ።
፴፬ ፤ የመንዝንና ፡ የመርሐቤቴን ፡ ሰዎች ፡ አስ
ተምሮ ያጠመቀ ፡ ነው ።
፴፭ ፤ ይኸውም ፡ ዓጽቀ ፡ ሌዊ ፡ ኀርበ ፡ ግሺ ፡
ከምትባል ፡ ሀገር ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ አግ
ብቶ ፡ ኀርበ ፡ ጐሽን ፡ ወለደ ።
፴፮ ፤ ኀርበ ፡ ጐሽም ፡ ይግናህ ፡ መስቀልን ።
ወለደ ።
፴፯ ፤ ይግናህ ፡ መስቀልም ፡ ይቅናዕ ፡ ዳዊትን ፡
ወለደ ።
፴፰ ፤ ይቅናዕ ፡ ዳዊትም ፡ ዘልዑልን ፡ ወለደ ።
፴፱ ፤ ዘልዑልም ፡ ሚናስን ፡ ወለደ ፡ ሃምሳ ፡
ትውልድ ፡ ይሆናል ።
፵ ፤ ሚናስም ፡ አበይድላን ፡ ወለደ ።
፵፩ ፤ አበይድላን፡ ማለትም ፡ የሸዋን ፡ አውራጃ ፡
ያስተምር ፡ ዘንድ ፡ ይሂድ ፡ ማለት ፡ ነው ።
፵፪ ፤ የአምሐራ ፡ ሰዎች ፡ ሀብተ ፡ ትንቢት ፡
አድሮባቸው ይናገሩ ፡ ነበርና ።
፵፫ ፤ የተናገሩትም ነገር ፡ ፈጥኖ ፡ ይደረግ ፡
ነበር ።
፵፬ ፤ አበይድላንም ፡ ንጉሡ፡ ድንግዘን ፡ ወደ
ሸዋ ፡ ሹሞ ፡ ሰደደው ።
፵፭ ፤ ወምበር፡ ተሹመው ፡ ከከበሩ ፡ መቶ ፡
ሃምሳ ፡ ካህናት ፡ ጋራ ።
፵፮ ፤ በሸዋ ፡ የተገኘውን ፡ ሁሉ ፡ ያስተምሩ
ዘንድ ።
፵፯ ፤ ለነዚህም ፡ አለቃቸው ፡ አበይድላ ፡ ነው ።
፵፰ ፤ ሸዋም ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ አበይድላ ፡ ጽላልሽ ፡
ከምትባል ፡ ቦታ ፡ ገብቶ ፡ ተቀመጠ ።
፵፱ ፤ በውስጧ ፡ ያገኘውን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እያ
ስተማረ ፡ አጠመቀ ።

፶ ፤ በበ፲፻ ፡ ወበበ፳፻ ፡ በአሐቲ ፡ ዕለት ።

፶፩ ፤ ወተሐንጸ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ለምድረ ሸዋ ፡ በመዋዕሊሆሙ ፡ ለእሙንቱ ፡ ካህናት ።

፶፪ ፤ እስመ ፡ ታቦትሂ ፡ ወንዋየ ፡ ቅድሳት ፡ ወኵሉ ፡ መጻሕፍተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እስመ ፡ መጽኡ ፡ ምስለ ፡ ካህናት ፡ በትእዛዘ ፡ ንጉሥ ።

፶፫ ፤ ወውእቱ ፡ አበይድላ ፡ ሐረየ ፡ ምድረ ፡ እምነ ፡ ጽላልሽ ፡ ወነበረ ፡ ውስቴታ ።

፶፬ ፤ ወነሥኦ ፡ ብእሲተ ፡ እምክቡራነ ፡ ሀገር ።

፶፭ ፤ ወለዶ ፡ ለሐርበሽ ።

፶፮ ፤ ዘውእቱ ፡ ሕይወት ፡ ብነ ፡ በጽዮን ።

፶፯ ፤ ወሕይወት ፡ ብነ ፡ በጽዮን ፡ ወለዶ ፡ ለበኵረ ፡ ጽዮን ፤

፶፰ ፤ ዘውእቱ ፡ ኀበነ ፡ እግዚእ ።

፶፱ ፤ ወበኵረ ፡ ጽዮን ፡ ወለዶ ፡ ለሕዝበ ፡ ቀድስ ።

፷ ፤ ዘውእቱ ፡ ነገደ ፡ እግዚእ ።

፷፩ ፤ ወሕዝበ ፡ ቀድስ ፡ ወለዶ ፡ ለብርሃነ ፡ መስቀል ፡ ዘውእቱ ፡ ዓቃቢነ ፡ እግዚእ ።

፷፪ ፤ ወበውእቱ ፡ መዋዕል ፡ እመ ፡ መንግሥተ ፡ ድልንዓድ ። ፈለሰት ፡ መንግሥት ፡ እምእሥኤል ፡ ኀበ ፡ ነገደ ፡ ሔጻጻ ፡ ዘውእቱ ፡ ዛጔ ።

## ምዕራፍ ፡ ፯ ።

፩ ፤ ወዝውእቱ ፡ ዜና ፡ ልደቶሙ ፡ ለነገሥተ ኢትዮጵያ ።

፪ ፤ እብነ ፡ ሐኪም ፡ ወለዶ ፡ ለተማይ ።

፫ ፤ ወተማይ ፡ ወለዶ ፡ ለዘግዱር ።

፬ ፤ ወዝግዱር ፡ ወለዶ ፡ ለአኩስማይ ።

፭ ፤ ወአኩሱማይ ፡ ወለዶ ፡ ለአውሳብዮስ ። ትውልድ ፡ ፵ ።

፮ ፤ ወአውሳብዮስ ፡ ወለዶ ፡ ለተሐዋስያ ።

፯ ፤ ወተሐዋስያ ፡ ወለዶ ፡ ለአብራልዩስ ።

፰ ፤ ወአብራልዩስ ፡ ወለዶ ፡ ለወረደ ፡ ፀሐይ ።

፱ ፤ ወወረደ ፡ ፀሐይ ፡ ወለዶ ፡ ለሕንደር ።

፲ ፤ ወሕንደር ፡ ወለዶ ፡ ለወረደ ፡ ነጋሽ ።

፲፩ ፤ ወወረደ ፡ ነጋሽ ፡ ወለዶ ለአውስያ ።

፲፪ ፤ ወአውስያ ፡ ወለዶ ፡ ለኤልሳልዮን ።

፲፫ ፤ ወኤልሳልዮን ፡ ወለዶ ፡ ለቆማ ፡ ጽዮን ፤

፲፬ ፤ ወቆማ ፡ ጽዮን ወለዶ ለባስልዮስ ።

፲፭ ፤ ወባስልዮስ ፡ ወለዶ ፡ ለአውጥጥ ። ትውልድ ፡ ፶ ።

፲፮ ፤ ወአውጥጥ ፡ ወለዶ ፡ ለዘዋሪ ፡ ንብረት ።

፲፯ ፤ ወዘዋሪ ፡ ንብረት ፡ ወለዶ ፡ ለሰይፋይ ።

፲፰ ፤ ወሰይፋይ ፡ ወለዶ ፡ ለረምሐይ ።

፲፱ ፤ ወረምሖይ ፡ ወለዶ ፡ ለሐንዲ ።

፶ ፤ ባንዲት ፡ ቀን ፡ አንድ ፡ አንድ ፡ እልፍ ። ሁለት ፡ ሁለት ፡ እልፍም ።

፶፩ ፤ በሊህም ፡ በካህናት ፡ ዘመን ፡ በሸዋ ፡ አውራጃ ፡ ብዙ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተሠሩ ።

፶፪ ፤ ጽላትም ፡ ንዋየ ፡ ቅድሳትም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚነበቡ ፡ መጻሕፍትም ፡ በንጉሡ ፡ ትእዛዝ ፡ ከሳይንት ፡ ከካህናቱ ፡ ጋራ ፡ መጥተው ፡ ነበርና ።

፶፫ ፤ አበይድላም ፡ ከጽላልሽ ፡ አውራጃ ፡ ዞረሬ፡ ከምትባል ፡ ቦታ ፡ መርጦ ፡ ገብቶ ፡ ተቀመጠ ።

፶፬ ፤ ከዚያም ፡ ከደጋጎቹ ፡ ወገን ፡ አንዲት ፡ ሴት፡ አግብቶ ።

፶፭ ፤ ሐበርሽን ፡ ወለደ ።

፶፮ ፤ ይኸውም ፡ ሕይወት ፡ ብነ ፡ በጽዮን ፡ ነው።

፶፯ ፤ ሕይወት ፡ ብነ ፡ በጽዮንም ፡ በኵረ ፡ ጽዮንን ፡ ወለደ ፤

፶፰ ፤ ይኸውም ፡ ኀበነ ፡ እግዚእ ፡ ነው ።

፶፱ ፤ በኵረ ፡ ጽዮንም ፡ ሕዝበ ፡ ቀድስን ፡ ወለደ ።

፷ ፤ ይኸውም ፡ ነገደ ፡ እግዚእ ፡ ነው ።

፷፩ ፤ ሕዝበ ፡ ቀድስም ፡ ዓቃቢነ ፡ እግዚእ ፡ የሚባል ፡ ብርሃን ፡ መስቀልን ፡ ወለደ ።

፷፪ ፤ በዚያም ወራት በድልነአድ ፡ መንግሥት ፡ ጊዜ ፡ መንግሥት ፡ ከእሥኤል ፡ ተለይታ ፡ ወደዛጔ ፡ ወገን ፡ ሄደች ።

## ሰባተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ የትውልዳቸው ፡ ቍጥር ፡ ይህ ፡ ነው ።

፪ ፤ እብነ ፡ ሐኪምም ፡ ተማይን ፡ ወለደ ።

፫ ፤ ተማይ ፡ ዘግዱርን ፡ ወለደ ።

፬ ፤ ዘግዱርም ፡ አክሱማይን ፡ ወለደ ።

፭ ፤ አክሱማይም ፡ አውሳብዮስን ፡ ወለደ ። አርባ ፡ ትውልድ ፡ ይሆናል ።

፮ ፤ አውሳብዮስም ፡ ተሐዋስያንን ፡ ወለደ ።

፯ ፤ ተሐዋስያም ፡ አብራልዩስን ፡ ወለደ ።

፰ ፤ አብራልዩስም ፡ ወረደ ፡ ፀሐይን ፡ ወለደ

፱ ፤ ወረደ ፡ ፀሐይም ፡ ሕንደርን ፡ ወለደ ።

፲ ፤ ሕንደርም ፡ ወረደ ፡ ነጋሽን ፡ ወለደ ።

፲፩ ፤ ወረደ ፡ ነጋሽም ፡ አውስያን ፡ ወለደ ።

፲፪ ፤ አውስያም ፡ ኤልሳልዮንን ፡ ወለደ ።

፲፫ ፤ ኤልሳልዮንም ፡ ቆማ ፡ ጽዮንን ፡ ወለደ ።

፲፬ ፤ ቆማ ፡ ጽዮንን ፡ ባስልዮስን ፡ ወለደ ።

፲፭ ፤ ባስልዮስም ፡ አውጥጥን ፡ ወለደ ። አምሳ ፡ ትውልድ ፡ ይሆናል ።

፲፮ ፤ አውጥጥም ፡ ዘዋሪ ፡ ንብረትን ፡ ወለደ ።

፲፯ ፤ ዘዋሪ ፡ ንብረትም ፡ ሰይፋይን ፡ ወለደ ።

፲፰ ፤ ሰይፋይም ፡ ረምሐይን ፡ ወለደ ።

፲፱ ፤ ረምሐይም ፡ ሐንዲን ፡ ወለደ ።

፳ ፡ ወሐንዲ ፡ ወለዶ ፡ ለሶፌልያ ፡፡
፳፩ ፡ ወሶፌሊያ ፡ ወለዶ ፡ ለአግልኡል ፡፡
፳፪ ፡ ወአግልኡል ፡ ወለዶ ፡ ለበዋውል ፡፡
፳፫ ፡ ወበዋውል ፡ ወለዶ ፡ ለበወሪስ ፡፡
፳፬ ፡ ወበወሪስ ፡ ወለዶ ፡ ለመሐሲ ፡፡
፳፭ ፡ ወመሐሲ ፡ ወለዶ ፡ ለናልኪ ፡፡
ትውልድ ፡ ፳ ፡፡

፳፮ ፡ ወናልኪ ፡ ወለዶ ፡ ለባዚን ፡፡
፳፯ ፡ ዘበመዋዕሊሁ ፡ ተወልደ ፡ እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሎቱ ፡ ስብሐት ፡፡
፳፰ ፡ በ፰ ፡ ዓመተ ፡ መንግሥቱ ፡ ለዝኩ ፡ ንጉሥ ፡፡
፳፱ ፡ ወባዚን ፡ ወለዶ ፡ ለጽንፈ አርድ ፡
ወጽንፈ ፡ አርድ ፡ ወለዶ ፡ ለባሕር ፡ አሰግድ ፡፡

፴ ፡ ወባሕር ፡ አሰግድ ፡ ወለዶ ፡ ለግርማሶር ፡፡
፴፩ ፡ ወግርማሶር ፡ ወለዶ ፡ ለግርማሰፈር ፡፡
፴፪ ፡ ወግርማሰፈር ፡ ወለዶ ፡ ለሠርጓይ ፡፡
፴፫ ፡ ወሠርጓይ ፡ ወለዶ ፡ ለዘርአይ ፡፡
፴፬ ፡ ወዘርዓይ ፡ ወለዶ ፡ ለሰብአ ፡ አሰግድ ፡፡
፴፭ ፡ ወሰብአ ፡ አሰግድ ፡ ወለዶ ፡ ለጽዮን ፡ ግዛ፡፡
፴፮ ፡ ወጽዮን ፡ ግዛ ፡ ወለዶ ፡ ለአግዱር ፡፡
፴፯ ፡ ወአግዱር ወለዶ ፡ ለሰይፈ ፡ አርእድ ፡፡
፩ ፡ ትውልድ ፡ ፶ ፡፡
፪ ፡ ወሰይፈ ፡ አርእድ ፡ ወለዶሙ ፡ ለአብርሃ ፡ ወአጽብሐ ፡ ዘበመዋዕሊሆሙ ፡ መጽአ ፡ ክርስትና ፡፡
፫ ፡ እንዘ ሀለዉ ፡ በአክሱም ፡፡
፬ ፡ ዘሥምጽአስ ፡ ስመ ፡ ክርስትና ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ ውእቱ ፡፡
፭ ፡ ወዜናሁስ ፡ ነገርነ ፡ ቅድመ ፡፡

፮ ፡ ወሕዝበ ፡ ኢትዮጵያስ ፡ እስከ ፡ አሚሃ ፡ ቦ ፡ እለ ፡ ሀለው ፡ በሕገ ፡ ኦሪት ፡፡
፯ ፡ ወቦ ፡ እለ ፡ ነበሩ ፡ እንዘ ፡ ያመልኩ ፡ በአርዌ ፡፡
፰ ፡ ወእምዝ ፡ መሐሮሙ ፡ ውእቱ ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ ዜናሁ ፡ ለእግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡፡
፱ ፡ ወገብረ ተአምራተ ፡ ወመንክራተ ፡ በቅድሜሆሙ ፡፡
፲ ፡ ወእሙንቱኒ ፡ አምኑ ፡ ጥምቀተ ፡ ክርስትና፤
፲፩ ፡ ወእምነትሙስ ፡ ኮነ ፡ እምዕርገተ ፡እግዚእነ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በ፫፻፴ ፡ ወ፰ ፡ ዓመት፡፡
፲፪ ፡ ወሐነጽዋ ፡ ለአክሱም ፡ አብርሃ ፡ ወአጽብሃ ፡
አብርሃ ፡ ወለዶ ፡ ለአስፍሕ ፡ ወአስፍሕ ፡ ወለዶ ፡ ለአርፍድ ፡፡ ወአርፍድ ፡ ወለዶ ፡ ለአምሴ ፡፡ ወአምሴ ፡ ወለዶ ፡ ለአልአዳባ ፡፡
ወአልአዳባ ፡ ወለዶ ፡ ለአልአሜዳ ፡፡

፳ ፡ ሐንዲም ፡ ሶፌልያን ፡ ወለደ ፡፡
፳፩ ፡ ሶፌሊያም ፡ አግሉውልን ፡ ወለደ ፡፡
፳፪ ፡ አግልውልም ፡ በዋውልን ፡ ወለደ ፡፡
፳፫ ፡ በዋውልም ፡ በወሪስን ፡ ወለደ ፡፡
፳፬ ፡ በወሪስም ፡ መሐሲን ፡ ወለደ ፡፡
፳፭ ፡ መሐሲም ፡ ናልኪን ፡ ወለደ ፡፡
ስልሳ ፡ ትውልድ ፡ ይሆናል ፡፡

፳፮ ፡ ናልኪም ፡ ባዚንን ፡ ወለደ ፡፡
፳፯ ፡ ክብር ምስጋና ፡ ይግባውና ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ፡ በዘመኑ ፡ የተወለደ ፡፡
፳፰ ፡ ባዚን ፡ በነገሠ ፡ በስምንት ፡ ዘመን ፡፡
፳፱ ፡ ባዚንም ፡ ጽንፈ ፡ አርድን ፡ ወለደ ፡፡
ጽንፈ ፡ አርድም ፡ ባሕር ፡ አሰግድን ፡ ወለደ ፡፡

፴ ፡ ባሕር ፡ አሰግድም ፡ ግርማሶርን ፡ ወለደ ፡፡
፴፩ ፡ ግርማሶርም ፡ ግርማ ፡ ሰፈርን ፡ ወለደ ፡፡
፴፪ ፡ ግርማ ፡ ሰፈርም ፡ ሠርጓይን ፡ ወለደ ፡፡
፴፫ ፡ ሠርጓይም ፡ ዘርዓይን ፡ ወለደ ፡፡
፴፬ ፡ ዘርዓይም ፡ ሰብአ ፡ አሰግድን ፡ ወለደ ፡፡
፴፭ ፡ ሰብአ ፡ አሰግድም ፡ ጽዮን ፡ ግዛን ፡ ወለደ፡፡
፴፮ ፡ ጽዮንግዛም ፡ አግዱርን ፡ ወለደ ፡፡
፴፯ ፡ አግዱርም ፡ ሰይፈ ፡፡ አርዕድን ፡ ወለደ ፡፡
፩ ፡ ሃምሳ ፡ ትውልድ ፡ ይሆናል ፡፡
፪ ፡ ሰይፈ ፡ አርዕድም ፡ በዘመናቸው ፡ የክርስትና ፡ ሥራ ፡ የተሠራ ፡ አጽብሃና ፡ አብርሃን ፡ ወለደ ፡፡
፫ ፡ በአክሱም ፡ ሳሉ ፡፡
፬ ፡ የክርስትናን ፡ ሥራ ፡ ያስተማረ ፡ ግን ፡ አባ፡ ሰላማ ፡ ነው ፡፡
፭ ፡ የሱንም ፡ ታሪክ ፡ አስቀድመን ፡ ተናግረናል ፡፡
፮ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ በኦሪት ፡ ሕግ ፡ የሚኖሩም ፡ ነበሩ ፡፡
፯ ፡ በአራዊትም ፡ የሚያመልኩ ፡ ነበሩ ፡፡

፰ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ አባ ፡ ሰላማ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ያስተማራት ፡ ወንጌልን ፡ አስተማራቸው ፡፡
፱ ፡ በፊታቸው ፡ ብዙ ፡ አምራትን ፡ እያደረገ፡፡

፲ ፡ እነሱም ፡ አምነው ፡ ተጠምቀው ፡ ክርስትና ፡ ተነሡ ፡፡
፲፩ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰዎች ፡ ያመኑት ፡ ጌታ ፡ ባረገ ፡ በሦስት ፡ መቶ ፡ ስሳ ፡ አምስት ፡ ዘመን ፡ ነው ፡፡
፲፪ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡፡ አብርሃና ፡ አጽብሃ ፡ አክሱም ፡ ጽዮንን ፡ ሠሩዋት ፡፡ አብርሃም ፡ አስፍሕን ፡ ወለደ ፡፡ አፍስሕም ፡ አርፍድን ፡ ወለደ ፡፡
አርፍድም ፡ አምሴን ፡ ወለደ ፡፡
አምሴም ፡ አልአዳባን ፡ ወለደ ፡፡ አልአዳባም ፡ አልአሚዳን ፡ ወለደ ፡፡

፲፫ ፤ ዘመጽኡ ፡ በመንግሥቱ ፡ ፱ ፡ ቅዱሳን ፡
እምሮም ፡ ወግብጽ ።

፲፬ ፤ ወአስተራትዑ ፡ ሃይማኖተ ።

፲፭ ፤ ዘውእቶሙ ። አባ ፤ አሌፍ ፤ አባ ፤ ጽሕማ ፤
አባ ፤ አረጋዊ ፤ ካህን ፡ ዘውእቱ ፤ ዘሚካ
ኤል ። ወአባ ፡ አፍጼ ፤ አባ ፤ ገሪማ ፤ አባ ፤
ጳንጠሌዎን ፡ አባ ፡ ሊቃኖስ ፤ ወአባ ፤ ጉባ ።
ወአባ ፡ ይምዓታ ።

፲፮ ፤ እሉ ፡ እሙንቱ ፡ ከዋክብት ፡ ብሩሃን ፡ ዘአ
ዋከዩ ፡ ኵሎ ፡ አድያማተ ፡ ኢትዮጵያ ።

፲፯ ፤ ወአልአሜዳ ፡ ወለዶ ፡ ለታዚና ።

፲፰ ፤ ወታዚና ፡ ወለዶ ፡ ለካሌብ ፡ ዘሠጠቀ ፡
ምድረ ። ወካሌብ ፡ ወለዶ ፡ ለገብረ ፡ መስ
ቀል ፡ ዘሐነጻ ፤ ለዳሞ ፡ እንተ ፡ ይእቲ ፡
መካነ ፡ አባ ፡ አረጋዊ ፡ አቡነ ።
ትውልድ ፡ ፰ ።
ወገብረ ፡ መስቀል ፡ ወለዶ ፡ ለቈስጠስ
ጢኖስ ።
ወቈስጠንጢኖስ ፡ ወለዶ፡ ለወሰን ፡ ሰገድ ።
ወወሰን ፡ ሰገድ ፡ ወለዶ ፡ ለፍሬ ፡ ሠናይ ።
ወፍሬ ፡ ሠናይ ፡ ወለዶ ፡ ለአድርአዝ ።
ወአደርአዝ ፡ ወለዶ ፡ ለእክለ ፡ ውድም ።
ወእክለ ፡ ውድም ፡ ወለዶ ፡ ለግርማ ፡ ሠፈር ።
ወግርማ ፡ ሠፈር ፡ ወለዶ ፡ ለዝርጋዝ ።
ወዝርጋዝ ፡ ወለዶ ፡ ለድግና ፡ ሚካኤል ።
ወድግና ፡ ሚካኤል ፡ ወለዶ ፡ ለባሕር፡ኢክላ፡
ወባሕር ፡ ኢክላ ፡ ወለዶ ፡ ለጉም ፤
ትውልድ ፡ ፺ ።
ወጉም ፡ ወለዶ ፡ ለአስጎምጉም ።
ወአስጎምጉም ፡ ወለዶ ፡ ለልትም ።
ወልትም ፡ ወለዶ ፡ ለተላትም ።
ወተላትም ፡ ወለዶ ፡ ለዖደጎሽ
ወዖደጎሽ ፡ ወለዶ ፡ ለአይዞርር ፡ ዘነግሠ ፡
መንፈቀ ፡ ዕለት ።
ወአይዞርር ፡ ወለዶ ፡ ለድድም ።
ወድድም ፡ ወለዶ ፡ ለውድድም ።
ወውድድም ፡ ወለዶ ፡ ለውድም ፡ አስፈሬን ።
ዘመዋዕሊሁ ፡ ፻ወ፶ ፡ ዓመት ።
ወውድመ ፡ አስፈሬን ፡ ወለዶ ፡ ለአርማኅ ።
ወአርማኅ ፡ ወለዶ ፡ ለድግናዝርን ፤
ትውልድ ፡ ፻ ።
ወድግናዝርን ፡ ወለዶ ፡ ለግድአዠን ።
ወግድአዠን ፡ ወለዶ ፡ ለአንበሳ ፡ ውድም ፤
ወአንበሳ ፡ ውድም ፡ ወለዶ ፡ ለድልነአድ ፤
ትውልድ ፡ ፻ወ፲ቱ ፡ እምአዳም ።
ወእምዕብነ ፡ ሐኪም ፡ ፷ወ፰ቱ ።

፲፱ ፤ ወእምኔሁ ፡ ተሐይደት ፡ መንግሥት ፡ ወተ
ውህበት ፡ ለካልዓን ፡ እለ ፡ ኢኮኑ ፡ እም
ሕዝበ ፡ እሥራኤል ፡ ዘውእቶሙ ፡ ዛጌ ።

፳ ፤ ወነግሡ ፡ ፫፻፴ ወ፫ተ ፡ ዓመተ ።

፲፫ ፤ በነገሠበት ፡ ዘመን ፡ ዘጠኙ ፡ ቅዱሳን ፡
ከግብጽና ፡ ከሮም ፡ የመጡ ።

፲፬ ፤ ሃይማኖትን ፡ ያቀኑ ፡ ያጸኑ ።

፲፭ ፤ እነዚህም ፡ አባ ፡ አሌፍ ፡ አባ ፡ ጽሕማ ፤
አባ ፡ አረጋዊ ። አባ ፡ አፍጼ ፤ አባ ፡ ገሪማ፡
አባ ፡ ጳንጠሌዎን ፡ አባ ፤ ሊቃኖስ ፤ አባ ፤
ጉባ ፤ አባ ፤ ይምዓታ ፤ ናቸው ።

፲፮ ፤ ኢትዮጵያን ፡ በብሩህ ፡ ትምህርታቸው ፡
ብርህት ፡ ያደረጉ ፡ ብሩሃን ፡ ከዋክብት ፡
እሊህ ፡ ናቸው ።

፲፯ ፤ አልአሚዳም ፡ ታዚናን ፡ ወለደ ።

፲፰ ፤ ታዚናም ፡ ምድርን ፡ የከፈለ ፡ ካሌብን ፡
ወለደ ። ካሌብም ፡ አባታችን ፡ አቡነ ፡
አረጋዊ ፡ ያቀኗት ፡ ደብረ ፡ ዳሞን ፡ ያሠራ ፡
ገብረ ፡ መስቀልን ፡ ወለደ ።
ሰማንያ ፡ ትውልድ ፡ ይሆናል ።
ገብረ ፡ መስቀልም ፡ ቆስጠንጢኖስን ፡
ወለደ ፡ ቆስጠንጢኖስም ፡ ወሰን ፡ ሰገድን፡
ወለደ ፡ ወሰን፡ ሰገድም ፡ ፍሬ፡ ሠናይን፡ወለደ
ፍሬ ፡ ሠናይም ፡ አድርአዝን ፡ ወለደ ።
አድርአዝም ፡ እክለ ፡ ውድምን ፡ ወለደ ።
እክለ ፡ ውድምም ፡ ግርማ ፡ ሰፈርን ፡ ወለደ
ግርማ ፡ ሰፈርም ፡ ዝርጋዝን ፡ ወለደ ።
ዝርጋዝም ፡ ድግና ፡ ሚካኤልን ፡ ወለደ ።
ደግና ፡ ሚካኤልም ፡ ባሕር ፡ ኢክላን ፡ ወለደ
ባሕር ፡ ኢክላም ፡ ጉምን ፡ ወለደ ።
ዘጠና ፡ ትውልድ ፡ ይሆናል ።
ጉምም ፡ አስጎምጉምን ፡ ወለደ ።
አስጎምጉምም ፡ ልትምን ፡ ወለደ ።
ልትምም ፡ ተላትምን ፡ ወለደ ። ተላትምም፡
ዖደጎሽን ፡ ወለደ ፡ ዖደጎሽም ፡ የዕለት ፡
እኩሌታ ፡ የነገሠ ፡ አይዞርርን ፡ ወለደ ።
አይዞርርም ፡ ድምድምን ፡ ወለደ ።
ድድምም ፡ ውድድምን ፡ ወለደ ።
ውድድምም ፡ ውድም ፡ አስፈሬን ፡ ወለደ።
ዘመኑ ፡ መቶ ፡ ሃምሳ ፡ የሆነ ፡ ውድመ ፡
አስፈሬንም ፡ አርማኅን ፡ ወለደ ። አርማ
ኅም ፡ ድግናዝርንን ፡ ወለደ ፤ መቶ ፡ ትው
ልድ ፡ ይሆናል ። ድግናዝርንም ፡ ግድአዠ
ንን ፡ ወለደ ። ግድአዠንም ፡ አንበሳ ፡
ውድምን ፡ ወለደ ። አንበሳ ፡ ውድምም ፡
ድልነአድን ፡ ወለደ ። ከአዳም ፡ ጀምሮ ፡
መቶ ፡ ሦስት ፡ ትውልድ ፡ ይሆናል ። ከእ
ብነ ፡ ሐኪም ፡ ጀምሮ ፡ ስሳ ፡ ስምንት ፡ ይሆ
ናል ።

፲፱ ፤ ያንጊዜ ፡ መንግሥት ፡ ከሱ ፡ ተለይታ ፡
ከእሥራኤል ፡ ወገን ፡ ላልሆኑ ፡ ለዛጌ ፡
ልጆች ፡ ተሰጠች ።

፳ ፤ እነዚህም ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሦስት ፡
ዘመን ፡ ገዙ ።

፳፩ ፡ ወከመሰ ፡ ተመይጠት ፡ መንግሥቶሙ ፡ ለእሥራኤል ፡ በዘመኑ ፡ ለይኩኖ ፡ አምላክ፡ እምድኅረ ፡ እሉ ፡ ዓመታት ፡ **ለአቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት** ፡ በጸሎቱ ።
፳፪ ፡ ድኅረ ፡ ንትናገሮ ።
፳፫ ፡ ለእመ ፡ አብጽሐነ ፡ **እግዚአብሔር** ፡ በሥምረቱ ፡ ኀበ ፡ ገጸ ፡ ነገር ፡ ዘንትናገር ፡ ቦቱ።

## ምዕራፍ ፡ ፯ ።

፩ ፡ ንምይእዜሰ ፡ ንግባዕ ፡ ኀበ ፡ ነገርነ ፡ ዘቀዳሚ ፡ ዘወእቱ ፡ ኍልቈ ፡ ልደቱ ፡ **ለቅዱስ ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት** ።

፪ ፡ ወበርሃን ፡ **መስቀል** ፡ ወለዶ ፡ ለሕይወት ፡ ብነ ፡ **በጽዮን** ።

፫ ፡ ዘውእቱ ፡ ኖላዊነ ፡ እግዚእ ።

፬ ፡ ወሕይወት ፡ ብነ ፡ በጽዮን ፡ ወለዶ ፡ ለሴት፡ ወሴት ፡ ወለዶ ፡ ለወረደ ፡ ምሕረት ።

፭ ፡ ወወረደ ፡ ምሕረት ፡ ወለዶ ፡ ለዘርዓ ፡ ዮሐንስ ፡ ዘውእቱ ፡ ቅዱስ ፡ **ጸጋ ፡ ዘአብ** ።

፮ ፡ ወውእቱኒ ፡ ወለዶ ፡ **ለአቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ሃይማኖት** ። ትውልድ ፡ ፷ወ፩ ፡ እምአዳም ፡ ወእምእዛርያስ ፡ ፳ወ፯ ።

፯ ፡ ወከመዝ ፡ ውእቱ ፡ ልደቱ ፡ **ለአቡነ፡ቅዱስ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት** ።

፰ ፡ ቅድመሰ ፡ ዘጸዋዕናሆሙ ፡ ለአበዊሁ ፡ እደው ፡ ስሙያን ፡ እለ ፡ አበዩ ፡ በመዋዕሊሆሙ ፡ ወተሰይሙ ፡ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ።

፱ ፡ በከመ ፡ ነሥአሙ ፡ ሙሴ ፡ ለመላሕቅተ ፡ ሕዝብ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ ስምዐ ።

፲ ፡ ወንሕነሂ ፡ ኪያሆሙ ፡ ፡ መላህቅተ ፡ ሕዝብ ጸዊዓነ ፡ ኃደግነ ፡ ከመ ፡ ኢይኑህ ፡ ነገር።

፲፩ ፡ ወከመ ፡ ይኩንዎ ፡ ስምዐ ፡ ለነገርነ ።
፲፪ ፡ ወከመዝ ፡ ተረክበ ፡ በመጻሕፍተ ፡ አበዊነ።

፲፫ ፡ ዝየ ፡ ተፈጸመ ፡ ቃል ፡ ዘተብህለ ፡ ተረክበ፡ ዘርዕ ፡ ምስለ ፡ ሠርጽ ፡ ወኃብረ ፡ ቀስም ፡ ምስለ ፡ ማዕረር ።

**አሞጽ ፡ ም ፡ ፱ ፡ ቍ ፡ ፲፫ ።**

፲፬ ፡ በረከተ እሉ ፡ ቅዱሳን ፡ ክቡራን ፡ ወበረከተ ፡ **አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት** ፡ ትኩን ፡ ምስለ ፡ ሀገሪትነ ፡ ኢትዮጵያ ፤
፲፭ ፡ ወለጸሐፊሁ ፡ ኃጥእ ።
፲፮ ፡ ለዓለመ ፡ ዓለም ፡ አሜን ።

፳፩ ፡ ከሦስት ፡ መቶ ፡ ሠላሳ ፡ ሦስት ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ በአባታችን ፡ **በተክለ ፡ ሃይማኖት** ፡ ልመና ፡ በይኩኖ ፡ አምላክ ፡ ጊዜ፡ የእሥራኤል ፡ መንግሥት ፡ እንደተመለሰች።

፳፪ ፡ ወደፊት ፡ በሚመጣው ፡ እንናገራለን።
፳፫ ፡ ከምንናገርበት ፡ አንቀጽ ፡ በፈቃዱ **እግዚአብሔር** ፡ ቢያደርሰን ።

## ሰባተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፡ እንግዲህስ ፡ ወደቀደመ ፡ ነገራችን ፡ የክቡር ፡ አባታችን ፡ **የተክለ ፡ ሃይማኖትን** ፡ ልደት ፡ ወደ ፡ መቍጠር ፡ እንመለስ።

፪ ፡ ብርሃነ ፡ **መስቀልም** ፡ ሕይወት ። ብነ **በጽዮንን** ፡ ወለደ ።

፫ ፡ ይኸውም ፡ ኖላዊነ ፡ እግዚእ ፡ ይባላል።

፬ ፡ ሕይወት ፡ ብነ ፡ **በጽዮንም** ፡ ሴትን፡ ወለደ ። ሴትም ፡ ወረደ ፡ ምሕረትን ፡ ወለደ ፤

፭ ፡ ወረደ ፡ ምሕረትም ፡ ዘርዓ፡ ዮሐንስን ፡ ወለደ ፡ ይኸውም ፡ ክቡር ፡ **ጸጋ ፡ ዘአብ** ፡ ነው ።
፮ ፡ እሱም ፡ ክቡር ፡ አባታችንን ፡ **ተክለ ፡ ሃይማኖትን** ፡ ወለደ ፡ ከአዳም ፡ ጀምሮ ፡ ስልሳ ፡ አንድ ፡ ትውልድ ፡ ነው ፡ ከአዛርያስ ፡ ጀምሮ ፡ ቢቈጥሩ ፡ ሃያ፡ ሰባት ፡ ትውልድ፡ ነው ።
፯ ፡ የክቡር ፡ አባታችን ፡ **የተክለ ፡ ሃይማኖት** ፡ ልደት ፡ እንደዚህ ፡ ነው ።

፰ ፡ በዘመናቸው ፡ ሊቃነ ፡ ካህናት ፡ ሁነው ፡ ተሾመው ፡ የከበሩ ፡ ስመ ፡ ጥር ፡ የሆኑ ፡ አባቶቹን ፡ አስቀድሞ ፡ የጠራናቸው ፡ ግን፡ ምስክር ፡ ይሆኑን ፡ ዘንድ ፡ ነው ።
፱ ፡ ሙሴ ፡ የሕዝቡን ፡ አለቆች ፡ ምስክር ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ እንደመረጣቸው ።

፲ ፡ እኛም ፡ የሕዝብ ፡ አለቆች ፡ የሚሆኑ ፡ አባቶቹን ፡ ስማቸውን ፡ ጠርተን ፡ የተውነው፡ ነገር ፡ እንዳይበዛ ።
፲፩ ፡ ለሀገራችን ፡ ምስክር ፡ ይሆኑት ፡ ዘንድ ።
፲፪ ፡ አባቶቻችን ፡ በጻፉት ፡ መጽሐፍ ፡ የአባቶቻችን ፡ ልደት ፡ እንደዚህ ፡ ተገኘ ።
፲፫ ፡ ዘር ፡ ከቡቃያ ፡ ጋራ ፡ መከር ፡ ከቃርሚያ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ሆኖ ፡ ተገኘ ፡ ብሎ ፡ የተናገረው ፡ ነገር ፡ ደረሰ ፡ ተፈጸመ ።

፲፬ ፡ የክቡር ፡ አባታችን ፡ **የተክለ፡ሃይማኖትና** ፡ የሊህ ፡ የክቡራን ፡ አባቶቹ ፡ በረከት ፡ ለሀገራችን ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ትሁን ፡ ትደረግ ።
፲፭ ፡ ኃጥእ ፡ ለሚሆን ፡ ለጸሐፊውም ።
፲፮ ፡ ለዘለዓለሙ ፡ በውነት ፡ ያለሐሰት ።

፲፯ ፤ ናሁ ፡ አብጸሕነ ፡ ልደቶሙ ፡ ለአበው ፡
አበዊነ ፡ ሌዋውያን ።

፲፰ ፤ አኮ ፡ እንዘ ፡ ንሒሥሥ ፡ ክብረ ፡ ምሂሮቶሙ
ኪያነ ።

፲፱ ፤ ሥርዓተ ፡ ግዝረት ፡ ወሕገ ፡ ኦሪት ።

፳ ፤ እምአዛርያስ ፡ እስከ ፡ እንበረም ። ወእም
እንበረም ፡ እስከ ፡ አቡነ ፡ ቅዱስ ፡ ተክለ፡
ሃይማኖት ።

፳፩ ፤ እንዘ ፡ ንሒሥሥ ፡ ክብረ ፡ አጥምቆቱ ፡
ኪያነ ።

፳፪ ፤ ወምሂሮቶሙ ፡ ለነ ፡ ሕገ ፡ እግዚአብሔር፡
እግዚእነ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እንተ ፡
ይእቲ ፡ ወንጌል ።

፳፫ ፤ ወሥርዓተ ፡ አበዊነ ፡ ቅዱሳን ፡ ሐዋርያት ።

፳፬ ፤ ሶበሰ ፡ ኃሠሥነ ፡ ክብረ ፡ ልደቶሙ ፡ ሥጋ
ዊተ ።

፳፭ ፤ እምአይዳዕናክሙ ፡ እንዘ ፡ ናቀውም ፡ ስምዓ
እመጻሕፍት ፡ ቅዱሳት ።

፳፮ ፤ ቅድመ ፡ እምኦሪት ።

፳፯ ፤ ወዳግመ ፡ እመጻሕፍተ ፡ ነገሥት ።

፳፰ ፤ ወሣልሰ ፡ እምመጽሐፈ ፡ ታሪክ ፡ ዘይነግር፡
ዜናሆሙ ፡ ለአበው ፡ ቀደምት ።

፳፱ ፤ አላ ፡ ባሕቲቱ ፡ ንጌሥዕ ፡ እንከ ፡ ከመ ፡
ንንግር ፡ ዜና ፡ አቡነ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
መምህር ።

፴ ፤ ዘይጥዕም ፡ እመዓር ፡ ወሦከር ።

፴፩ ፤ ወይትበደር ፡ እምዕንቍ ፡ ሰንፔር ፡ እም
ወርቅሂ ፡ ወእምብሩር ።

፴፪ ፤ ስብሐት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘአብጽሐነ፡
ኀበ ፡ ገጸ ፡ ዛቲ ፡ ነገር ።

## ምዕራፍ ፡ ፰ ።

፩ ፤ ወጸጋ ፡ ዘእብ ፡ ነሥአ ፡ ብእሲተ ፡ እምክ
ቡራነ ፡ ሀገር ፡ እንተ ፡ ስማ ፡ ሣራ ።

፪ ፤ ወኮኑ ፡ ጥቀ ፡ መሠምርያነ ፡ ለእግዚአብ
ሔር ።

፫ ፤ በጾም ፡ ወበጸሎት ።

፬ ፤ ወበትዕግሥት ።

፭ ፤ ወያፈደፍዱ ፡ ገቢረ ፡ ሠናይ ፡ እምዕለት ፡
ዕለተ ።

፮ ፤ ወ፪ሆሙ ፡ ፍቁራን ፡ በበይናቲሆሙ ።

፯ ፤ ከመ ፡ አብርሃም ፡ ወሣራ ።

፰ ፤ ወከመ ፡ ዘካርያስ ፡ ወኤልሳቤጥ ።

፱ ፤ ወሣራሰ ፡ ላህይት ፡ ወመዓድምት ።

፲ ፤ ወያነክራ ፡ ኵሉ ፡ ዘርእየ ፡ ገጻ ፡ ወዘሰምዓ ፡
ድምፃ ።

፲፯ ፤ እነሆ ፡ ያባታችን ፡ የተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
ያባቶቹ ፡ የሌዋውያንን ፡ ልደት ፡ ቆጥረን ፡
ነገርናችሁ ።

፲፰ ፤ መናገራችንም ፡ የነሱን ፡ ክብር ፡ ሽተን ፡
አይደለም ።

፲፱ ፤ የኦሪትን ፡ ሥራትና ፡ የግዝረትን ፡ ሥራት፡
አስተምረውናል ፡ ብለን ።

፳ ፤ ከአዛርያስ ፡ እስከ ፡ እንበረም ፡ ከእንበ
ረም ፡ እስከ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ድረስ ።

፳፩ ፤ እኛ ፡ የማጥመቃቸውን ፡ ክብር ፡ ሽተን ፡
አይደለም ።

፳፪ ፤ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ያስተማ
ራትን ፡ ወንጌል ፡ አስተምረውናል ፡ ብለን ፡
አይደለም ።

፳፫ ፤ መጻሕፍተ ፡ ሐዲሳት ፡ አስተምረውናል ፡
ብለን ፡ አይደለም ።

፳፬ ፤ የሥጋ ፡ ልደታቸውንስ ፡ ክብር ፡ ሽተን ፡
ቢሆን ።

፳፭ ፤ የክቡራት ፡ መጻሕፍትን ፡ ምስክር ፡ እየ
ጠራን ፡ በነገርናችሁ ፡ ነበር ።

፳፮ ፤ ቀድሞ ፡ መጀመሪያ ፡ ከኦሪት ።

፳፯ ፤ ሁለተኛም ፡ ከመጽሐፈ ፡ ነገሥት ።

፳፰ ፤ ሦስተኛም ፡ ያባቶቻችንን ፡ ነገር ፡ የሚ
ናገር ፡ ከመጽሐፈ ፡ ታሪክ ፡ እያመጣን ፡
በነገርናችሁ ፡ ነበር ።

፳፱ ፤ የክቡር ፡ አባታችን ፡ የተክለ ፡ ሃይማኖት
ነገር ፡ ብቻ ፡ እንናገር ፡ ዘንድ ፡ እንቸኩላ
ለን ፡ እንጂ ።

፴ ፤ ከማር ፡ ከሦከር ፡ ይልቅ ፡ የሚጣፍጥ ።

፴፩ ፤ ከብር ፡ ከወርቅ ፡ ከዕንቍ ፡ ይልቅ ፡ የሚ
ወደድ ፡

፴፪ ፤ ይኸንን ፡ ነገር ፡ ለመናገር ፡ ላበቃን ፡ ለእ
ግዚአብሔር፡ ክብር ፡ ምስጋና ፡ ይግባው ።

## ስምንተኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ጸጋ ፡ ዘአብም ፡ ከዚያች ፡ ሀገር ፡ ደጋግ ፡
ከሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ወገን ፡ ሣራ ፡ የምትባል ፡
ሴት ፡ አግብቶ ፡ ተቀመጠ ።

፪ ፤ እግዚአብሔርን ፡ በማገልገል ፡ እጅግ ፡
ደግ ፡ ሆኑ ።

፫ ፤ ጾም ፡ በመጾም ፡ ጸሎት ፡ በመጸለይ ።

፬ ፤ ትዕግሥትንም ፡ ገንዘብ ፡ በማድረግ ።

፭ ፤ ከቀን ፡ ቀን ፡ እያሉ ፡ በጎ ፡ ሥራን ፡ እያ
በዙ ፡ ሄዱ ።

፮ ፤ ሁለቱም ፡ እጅግ ፡ ይዋደዱ ፡ ነበር ።

፯ ፤ እንደ ፡ አብርሃምና ፡ እንደሣራ ።

፰ ፤ እንደ ፡ ኤልሳቤጥና ፡ እንደ ፡ ዘካርያስ ።

፱ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ሣራ ፡ እጅግ ፡ መልከ ፡ መል
ካም ፡ ነበረች ።

፲ ፤ ነገሯን ፡ የሰማ ፡ መልኳን ፡ ያየ ፡ ሁሉ ፡
እጅግ ፡ ያደንቃት ፡ ነበረ ።

፲፩ ፡ ወእንዘ ፡ ሀለወት ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ሐሙሃ፡
ከሠተት ፡ ዘበሕግ ።
፲፪ ፡ ወዓቀመት ፡ ሥርዓተ ፡ ለልሳና ።
፲፫ ፡ ወእሙንታ ፡ አጽንዓት ፡ ለፈቲል ።
፲፬ ፡ ወሶበ ፡ ርእያ ፡ ሐሙሃ ፡ ኵሎ ፡ ሥነ ፡ ጊሩታ።

፲፭ ፡ ወለጠ ፡ ስማ ፡ ወሰመያ ፡ እግዚእ ፡ ሐረያ ።
፲፮ ፡ ወእምይእቲ፡ ሰዓት ፡ ተጸወዓት ፡ በዝንቱ ፡
ስም ።
፲፯ ፡ ወእምዝ ፡ ሞተ ፡ ሕይወት ፡ ብነ ፡ በጽዮን ።

፲፰ ፡ ወተርፉ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ወብእሲቱ ።
፲፱ ፡ ወኮኑ ፡ ብዑላነ ፡ ጥቀ ፡ በንዋይ ።
፳ ፡ ወባሕቱ ፡ ኮነት ፡ መካነ ፡ እግዚእ ፡ ሐረያ።

፳፩ ፡ ወአልባቲ ፡ ውሉድ ።
፳፪ ፡ ወበበይነ ፡ ዝንቱ ፡ አኀዙ ፡ ገቢረ ፡ በዓሉ ፡
ለሚካኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡ አመ ፡
፲ወ፪ ፡ ለለወርኁ ።
፳፫ ፡ በአጽግቦ ፡ ርኁባን ፡ ወበአርውዮ ፡ ጽሙ
ኣን ።

ማቴ ፡ ም ፡ ፳፭ ፡ ቍ ፡ ፴፭ ።

፳፬ ፡ ወበአልብሶ ፡ ዕሩቃን ።
፳፭ ፡ ወበአልዕሎ ፡ ንዳያን ።
፳፮ ፡ በረዲአ ፡ ምንዱባን ።
፳፯ ፡ ወበሰዊቀ ፡ ትንቱናን ።

፳፰ ፡ ወተወክፎ ፡ ነግድስ ፡ ልማዶሙ ፡ ውእቱ ፡
ለዘልፍ ።
፳፱ ፡ ወይቴክዝ ፡ ኵሉ ፡ ዘርእየ ፡ ኪያሆሙ ።
፴ ፡ ወዘሰምዓ ፡ ዜናሆሙ ፡ በእንተ ፡ ዘአልቦሙ
ውሉድ ።
፴፩ ፡ ወሰብአ ፡ ሀገርሂ ፡ ይትበሃሉ በበይናቲ
ሆሙ ።
፴፪ ፡ ምንተ ፡ ይሜኒ ፡ ወምንተ ፡ ይትፊቀር ፡
ህላዌ ፡ ንብረቶሙ ፡ ለጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ወለ
እግዚእ ፡ ሐረያ ፡ በኀበ ፡ እግዚአብሔር
ወሰብእ ።
፴፫ ፡ ወእግዚእ ፡ ሐረያ ፡ ኮነት ፡ ሕምምተ ፡ ልብ
በእንተ ፡ ዘኮነት ፡ መካነ ።
፴፬ ፡ ወባሕቱ ፡ አጥብዓት ፡ ልባ ፡ ኀበ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ከመ ፡ የሀባ ፡ ወልደ ።

፴፭ ፡ ወጌሠት ፡ ኀበ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወጸለ
የት ፡ እንዘ ፡ ትብል ።
፴፮ ፡ አ ፡ እግዚእየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡እግዚኡ
ለሚካኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡ ወንጌል ።
፴፯ ፡ አንተ ፡ ውእቱ ፡ ገባሬ ፡ መላእክት ።
፴፰ ፡ እበ ፡ ኵሉ ፡ ሰርጐ ፡ ዓለም ።
፴፱ ፡ ፍሥሓሆሙ ፡ ለሕዙናን ።

፵ ፡ ወረዳኢሆሙ ፡ ለምንዱባን ።

፲፩ ፡ ከአማቷ ፡ ቤትም ፡ ሳለች ፡ በሕግ ፡ ጸንታ ፡
ሥራዋን ፡ ሁሉ ፡ ገለጸች ።
፲፪ ፡ ለአንደበቷ ፡ መወሰንን ።
፲፫ ፡ ክንዷን ፡ ለመፍተል ፡ አጸናች ።
፲፬ ፡ አማቷ ፡ የሥራዋን ፡ ሁሉ ፡ ደግነት ፡ ባየ ፡
ጊዜ ።
፲፭ ፡ ስሟን ፡ ለውጦ ፡ እግዚእ ፡ ሐረያ ፡ አላት ።
፲፮ ፡ ከዚያች ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ በዚህ ፡ ስም ፡ ስት
ጠራ ፡ ኖረች ።
፲፯ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሕይወት ፡ ብነ ፡ በጽዮን ፡
ሞተ ።
፲፰ ፡ ሚስቱና ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ተቀመጡ ።
፲፱ ፡ በገንዘብ ፡ እጅግ ፡ የከበሩ ፡ ሆኑ ።
፳ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እግዚእ ፡ ሐረያ ፡ መካን ፡
ሆነች ።
፳፩ ፡ ልጅም ፡ አልነበራት ።
፳፪ ፡ ስለዚህም ፡ ነገር ፡ በወር ፡ በወሩ ፡ በዐስ
ራሁለት ፡ ቀን ፡ የሚካኤልን ፡ በዓል ፡ ማዘ
ከር ፡ ጀመሩ ።
፳፫ ፡ የተራበ ፡ በማብላት ፡ የተጸማ ፡ በማጠ
ጣት ።

ማቴ ፡ ሃያ ፡ አምስት ፡ ቍ ፡ ፴፭ ።

፳፬ ፡ የታረዘ ፡ በማልበስ ።
፳፭ ፡ ነዳያንን ፡ በማክበር ።
፳፮ ፡ የተቸገሩትን ፡ በመርዳት ።
፳፯ ፡ ቀን ፡ ያዋረዳቸውን ፡ ወራት ፡ የባሳቸውን ፡
በመደገፍ ።
፳፰ ፡ እንግዳ ፡ መቀበል ፡ ግን ፡ የዘወትር ፡ ልማ
ዳቸው ፡ ነበር ።
፳፱ ፡ እነሱን ፡ ያየ ፡ ልጅ ፡ እንደ ሌላቸው ም ።
፴ ፡ የሰማ ፡ ሁሉ ፡ ያዝን ፡ ነበር ።

፴፩ ፡ ያገራቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ እርስ በርሳቸው ፡
እንዲህ ፡ ይባባሉ ፡ ነበር ።
፴፪ ፡ በሰወና ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የእ
ግዚእ ፡ ሐረያና ፡ የጸጋ ፡ ዘአብ ፡ አነዋወር ፡
ምን ፡ ያምር ፡ ምንኛ ፡ ይወደድ ፡ ይሉ ፡
ነበር ።
፴፫ ፡ እግዚእ ፡ ሐረያም ፡ መካን ፡ ስለሆነች ፡
በልቡናዋ ፡ ታዝን ፡ ትቆረቆር ፡ ነበር ።
፴፬ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ልጅ ፡ ይሰጣት ፡ ዘንድ ፡ ልቡ
ናዋን ፡ አጽንታ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለመ
ነች ።
፴፭ ፡ ማለዳ ፡ ወደቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሄዳ ፡ እን
ዲህ ፡ ብላ ፡ ለመነች ።
፴፮ ፡ የመላእክት ፡ አለቃ ፡ የሚሆን ፡ የሚካኤል
ጌታ ፡ ጌታዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ።
፴፯ ፡ የመላእክት ፡ ፈጣሪ ፡ አንተ ፡ ነህ ።
፴፰ ፡ ያለሙ ፡ ሁሉ ፡ ጌጽ ፡ መገኛ ፡ አንተ ፡ ነህ ።
፴፱ ፡ ያዘኑትን ፡ ደስ ፡ የምታሰኛቸው ፡ አንተ ፡
ነህ ።
፵ ፡ ለተቸገሩትም ፡ ረዳታቸው ፡ አንተ ፡ ነህ ።

፵፩ ፤ ተሰፋሆሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ አጽናፈ ፡ ምድር።

፵፪ ፤ ወለእለሂ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡ ርኁቅ ።

፵፫ ፤ አንተ ፡ ውእቱ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ።

፵፬ ፤ ወእግዚአ ፡ አጋእዝት ።

፵፭ ፤ ኃይሎሙ ፡ ለኃይላት ።

፵፮ ፤ ወአምላኮሙ ፡ ለአማልክት ።

፵፯ ፤ ዘለከ ፡ ይሰግዱ ፡ አዕማደ ፡ መባርቅት ።

፵፰ ፤ ወለከ ፡ ይሰግዱ ፡ ይትቀነዩ ፡ ነጐድጓድ፡ ወጸዓዕ ፡ ወነፋሳት ።

፵፱ ፤ ወበትእዛዝከ ፡ ሥሩዕ ሩጸተ፡ ፀሐይ ፡ወወርኅ ፡ ወከዋክብት ።

፶ ፤ በክሂሎትከ ፡ ወበጽንዓ ፡ መንግሥትከ ።

፶፩ ፤ ስምዓኒ ፡ እግዚኦ ፡ ጸሎትየ ፤

፶፪ ፤ ወሀበኒ ፡ ወልደ ፡ ዘኢያስምሮ ፡ ለኂሩትከ።

፶፫ ፡ ወእመሰ ፡ ኮነ ፡ ዘኢያስምሮከ ፡ ዕጹ ፡ ማኅፀንየ ።

፶፬ ፤ ወዘንተ ፡ ብሂላ ፡ አተወት ፡ ቤታ ።

፶፭ ፤ ወለምታሰ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ልማዱ ፡ ውእቱ ገይሠ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሌሊት ፡ ወበመዓልት ፡ በጽባሕ ፡ ወበምሴት ።

፶፮ ፤ ቦ ፡ አመ ፡ ይገይስ ፡ ለአጢን ፡ ዕጣን ።
ወቦ ፡ አመ ፡ ይገይስ ፡ ለሠሪዓ ፡ ቍርባን።

፶፯ ፤ ቦ ፡ አመ ፡ ይገይስ ፡ ለዘምሮ ፡ ዳዊት ።

፶፰ ፤ ወቦ ፡ አመ ፡ ይገይስ ፡ ለአንበቦ ፡ መጻሕፍት ።

፶፱ ፤ ወቦ ፡ አመ ፡ ይገይስ ፡ ለምህሮ ፡ ሃይማኖት ።

፷ ፤ ወቦ ፡ አመ ፡ ይገይስ ፡ ለገቢረ ፡ ጸሎት ፡ ወትሩፋት ።

፷፩ ፤ ወምስለዝ ፡ ኵሉ ፡ ሩጸቱ ፡ መስተፋጥኒት ። ኢያስተርኢ ፡ ዕራቀ ፡ ቅድመ ፡ እግዚአብሔር ፡

፷፪ ፤ ወያመጽእ ፡ አምኃ ፡ ብዙኃ ፡ ለቤተ ክርስቲያን ።

፷፫ ፤ ወፈጺሞ ፡ መልእክቶ ፡ የሐቱ ፡ ቤቶ ።

፷፬ ፤ ወነበሩ ፡ ከመዝ ፡ ብዙኃ ፡ መዋዕለ ።

## ምዕራፍ ፡ ፱ ።

፩ ፤ ወአሐተ ፡ ዕለተ ፡ ትቤሎ ፡ እግዚእ ፡ ሐረያ ለጸጋ ፡ ዘአብ ።

፪ ፤ እግዚእየ ፡ ሀለወኒ ፡ ነገር ፡ ዘእነግረከ ።

፫ ፤ ትትዌከፍኑ ፡ እምኔየ ፡ ዘእነግረከ ።

፬ ፡ ወይቤላ ፡ እመሰ ፡ ኮነ ፡ ሠናየ ፡ እትዌከፍ።

፵፩ ፤ በዓለሙ ፡ ዳርቻ ፡ ላሉት ፡ ሁሉ ፡ አለኝታቸው ፡ አንተ ፡ ነህ ።

፵፪ ፤ በባሕርም ፡ ላሉት ፡ ሁሉ ፡ አለኝታቸው ፡ አንተ ፡ ነህ ።

፵፫ ፤ የነገሥታቱ ፡ ገዥ ፡ አንተ ፡ ነህ ።

፵፬ ፤ የመላዕክት ፡ ጌታቸው ።

፵፭ ፤ የመላዕክት ፡ ኃይላቸው ።

፵፮ ፤ አማልክት ፡ ዘበጸጋ ፡ ለተባሉት ፡ ፈጣሪያቸው ፡ አንተ ፡ ነህ ።

፵፯ ፤ የመብረቅ ፡ ምሰሶዎች ፡ ሁሉ ፡ የሚታዘዙልህ ።

፵፰ ፤ ነፋሳትና ፡ ብልጭልጭታ ፡ ነጐድጓድም፡ የሚገዙልህ ።

፵፱ ፤ ለይኩን ፡ ብርሃን ፡ ባልከው ፡ ትእዛዝ ፡ የከዋክብትና ፡ የጨረቃ ፡ የፀሐይ ፡ መመላለስ የተሰራ ።

፶ ፤ በጌትነትህ ፡ ጽናትና ፡ በከሃሊነትህ ።

፶፩ ፤ አቤቱ ፡ ልመናዬን ፡ ስማኝ ።

፶፪ ፤ ቸርነትህን ፡ የሚያገለግል ፡ ልጅ ፡ ስጠኝ ።

፶፫ ፤ አንተን ፡ የማያገለግል ፡ ከሆነ ፡ ማኅፀኔን፡ ዝጋ ፡ ብላ ፡ ለመነች ።

፶፬ ፤ ይህን ፡ ብላ ፡ ወደቤቷ ፡ ተመልሳ ፡ ገባች ።

፶፭ ፤ የባሏ ፡ የጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ግን ፡ ሥራው ፡ ጧት ፡ ማታም ፡ በመዓልትም ፡ በሌሊትም ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መገስገስ ፡ ነበር።

፶፮ ፤ ዕጣን ፡ ለማጠን ፡ ለሚሄድበትም ፡ ጊዜ ፡ አለ ፡ መሥዋዕት፡ ለመሥራት ፤ የሚሄድበትም ፡ ጊዜ፡ አለ ።

፶፯ ፤ ዳዊት ፡ ለመድገምም ፡ የሚሄድበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ።

፶፰ ፤ መጻሕፍት ፡ ለማንበብ ፡ (ለመመልከት) የሚሄድበትም ፡ ጊዜ ፡ አለ ።

፶፱ ፤ ወንጌልን ፡ ለማስተማር ፡ የሚሄድበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ።

፷ ፤ የትሩፋት ፡ ሥራ ፡ ለመሥራትና ፡ ጸሎት ፡ ለማድረግ ፡ የሚሄድበት ፡ ጊዜ ፡ አለ ።

፷፩ ፤ እየተፋጠነ ፡ ከሚሠራው ፡ ሥራ ፡ ሁሉ፣ ጋራ ፡ ወደቤተ ፡ እግዚአብሔር፡ ባዶ ፡ እጁን ፡ አይሄድም ።

፷፪ ፤ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚሆን ፡ እጅ ፡ መንሻ ፡ ይዞ ፡ ይመጣል ።

፷፫ ፤ ሥራውንም ፡ ከጨረሰ ፡ በኋላ ፡ ወደቤቱ ፡ ይመለሳል ።

፷፬ ፤ እንዲህ ፡ እያደረጉ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ተቀመጡ ።

## ዘጠነኛ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ከዕለታት ፡ በአንድ ፡ ቀን ፡ እግዚእ ፡ ሐረያ፡ ጸጋ ፡ ዘአብን ፡ እንዲህ ፡ አለችው ።

፪ ፤ ጌታዬ ፡ የምነግርህ ፡ ነገር ፡ ነበረኝ ።

፫ ፤ ብነግርህ ፡ ትቀበለኛለህን ፡ አለችው ።

፬ ፤ ደግም ፡ እንደሆነ ፡ እቀበልሻለሁ ።

፭ ፡ እመሰ ፡ አልቦ ፡ ኢይትዌከፍ ።
፮ ፡ ወትቤሎ ፡ ሠናይ ፡ ውእቱ ፡ ነገርየ ፡ እግዚእየ ።
፯ ፡ ወይቤላ ፡ በሊ ፡ ተናገሪ ።
፰ ፡ ወትቤሎ ፡ እስመ ፡ ናሁ ፡ አቡከ ፡ ወእምከ፡ ሞቱ ።
፱ ፡ ወንሕነኒ ፡ አልብነ ፡ ውሉድ ።
፲ ፡ ለመኑ ፡ ይከውን ፡ ንዋይነ ።
፲፩ ፡ ነሀብ ፡ ዘይትፈቀድ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን።
፲፪ ፡ ወዘይትፈቀድ ፡ ለነዳያን ፡ ይኩን ፡ ለነዳያን ።
፲፫ ፡ ለአግብርቲነሂ ፡ ወለአእማቲነሂ ፡ ናግእዞሙ ፡ እምግብርናት ።
፲፬ ፡ ከመ ፡ ያግዕዘነ ፡ እግዚአብሔር ፡ እምግብርናተ ፡ ኃጢያት ።
፲፭ ፡ ወኵሎ ፡ ቆሳቊሳተ ፡ ቤትነ ፡ ዘተርፋ ፡ ይኩን ለምስኪናን ።
፲፮ ፡ ከመ ፡ ይኩን ፡ እግዚአብሔር ፡ በዓለ ፡ ዕዳነ።
፲፯ ፡ እመኒ ፡ ወለድነ ፡ ወልደ ።
፲፰ ፡ ዘጊበነ ፡ ወርቀ ፡ ወብሩረ ፡ ወኵሎ ፡ ንዋያተ ፡ ዓለም ፡ ዘአልቦ ፡ ኍልቍ ፡ ለእመ ፡ ኀደግነ ፡ ሎቱ ፡ ምንተ ፡ ይበቍዖ ።
፲፱ ፡ ሶበ ፡ ኮነ ፡ ዘኢያሠምሮ ፡ ለእግዚአብሔር ።
፳ ፡ ኵሉ ፡ ይጠፍዕ ፡ ቦቱ ፡ በከንቱ ።
፳፩ ፡ ወይቤላ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ አ ፡ እኅትየ ፡ ነገርኪሰ ፡ ጥቀ ፡ አዳም ፡ ወጥቀ ፡ ሠናይ ።
፳፪ ፡ ወባሕቱ ፡ ንስቲተ ፡ ንትአገሥ ።
፳፫ ፡ ጽሑፍ ፡ ዘይብል ።
፳፬ ፡ ለውሂብ ፡ ኢትጕጕዕ ።
፳፭ ፡ ወውሂበከ ፡ ኢትናፍቅ ።
፳፮ ፡ እስመ ፡ ንፉቅ ፡ እም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይርኁቅ ፡
፳፯ ፡ ወትቤሎ ፡ እግዚእ ፡ ሐረያ ፡ ሐሰ ፡ ለከ ፡ እግዚእየ ።
፳፰ ፡ ናስተፋጥን ፡ ለገቢረ ፡ ሠናይ ።
፳፱ ፡ መኑ ፡ ይሴብሖ ፡ ለልዑል ፡ በውስተ ፡ መቃብር ።
፴ ፡ እንዘ ፡ ፍቱሕ ፡ ሥጋነ ፡ ናስተፍሥሖ ፡ ለነፍስነ ።
፴፩ ፡ ወናሥምሮ ፡ ለአምላክነ ።
፴፪ ፡ ወሰሚዖ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ዘንተ ፡ ቃለ ፡ እምአፈ ብእሲቱ ፡ አንከረ ፡ ወተደመ ።
ማቴ ፡ ም ፡ ፲፭ ፡ ቍ ፡ ፳፰ ።
፴፫ ፡ ወይቤላ ፡ ቦ ፡ ብእሲቶ ፡ ዓቢይ ፡ ሃይማኖትኪ።
፴፬ ፡ ፍቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አንቲ ።
፴፭ ፡ አንሰ ፡ እብል ፡ በእንቲአኪ ፡ ከመ ፡ ቃለ ፡ ነቢይ ። ።
፴፮ ፡ ውሉድ ፡ ወሕንጻ ፡ ሀገር ፡ ያዓብዩ ፡ ስመ ።
፴፯ ፡ ወእምፀሆሙ ፡ ብእሲት ፡ እንተ ፡ ሠናይ ፡ ልባ ።

፭ ፡ ዳግም ፡ ካልሆነ ፡ አልቀበልሽም ፡ አላት።
፮ ፡ ጌታዬ ፡ ነገሩስ ፡ ደግ ፡ ነው ።
፯ ፡ በይ ፡ ተናገሪ ፡ አላት ።
፰ ፡ እነሆ ፡ አባትህም ፡ እናትህም ፡ ሞቱ ።
፱ ፡ እኛም ፡ ልጅ ፡ የለን ።
፲ ፡ ገንዘባችን ፡ ለማን ፡ ይሆናል ።
፲፩ ፡ ለቤተ ክርስቲያን ፡ የሚያሻውን ፡ እንስጥ።
፲፪ ፡ ለነዳያንም ፡ የሚያሻውን ፡ ለነዳያን ፡ እንስጥ ።
፲፫ ፡ ወንዶችንም ፡ ሴቶችንም ፡ ባሮቻችንን ፡ ነጻ ፡ እናውጣቸው ።
፲፬ ፡ ለኃጢያት ፡ ከመገዛት ፡ እግዚአብሔር ፡ ነጻ ፡ ያደርገን ፡ ዘንድ ።
፲፭ ፡ የቀረው ፡ የቤት ፡ ዕቃችንንም ፡ ሁሉ ፡ ለድኃ ፡ እንስጠው ።
፲፮ ፡ ብድራችንን ፡ እግዚአብሔር ፡ ይከፍለን ፡ ዘንድ ።
፲፯ ፡ ልጅ ፡ ወልደን ።
፲፰ ፡ ሥፍር ፡ ቍጥር ፡ የሌለው ፡ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ገንዘብ ፡ ሰብስበን ፡ ብንተውለት ፡ ምን ፡ ይረባዋል ፡ (ምን ፡ ይጠቅመዋል ።)
፲፱ ፡ እግዚአብሔርን፡ ደስ ፡ የማያሰኝ ፡ ካልሆነ።
፳ ፡ ሁሉም ፡ ፈጥኖ ፡ ይጠፋበታል ።
፳፩ ፡ እኅቴ ፡ ነገርሽስ ፡ እጅግ ፡ ያማረ ፡ የተወደደ ፡ ነው ።
፳፪ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ጥቂት ፡ እንታገስ ።
፳፫ ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ጽሑፍ ፡ አለና ።
፳፬ ፡ ለመስጠት ፡ አትቸኩል ።
፳፭ ፡ ከሰጠህም ፡ በኋላ ፡ አይቆጭህ ።
፳፮ ፡ የሚጠራጠር ፡ ሰው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አንድነት ፡ የተለየ ፡ ነውና ።
፳፯ ፡ እግዚእ ፡ ሐረያም ፡ ጌታዬ ፡ ይህ ፡ ላንተ አይደለም ፡ ትለችው ።
፳፰ ፡ ለበጎ ፡ ሥራ ፡ እንቸኩል ፡ እንጂ ።
፳፱ ፡ ሰው ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚያመሰግነው ፡ ማነው ።
፴ ፡ ለመስጠት ፡ ሲቻለን ፡ መጽውተን ፡ ነፍሳችንን ፡ ደስ ፡ እናሰኛት ፡ እንጂ ።
፴፩ ፡ ፈጣሪያችንን ፡ ደስ ፡ እናሰኘው ፡ እንጂ ።
፴፪ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብም ፡ ይኸን ፡ ነገር ፡ ከሚስቱ፡ ሰምቶ ፡ ፈጽሞ ፡ አደነቀ ።
፴፫ ፡ አንቺ ፡ ሴት ፡ ሃይማኖትሽ ፡ ፍጹም ፡ ነው ።
፴፬ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ዳረጎት ፡ ነሽ ።
፴፭ ፡ ስላንቺ ፡ እናገራለሁ ፡ ነቢይ ፡ እንደተናገረ።
፴፮ ፡ ሥራና ፡ ልጅ ፡ ስም ፡ ያስጠራሉ ።
፴፯ ፡ ከሁለቱም ፡ ይልቅ ፡ ልቦናዋ ፡ ቀና ፡ የሆነ ፡ ሴት ፡ ትበልጣለች ።

፷፰ ፤ ግርከ ፡ ወማኅበር ፡ ይበቍዑ ፡ በመዋዕሊሆሙ ።
፷፱ ፤ ወእምነ ፡ ፪ሆሙ ፡ ብእሲት ፡ ኄርት ፡ ለምታ ።
፸ ፤ ወበእንተ ፡ ምክርኪ ፡ ዕብል ።
፸፩ ፤ አኃው ፡ ወረድኤት ፡ ይከውኑ ፡ ኃይለ ፡ ለዕለተ ፡ ምንዳቤ ።
፸፪ ፤ ወእም፪ሆሙ ፡ ምጽዋት ፡ ትኄይስ ፡ ለአድኅኖ ።
፸፫ ፤ ወርቅ ፡ ወብሩር ፡ ያጸንዑ ፡ ሀገረ ።
፸፬ ፤ ወእምነ ፡ ፪ሆሙ ፡ ምክር ፡ ሠናይት ።
፸፭ ፤ ብዕል ፡ ወንዋይ ፡ ያስተፌሥሑ ፡ ልበ ።
፸፮ ፤ ወእምነ ፡ ፪ሆሙ ፡ ፈሪሃ ፡ እግዚአብሔር ።
፸፯ ፤ አልቦ ፡ ዘታኅጥእ ።
፸፰ ፤ ወኢትፈቅድ ፡ ባቲ ፡ ረድኤተ ።
፸፱ ፤ ፈሪሃ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመ ፡ ገነተ ፡ እግዚአብሔር ፡ በረከታ ።
፹ ፤ ወኵሉ ፡ ክብር ፡ ወትፍሥሕት ፡ ሀሎ ፡ ውስቴታ ።
፹፩ ፤ አ ፡ ብእሲቶ ፡ ጽድቀ ፡ ሀለየ ፡ ልብኪ ።
፹፪ ፤ ወጽድቀ ፡ ተናገረ ፡ አፉኪ ።
፹፫ ፤ እገብር ፡ ፍጡነ ፡ ኵሎ ፡ ዘትቤልኒ ።
፹፬ ፤ ወዘንተ ፡ ብሂሎ ፡ ዘረወ ፡ ኵሎ ፡ ንዋዮ ፡ ለነዳያን ፡ ወለምስኪናን ።
፹፭ ፤ ለዕቤራት ፡ ወለዕጓለ ፡ ማውታ ።
፹፮ ፤ ወለእለ ፡ ቦሙ ፡ ተጽናስ ።
፹፯ ፤ ወመንፈቀ ፡ ወሀበ ፡ ለቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ በከመ ፡ አምከረቶ ፡ ብእሲቱ ፡ ኄርት ።
፹፰ ፤ ወካዕበ ፡ ጸውዓሙ ፡ ለአግብርቲሁ ፡ ወለአዕማቲሁ ፤
፹፱ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ለክሙ ፡ ዕብለክሙ ፡ ሑሩ ፡ ኀበ ፡ ፈቀድክሙ ።
፺ ፤ እምግብርናት ፡ ግዑዛነ ፡ ኩኑ ፡ በእንተ ፡ ፍቅረ ፡ እግዚአብሔር ።
፺፩ ፤ ከመ ፡ ያግዕዘኒ ፡ ወእቱ ፡ ሊተኒ ፡ ወለብእሲትየኒ ፤
፺፪ ፤ ወሰሚዖሙ ፡ አግብርቲሁ ፡ ወአዕማቲሁ ፡ በከዩ ፡ ጥቀ ።
፺፫ ፤ ወይቤልዎ ፡ ምንተ ፡ ረሰይናከ ፡ እግዚእነ ።
፺፬ ፤ ወምንተ ፡ ገበርነ ፡ ዘየኃዝነከ ፡ ወዘያስተቆጥዐከ ፡ አ ፡ አቡነ ።
፺፭ ፤ ወለእመኒ ፡ አበስነ ፡ ለከ ፡ ናሁ ፡ ቅድሜከ ፡ ሰውቀ ፡ ወመቃይጽ ፡ ገሥጸነ ፡ ወንትጌሠጽ ።
፺፮ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ።
፺፯ ፤ አልቦ ፡ ዘአኅዘንክሙኒ ፡ ወአልቦ ፡ አመ ፡ አተከዝክሙኒ ።

፷፰ ፤ ወዳጅ ፡ ወገን ፡ በዘመናቸው ፡ ይጠቅማሉ ።
፷፱ ፤ ከነሱም ፡ ይልቅ ፡ ለባሏ ፡ ደግ ፡ የሆነች ፡ ሴት ፡ ትበልጣለች ።
፸ ፤ ስለምክርሽም ፡ እንዲህ ፡ እላለሁ ።
፸፩ ፤ ወንድም ፡ ረዳትም ፡ በመከራ ፡ ጊዜ ፡ ኃይል ፡ ይሆናሉ ።
፸፪ ፤ ከሁለቱም ፡ ይልቅ ፡ ለማዳን ፡ ምጽዋት ፡ ትበልጣለች ።
፸፫ ፤ ገንዘብ ፡ ሀገርን ፡ ያጸናል ።
፸፬ ፤ ከሁለቱ ፡ ይልቅ ፡ በጎ ፡ ምግባር ፡(በጎ ፡) ምክር ፡ ትበልጣለች ።
፸፭ ፤ መክበር ፡ ገንዘብ ፡ ማግኘት ፡ ልብ ፡ ደስ ያሰኛል ።
፸፮ ፤ ከነዚህ ፡ ይልቅ ፡ ፈሪሃ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትበልጣለች ።
፸፯ ፤ የምታሳጣው ፡ የለም ።
፸፰ ፤ ረዳት ፡ አትሻም ።
፸፱ ፤ ፈሪሃ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደገነት ፡ በረከቷ ፡ ብዙ ፡ ነው ።
፹ ፤ ፍጹም ፡ ክብር ፡ ተድላ ፡ (ደስታ ፡)በሷ ፡ ይገኛል ።
፹፩ ፤ አንቺ ፡ ሆይ ፡ ልቡናሽ ፡ በጎ ፡ ነገርን ፡ አስቧል ።
፹፪ ፤ እውነት ፡ ነገር ፡ ተናገርሽ ።
፹፫ ፤ ያልሽኝን ፡ ሁሉ ፡ ፈጥኜ ፡ አደርጋለሁ ።
፹፬ ፤ ይኸን ፡ ብሎ ፡ ገንዘቡን ፡ ሁሉ ፡ ለነዳያን ፡ መጸወተ ።
፹፭ ፤ ባል ፡ ልጅ ፡ (ረጅ ፡) ለሌላት ፡ ረዳ ።
፹፮ ፤ ሐዘኒ ፡ መጋቢ ፡ ለሌለው ።
፹፯ ፤ ቸር ፡ የሆነች ፡ ሚስቱ ፡ እንደነገረችው ፡ እኩሌታውን ፡ ገንዘብ ፡ ለቤተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰጠ ።
፹፰ ፤ ዳግመኛ ፡ ወንዶችንም ፡ ሴቶችንም ፡ባሮቹን ፡ ጠርቶ ፡ እንደዚህ ፡ አላቸው ።
፹፱ ፤ ወደ ወደዳችሁበት ፡ ሂዱ ።
፺ ፤ ስለእግዚአብሔር ፡ ብዬ ፡ ከመገዛት ፡ የወጻችሁ ፡ ሁኑ ፡ (ነጻ ፡ አውጥቻችኋለሁ ።
፺፩ ፤ እሱም ፡ እኔንም ፡ ሚስቴንም ፡ ከዲቢሎስ ፡ መገዛት ፡ ነጻ ፡ ያደርገን ፡ ዘንድ ።
፺፪ ፤ ወንዶች ፡ ሴቶችም ፡ ባሮቹ ፡ እንዲህ ፡ ባላቸው ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ አዘኑ ።
፺፫ ፤ ጌታችን ፡ ምን ፡ አደረግንህ ።
፺፬ ፤ አባታችን ፡ ሆይ ፡ የሚያስቆጣህ ፡ የሚያሳዝንህ ፡ ሥራ ፡ ምን ፡ ሠራን ።
፺፭ ፤ ብንበድልህም ፡ እነሆ ፡ አለንጋ ፡ ጅራፍ ፡ በፊትህ ፡ አለ ፡ ግረፈን ፡ እንገረፋለን ።
፺፮ ፤ ጸጋ ፡ ዘአብም ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ።
፺፯ ፤ ያሳዘናችሁኝም ፡ ነገር ፡ የለ ።

፳፰ ፤ **እግዚአብሔር** ፡ ይባርክ ፡ ላዕሌክሙ ፡ በበ
ረከተ ፡ አበውየ ፡ ካህናት ፡ እለ ፡ ቅድሜሁ፡
በጽድቅ ፡ ወበርትዕ ።
፳፱ ፤ እመኒ ፡ ፈቀድክሙ ፡ ትንበሩ ፡ በቤትየ
ንበሩ ፡ ከመ ፡ ልደ ፡ ቤት ።
፴ ፤ ኢ ይ በ ሉ ክ ሙ ፡ አ ግ ብ ር ት ፡
ወአዕማት ።
፴፩ ፤ ለአግብርት ፡ ይበሉክሙ ፡ አርካኒሁ ፡ **ለጸጋ
ዘአብ** ።
፴፪ ፤ ወለአዕማት ፡ ይቤሉክን ፡ አዕርክቲሃ ፡
**ለእግዚእ ፡ ሐረያ** ።
፴፫ ፤ ወሰሚያሙ ፡ አግብርት ፡ ወአእማት ፡ ተፈ
ሥሁ ፡ ወሰዓሙ ፡ እደዊሁ ፡ ወእገሪሁ ።
፴፬ ፤ ወነበሩ ፡ ምስሌሁ ፡ ብዙኃ ፡ መዋዕለ ፡ አዕ
ማት ፡ ኮነ ፡ በዓልታተ ፡ ቤት ፡ ወአግብ
ርት ፡ ኮኑ ፡ አግዓዚያነ ።

## **ምዕራፍ ፡ ፲**

፩ ፤ ወእንዘ ፡ ሀለው ፡ ከመዝ ፡ ተንሥአ ፡ ፩ ፡
ዕልው ፡ ገብር ፡ ዘስሙ ፡ ሞተሎሚ ።
፪ ፤ ወስማ ፡ ለእሙ ፡ እስላደኒ ።
፫ ፤ ወነግሠ ፡ በፈቃዱ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ በሐው
ርት ፡ ዳሞት ፡ ወበሐውርተ ፡ ሸዋ ።
፬ ፤ እስከ ፡ ወሰነ ፡ አምሐራ ፡ ኅበ ፡ ፈለገ
ዐባይ ፡ እንተ ፡ ትሰመይ ፡ ዠማ ።
፭ ፤ ወነሠተ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ።
፮ ፤ ወሰገደ ፡ ለጣዖት ።
፯ ፤ እንዘ ፡ ይብል ፡ አንትሙ ፡ ፈጠርክሙኒ ።
፰ ፤ ወአንትሙ ፡ ኃይልየ ፡ በውስተ ፡ ጸብእ ።
፱ ፤ ወአማሰነ ፡ ኵሎ ፡ ሕገ ፡ **እግዚአብሔር** ።
፲ ፤ ወለስዩማን ፡ ሸዋ ፡ ይብሎሙ ፡ አምጽኡ ፡
አንስቲያክሙ ፡ ከመ ፡ አውስቦን ።
፲፩ ፤ ወይፌንው ፡ ሎቱ ፡ በበዕሬብቶሙ ፡ ፈሪ
ሆሙ ፡ ከመ ፡ ኢይቀትሎሙ ።
፲፪ ፤ እስመ ፡ ምሁረ ፡ ጸብዕ ፡ ውእቱ ፡ ከመ ፡
ሰብአ ፡ ቅንስጥቂስ ።
፲፫ ፤ ወበእንተዝ ፡ ነግሠ ፡ ላዕሌሆሙ፡ በኵናት ።
፲፬ ፤ ወደናግልሂ ፡ ኢተርፋ ፡ በመዋዕሊሁ ።
፲፭ ፤ እስመ ፡ ያመጽኡ ፡ ሎቱ ፡ ዘተረክበት ፡
ድንግልተ ፡ ወያማስን ፡ ድንግልናሃ ።
፲፮ ፤ ወእምነ ፡ ምህርካሂ ፡ ዘተረክበት ።
፲፯ ፤ ድንግልተ ፡ ያመጽኡ ፡ ሎቱ ፡ ኪያሃ ፡
ወያማስና ።
፲፰ ፤ ርኩስ ፡ ውእቱ ፡ በኵሉ ፡ ፍናዊሁ ።
፲፱ ፤ ወጽሉዕ ፡ በኵሉ ፡ ምግባሩ ።
፳ ፤ ወበውእቱ ፡ መዋዕል ፡ በጽሐ ፡ ምድረ ፡
ጽላልሽ ።
፳፩ ፤ ወአገታ ፡ በምድረ ፡ ዞረሬ ።

፳፰ ፤ ቢውነት ፡ ከፊቱ ፡ ቆመው ፡ የሚያገለግ
ሉት ፡ በካህናት ፡ በአባቶቼ ፡ በረከት ፡ **እግ
ዚአብሔር** ፡ ይባርካችሁ ።
፳፱ ፤ ከኔም ፡ ቤት ፡ ልትኖሩ ፡ ብትወዱ ፡ እን
ደቤት ፡ ልጅ ፡ ሆናችሁ ፡ ኑሩ ።
፴ ፤ ባሮች ፡ አይበሏችሁ ።
፴፩ ፤ ወንዶችንም ፡ **የጸጋ ፡ ዘአብ** ፡ ወዳጆች ።
፴፪ ፤ ሴቶችንም ፡ **የእግዚእ ፡ ሐረያ** ፡ ባለሟሎች፡
ይበሏችሁ ።
፴፫ ፤ እንዲህ ፡ ባላቸው ፡ ጊዜ ፡ ሴቶቹም ፡ ወን
ዶቹም ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ እጁን፡እግሩን ፡
ሳሙት ።
፴፬ ፤ ወንዶቹም ፡ ሴቶቹም ፡ እንደባለቤት ፡
ነጻ ፡ ሆነው ፡ ከርሱ ፡ ጋር ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡
ተቀመጡ ።

## **ዐሥረኛ ፡ ምዕራፍ ፡**

፩ ፤ እንደዚህ ፡ ሲኖሩ ፡ ሞተሎሚ ፡ የሚባል ፡
አንድ ፡ ከሃዲ ፡ ተነሥቶ ።
፪ ፤ እናቱም ፡ እስላደኒ ፡ ትባላለች ።
፫ ፤ በሸዋ ፡ አውራጃና ፡ በዳሞት ፡ አውራጃ ፡
በኃይሉ ፡ ነገሠ ።
፬ ፤ ያማራ ፡ ወሰን ፡ እስከምትሆን ፡ እስከ ፡
ዠማ ፡ ድረስ ።
፭ ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ አቃጥሎ ።
፮ ፤ ለጣዖትም ፡ ሰገደ ።
፯ ፤ የፈጠራችሁኝ ፡ እናንተ ፡ ናችሁ ፡ ብሎ ፤
፰ ፤ በሰልፍ ፡ ጊዜም ፡ ድል ፡ እንዳደርግ ፡ የም
ታደርጉኝ ፡ ብሎ ።
፱ ፤ **የእግዚአብሔርን** ፡ ሕግ ፡ ሁሉ ፡ አጠፋ ።
፲ ፤ የሸዋን ፡ መኳንንት ፡ ሁሉ ፡ ሴቶቻችሁን፡
አምጡልኝ ፡ አገባቸው ፡ ዘንድ ፡ ይላቸው፡
ነበር ።
፲፩ ፤ እነሱም ፡ እንዳይገድላቸው ፡ ፈርተው ፡
በፈረቃ ፡ ይልኩለት ፡ ነበር ።
፲፪ ፤ እንደቅንስጥቂስ ፡ ሰዎች ፡ ሰልፍ ፡ የተ
ማረ ፡ ነበርና ።
፲፫ ፤ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ በጦር ፡ (በኃይል) ፡ ነገሠ
ባቸው ።
፲፬ ፤ በዘመኑ ፡ ደናግልም ፡ አልቀሩት ።
፲፭ ፤ በድንግልና ፡ የተገኘችይቱን ፡ እየወሰዱ፡
እየሰጡት ፡ ከክብር ፡ ያሳንሳት ፡ ነበርና ።
፲፮ ፤ ከምርኮም ፡ ውስጥ ፡ ድንግል ፡ የተገኘች ፡
እንደሆነ ።
፲፯ ፤ ይዘው ፡ እየሰጡ ፡ ከክብር ፡ ያሳነሳት ፡
ነበር ።
፲፰ ፤ በሥራው ፡ ሁሉ ፡ የሚያጸይፍ ፡ ነው ።
፲፱ ፤ በሥራው ፡ ሁሉ ፡ የተጠላ ፡ ነው ።
፳ ፤ በዚያም ፡ ወራት ፡ ጽላልሽ ፡ አውራጃ ፡
ደረሰ ።
፳፩ ፤ ዞረሬን ፡ ከቧት ፡ ሠፈረ ።

፷፪ ፤ ወነጸረ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ እንዘ ፡ የዐግትዋ ፡ ለሀገር ።
፷፫ ፤ ወአእመረ ፡ ከመ ፡ ውእቱ ፡ ዕልው ፡ መጽአ ፡ ከመ ፡ ይቅትሎ ።
፷፬ ፤ ወጐየ ፡ ፍጡነ ፡ እምኔሁ ፡ እንተ ፡ ካልዕ ፡ ፍኖት ።
፷፭ ፤ ወሮጸ ፡ ፩ ፡ ሐራዊ ፡ እምነ ፡ ሐራሁ ፡ ለሞተለሚ ።
፷፮ ፤ እንዘ ፡ ይጼዓን ፡ ፈረሰ ፡ ወዴገኖ ፡ ለጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ከመ ፡ ይቅትሎ ።
፷፯ ፤ ወደርበየ ፡ ኲናቶ ፡ ላዕሌሁ ፡ ወኢረከቦ ።
፷፰ ፤ ወሶበ ፡ ፈቀደ ፡ ከመ ፡ ይደርቢ ፡ ካልዕተ ፡ ኲናቶ ፡ ተጣበቀት ፡ ኲናት ፡ ምስለ፡እራኊ።
፷፱ ፤ ወኢተክህሎ ፡ ይደርቢ ፡ ላዕሌሁ ።
፸ ፤ ወእንዘ ፡ ይዴግኖ ፡ ሐራዊ ፡ በጽሐ ፡ ጸጋ፡ ዘአብ ፡ ኀበ ፡ ቀላየ ፡ ማይ ፡ ወተወረወ ፡ ከመ ፡ እብን ።

፸፩ ፤ ወዘንተ ፡ ርእዮ ፡ ሐራዊ ፡ ቆመ ፡ በድንጋገ፡ ፈለግ ፡ ንስቲተ ።
፸፪ ፤ ከመ ፡ ይርአይ ፡ ለእመ ፡ ይወፅእ ፡ ጸቢቶ ፡ እምቀላየ ፡ ባሕር ።
፸፫ ፤ ወሶበ ፡ ኢወፅአ ፡ ውእቱ ፡ ተመይጠ ፡ ውስተ ፡ ሀገር ።
፸፬ ፤ ከመ ፡ ይማህርክ ፡ ጼዋ ፡ ዘረከበ ።
፸፭ ፤ ወጸጋ ፡ ዘአብሰ ፡ ካህን ፡ ንጹሕ ፡ በዊአ ፡ ውስተ ፡ ቀላየ ፡ ባሕር ፡ ኢርእየ ፡ ሙስና።

፸፮ ፤ አላ ፡ ኮነት ፡ ሎቱ ፡ ይእቲ ፡ ቀላይ ፡ ከመ ፡ ሐይመት ፡ እንተ ፡ ድሉት ፡ ለማኅደር ።
፸፯ ፤ እስመ ፡ ሚካኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡ የአቅቦ ።

፸፰ ፤ ወአሚሃ ፡ በዓሉ ፡ ውእቱ ፡ ለቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ አመ ፡ ፲ወ፪ ፡ ለወርኃ ፡ መጋቢት ።
፸፱ ፤ ወባሕቱ ፡ ውእቱ ፡ ኢየሬእዮ ።
፹ ፤ አላ ፡ ኮነ ፡ ይኬልህ ፡ ውስተ ፡ ባሕር ፡ ወይብል ።
፹፩ ፤ አ ፡ ሚካኤል ፡ ኃይልየ ።
፹፪ ፤ አ ፡ ሚካኤል ፡ ጸወንየ ።

፹፫ ፤ አይቴ ፡ ሀሎ ፡ ኃይልከ ፡
፹፬ ፤ አይቴ ፡ ሀሎ ፡ ጽንዕከ ።
፹፭ ፤ ወአይቴ ፡ ሀሎ ፡ ተአምሪከ ።
፹፮ ፤ ናሁ ፡ በጽሐ ፡ ላዕሌየ ፡ ሞት ።
፹፯ ፤ ዮም ፡ ዕለተ ፡ ምምዓ ።
፹፰ ፤ ዮም ፡ ዕለተ ፡ ምንዳቤ ።
፹፱ ፤ ዮም ፡ ምንሳዌ ፡ ኮነ ፡ ላዕሌየ ።
፺ ፤ በበዓልከኑ ፡ እምታስተፍሥሐኒ፡ተ ኀዝነኒኑ።

፺፩ ፤ ዘንተ ፡ ወዘይመስሎ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ይበኪ ወያስቈቊ ፡ ከመ ፡ ሕፃን ፡ ዘአኅደግዎ ፡ ጥበ ፡ እሙ ።
፺፪ ፤ ወያወኀዛ ፡ አዕይንቲሁ ፡ አንብዓ ፡ ውኁየ ።

፷፪ ፤ ጸጋ ፡ ዘአብም ፡ ሀገሩን ፡ ሲከቧት ፡ አይቶ ።
፷፫ ፤ ይህ ፡ ከሃዲ ፡ ሊገለው ፡ እንደመጣ ፡ ዐወቀ ።
፷፬ ፤ በሌላ ፡ ጐዳና ፡ ፈጥኖ ፡ ሸሸ ።
፷፭ ፤ ከሞተለሚ ፡ ጭፍራ ፡ አንዱ ፡ ፈጥኖ ፡ ተከተለው ።
፷፮ ፤ ጸጋ ፡ ዘአብን ፡ ሊገለው ፡ በፈረስ ፡ ተከተለው ።
፷፯ ፤ ጦሩን ፡ ወረወረበት ፡ አላገኘውም ።
፷፰ ፤ ሁለተኛ ፡ ጦሩን ፡ ሊወረውርበት ፡ ወዶ ፡ ሳለ ፡ ጦሩ ፡ ከጁ ፡ ጋራ ፡ ተጣብቃ ፡ ቀረች ።
፷፱ ፤ ለመወርወር ፡ አልተቻለውም ።
፸ ፤ ጸጋ ፡ ዘአብም ፡ ወታደሩ ፡ ሲከታተለው ፡ ከጥልቅ ፡ ባሕር ፡ ደርሶ ፡ እንደደንጊያ ፡ ተወርውሮ ፡ ጠለቀ ።

፸፩ ፤ ወታደሩም ፡ ይህን ፡ አይቶ ፡ ከወንዙ ፡ ዳር ፡ ጥቂት ፡ ቁሞ ፡ ጠበቀው ።
፸፪ ፤ ከውኀው ፡ ውስጥ ፡ ዋኝቶ ፡ (ምንአልባት ፡) የወጣ ፡ መስሎት ።
፸፫ ፤ እንዳልወጣለት ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ወደመንደር ፡ ተመለሰ ።
፸፬ ፤ ያገኘውን ፡ ይማርክ ፡ ዘንድ ።
፸፭ ፤ ንጹሕ ፡ አገልጋይ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ግን ፡ ከጥልቅ ፡ ባሕር ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ጉዳት ፡ አላገኘውም ።
፸፮ ፤ ይች ፡ ባሕር ፡ ለማደሪያ ፡ እንደተዘጋጀች፡ ድንኳን ፡ ሆነችለት ፡ እንጂ ።
፸፯ ፤ የመላእክት ፡ አለቃ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ይጠብቀዋልና ።

፸፰ ፤ ያንጊዜ ፡ በመጋቢት ፡ ዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ የቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ በዓል ፡ ነበር ።
፸፱ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እሱ ፡ አያየውም ።
፹ ፤ ከባሕር ፡ ውስጥ ፡ ሆኖ ፡ እንዲህ ፡ እያለ ፡ ይጮህ ፡ ነበር ፡ እንጂ ።
፹፩ ፤ ኃይል ፡ የምትሆነኝ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ።
፹፪ ፤ አምባ ፡ (መጸጊያ ፡ የምትሆነኝ ፡) ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ እያለ ፡ ይጮህ ፡ ነበር ፡ እንጂ ።
፹፫ ፤ ኃይልህ ፡ ወዴት ፡ ነው ።
፹፬ ፤ ከሃሊነትህ ፡ ወዴት ፡ ነው ።
፹፭ ፤ ተአምራት ፡ ማድረግህ ፡ ወዴት ፡ ነው ።
፹፮ ፤ እነሆ ፡ መሞቻዬ ፡ ደረሰ ።
፹፯ ፤ ዛሬ ፡ የሽብር ፡ ቀን ፡ ነው ።
፹፰ ፤ ዛሬ ፡ የመከራ ፡ ቀን ፡ ነው ።
፹፱ ፤ ዛሬ ፡ ጥፋት ፡ ተፈረደብኝ ።
፺ ፤ በበዓልህ ፡ ደስ ፡ ሳታሰኘኝ ፡ ታሳዝነኛለህን ።
፺፩ ፤ ይኸንና ፡ ይህንን ፡ የመሰለ ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ እያለ ፡ የናቱን ፡ ጡት ፡ እንዳስጣሉት ፡ ልጅ ፡ ያለቅስ ፡ ነበር ።
፺፪ ፤ እየተናደደ ፡ ያለቅስ ፡ ነበር ።

፶፫ ፤ ወውእተ ፡ ጊዜ ፡ አስተርአዮ ፡ ሚካኤል ፡ 
ገሃደ ።
፶፬ ፤ ወይቤሎ ፡ አ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ምንት ፡ ያበክየከ ።
፶፭ ፤ ናሁ ፡ አነ ፡ ሚካኤል ፡ አዓቅበከ ፡ ኢትፍ
ራህ ፡ ሀለውኩከ ፡ አነ ።
፶፮ ፤ ሶበሰ ፡ አድኃንኩከ ፡ እምሐራዊ ፡ በውስተ ፡ 
መርህብ ፡ እምኢተአንከረ ፡ ኃይልየ ፡ በላዕ
ሌከ ።
፶፯ ፤ አላ ፡ ሶበ ፡ አውጻኩከ ፡ ዳኅነ ፡ እምተሰ
ጥሞ ፡ ባሕር ።
፶፰ ፤ አኮ ፡ በእንቲአከ ፡ ባሕቲቱ ፡ ዘአድኀንኩከ ።
፶፱ ፤ አላ ፡ በእንተ ፡ ወልድ ፡ ኅሩይ ፡ ዘሀሎ ፡ 
ውስተ ፡ ሐቌከ ።
፷ ፤ ወውእቱ ፡ ይከውን ፡ ብርሃነ ፡ ለኵሉ ፡ ዓለም ።

፷፩ ፤ ወይከውን ፡ በኵሉ ፡ ግዕዙ ፡ ከማየ ።
፷፪ ፤ ወአነ ፡ አዓቅቦ ፡ ወሊተ ፡ ውእቱ ፡ መክ
ፈልትየ ።
፷፫ ፤ ወበእንቲአሁ ፡ ትድኅን ፡ እሞት ።
፷፬ ፤ ወብዙኃ ፡ ነገራተ ፡ ወልድ ፡ እንዘ ፡ ይነ
ግሮ ፡ ቤተ ፡ ወወዓለ ፡ በከርሠ ፡ ባሕር ፡ 
፫ ፡ መዓልተ ፡ ወ፫ ፡ ሌሊተ ።
፷፭ ፤ ወእምድኅረዝ ፡ ይቤሎ ፡ ሚካኤል ፡ 
ለቅዱስ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ።
፷፮ ፤ ናሁ ፡ ኃለፈ ፡ ዕለተ ፡ ጕዕትያ ፡ ወገፍታ
ዔሂ ፡ ነዓ ።
፷፯ ፤ ፃእ ፡ ውእተ ፡ ጊዜ ፡ መጠቆ ፡ በእዴሁ ፡ 
ወአውፅአ ፡ እምባሕር ።
፷፰ ፤ ወአብአ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ 
ዘዞረሬ ።
፷፱ ፤ ወተሰወረ ፡ እምኔሁ ።
፸ ፤ ወረከበ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ኮነት ፡ ሀገሩ ፡ ብዱተ ።
፸፩ ፤ ወተመዝበረት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንሂ ፡ ወአ
ብያተ ፡ ሰብእሂ ፡ ኵሎን ፡ ተመዝበራ ።
፸፪ ፤ ወጸንዓ ፡ ላዕሌሁ ፡ ብካይ ፡ እምዘቀዳሚ ።
፸፫ ፤ ሰብአ ፡ ሀገርሂ ፡ ተጼወው ፡ ወእንስሳሂ ፡ 
ኢተርፈ ።
፸፬ ፤ ወብእሲቱሂ ፡ ተጼወወት ፡ ምስሌሆሙ ፡ 
በይእቲ ፡ ዕለት ።
፸፭ ፤ አመ ፲ወ፪ ፡ ለመጋቢት ።
፸፮ ፤ ወባሕቱ ፡ ኅዳጣን ፡ ሰብእ ፡ እለ ፡ ተርፉ ፡ 
እምዔዋዌ ፡ ተኃቢኦሙ ፡ ውስተ ፡ ግበብ 
ወጸላዕት ፡ መጽኡ ፡ ኀቤሁ ፡ ከመ ፡ ይብ
ክዩ ፡ ምስሌሁ ፡ በእንተ ፡ ጥፍአተ ፡ ሀገሮሙ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፩ ።

፩ ፤ ወለእግዚእ ፡ ሐረያስ ፡ አመ ፡ ጼወውዋ ፡ 
ነሥእዋ ፡ ሐራ ፡ ሠገራት ።
፪ ፤ ወወሰድዋ ፡ በዓቢይ ፡ ወክብር ።
፫ ፤ እንዘ ፡ ይብሉ ፡ ትከውኖ ፡ ብእሲተ ፡ ለእ
ግዚእነ ፡ ንጉሥ ።
፬ ፤ እስመ ፡ ጥቀ ፡ ላህይት ፡ ብእሲት ፡ ይእቲ ።

፶፫ ፤ ያንጊዜ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ተገልጾ ፡ ታየው ።

፶፬ ፤ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ምን ፡ ያስለቅስሐል ።
፶፭ ፤ እነሆ ፡ እኔ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ እጠብ
ቅሃለሁ ፡ እኔ ፡ አለሁ ፡ አትፍራ ።
፶፮ ፤ ከሜዳ ፡ ሳለህ ፡ ከዚያ ፡ ከወታደር ፡ አላ
ዳንሁህ ፡ ቢሆን ፡ ተአምራቴ ፡ ባልተደነ
ቀም ፡ ነበር ።
፶፯ ፤ ከባሕር ፡ ውስጥ ፡ ሳለህ ፡ አድኜ ፡ ባወጣ
ሁህ ፡ ጊዜ ፡ ተአምራቴ ፡ ይደነቃል ፡ እንጂ ።
፶፰ ፤ የማድንህም ፡ ስላንተ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።
፶፱ ፤ በአብራክህም ፡ ስላለ ፡ ስለተመረጠ ፡ 
ልጅህ ፡ ነው ፡ እንጂ ።
፷ ፤ እሱም ፡ ለዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ ብርሃን ፡ ይሆ
ናል ።
፷፩ ፤ በሥራው ፡ ሁሉ ፡ እንደኔ ፡ ይሆናል ።
፷፪ ፤ እኔም ፡ እጠብቀዋለሁ ፡ እሱም ፡ ለኔ ፡ 
እድል ፡ (ፈንታዬ ፡) ነው ።
፷፫ ፤ ስለሱ ፡ ከሞት ፡ ትድናለህ ።
፷፬ ፤ ብዙ ፡ የልጁን ፡ ነገር ፡ እየነገረው ፡ በባ
ሕር ፡ ውስጥ ፡ ሦስት ፡ መዓልት ፡ ሦስት ፡ 
ሌሊት ፡ ውሎ ፡ አደረ ።
፷፭ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ጸጋ ፡ 
ዘአብን ፡ እንዲህ ፡ አለው ።
፷፮ ፤ እነሆ ፡ የጥፋት ፡ ቀን ፡ አለፈ ፡ ና ፡ ውጣ ፡ 
አለው ።
፷፯ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ በጁ ፡ መጥቶ ፡ ከባሕር ፡ አወ
ጣው ።
፷፰ ፤ በዞረሬ ፡ ወዳለች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ 
ወስዶ ፡ አገባው ።
፷፱ ፤ ከሱ ፡ ተሰወረ ፤
፸ ፤ አገሩን ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ሆና ፡ አገኛት ።
፸፩ ፤ ቤተ ፡ ክርስቲያኑም ፡ የሰውም ፡ ቤት ፡ 
ሁሉ ፡ ፈርሶ ፡ አገኘው ።
፸፪ ፤ ከቀደመው ፡ ይልቅ ፡ ኀዘን ፡ ጸናበት ።
፸፫ ፤ ሰውም ፡ ከብቱም ፡ ተማረከ ።

፸፬ ፤ በዚያች ፡ ቀን ፡ ሚስቱም ፡ ተማርካ ፡ ሄደች ።

፸፭ ፤ በመጋቢት ፡ በዐሥራ ፡ ሁለት ፡ ቀን ።
፸፮ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በዱር ፡ በገደል ፡ ተሰውረው 
ከምርኮ ፡ የቀሩ ፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ስለሀገ
ራቸው ፡ ጥፋት ፡ ከሱ ፡ ጋራ ፡ ይላቀሱ ፡ 
ዘንድ ፡ ወደሱ ፡ መጡ ።

## ዐሥራ ፡ አንድ ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ እግዚእ ፡ ሐረያን ፡ ግን ፡ እኒህ ፡ የወታደር ፡ 
ጭፍሮች ፡ በማረኳት ፡ ጊዜ ።
፪ ፤ አክብረው ፡ ይዘዋት ፡ ሄዱ ።
፫ ፤ ለጌታችን ፡ ለንጉሡ ፡ ሚስት ፡ ትሆነዋለች ፡ 
ብለው ።
፬ ፤ እጅግ ፡ መልከ ፡ መልካም ፡ ነበረችና ።

፭ ፤ ድምድማሃ ፡ ድሉል ።
፮ ፤ ወቆናዝኢሃ ፡ ፍቱል ።
፯ ፤ አዕይንቲሃ ፡ ይመስል ፡ ከመ ፡ ስርቀተ ፡ ቤዝ ።
፰ ፤ ወከሣዳ ፡ ከመ ፡ አርማስቆስ ፡ መኃልይ ።

**ም ፡ ፭ ፡ ቁ ፡ ፱ ።**

፩ ፤ ወኵለንታሃ ፡ አዳም ።
፲ ፤ አልቦ ፡ ሕስም ፡ እምርእሳ ፡ እስከ ፡ እግራ።
፲፩ ፤ ወሶበ ፡ ርእዩ ፡ ዘከመዝ ፡ ብእሲተ ፡ ነደ ፡ ልቦሙ ፡ ለሐራ ፡ ሠገራት ፡ እምብዝኃ ፡ ፍቅራ ።
፲፪ ፤ ቦ ፡ ዘይቤ ፡ አነ ፡ አዓቅባ ።
፲፫ ፤ ወቦ ፡ ዘይቤ ፡ አነ ፡ እጸውራ ።
፲፬ ፤ ወቦ ፡ ዘይቤ ፡ አነ ፡ እጼዕን ፡ ውስተ ፡ በቅልየ ።
፲፭ ፤ ወቦ ፡ ዘይቤ ፡ አነ ፡ እከድና ፡ በልብስየ ።
፲፮ ፤ ወእሉ ፡ ኵሎሙ ፡ ይትዋከሁ ፡ ዘዘዚአሆሙ ለፍትወቶሙ ።
፲፯ ፤ ወባሕቱ ፡ **ሚካኤል** ፡ ዘየዓቅባ ፡ ይከልዖሙ ከመ ፡ ኢያርኩስዋ ፡ ለቅድስት ።
፲፰ ፤ ወነገርዎ ፡ ለሞተለሚ ።
፲፱ ፤ ወይቤልዎ ፡ ብሥራት ከ ፡ አ ፡ ንጉሥ ፡ ረከብነ ፡ ብእሲተ ፡ አልቦ ፡ ዘይትማሰላ ።
፳ ፤ ወኢይትረከብ ፡ ዘከማሃ ፡ ዘኵሉ ፡ አብያተ፡ ነገሥት ።
፳፩ ፤ ለእመ ፡ አውሰብከ ፡ ኪያሃ ፡ ይሰግዱ ፡ ለከ፡ ኵሎሙ ፡ አጽናፈ ፡ ምድር ።
፳፪ ፤ ወይቤሎሙ ፡ በፍሥሐ ፡ እምአይቴ ፡ ረከብክምዋ ።
፳፫ ፤ ወይቤልዎ ፡ ዮም ፡ ጼወውናሃ ፡ ምስለ ፡ ሰብአ ፡ ሀገር ።
፳፬ ፤ ሶበ ፡ ርኢናሃ ፡ ከመ ፡ ጥቀ ፡ ሠናይት ፡ ይእቲ ፡ አምጻእናሃ ፡ ኀቤከ ።
፳፭ ፤ ከመ ፡ ትረስያ ፡ ብእሲት ።
፳፮ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ዕቀብዋ ፡ ሊተ ፡ በሠናይ ፡ ዕቅበት ።
፳፯ ፤ ወአኅድርዋ ፡ ውስተ ፡ ሠናይ ፡ ማኅደር ።
፳፰ ፤ ወኢይርአይ ፡ ገጻ ፡ መኑሂ ፡ እምሰብእ ፤
፳፱ ፤ ወአልብስዋ ፡ አልባስ ፡ ክቡራተ ፡ ዘሜላት።
፴ ፤ ወዘሲራይ ።
፴፩ ፤ ዘቢሶስ ፡ ወዘነት ።
፴፪ ፤ ዘተአንሙ ፡ በወርቅ ፡ ወበብሩር ፡ ወሀቦሙ ።
፴፫ ፤ ወይቤሎሙ ፡ በዝኵሉ ፡ አራዛተ ፡ ሰርጉ፡ አስተረስየክሙ ፡ ጊሠመ፡ አምጽእዋ ፡ ኀቤየ።
፴፬ ፤ ወተአዚዞሙ ፡ እምኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ዘንተ ፡ ኵሎ ፡ ሖሩ ፡ ሐራ ፡ ሠገራት ፡ ኀበ ፡ ቅድስት ፡ **እግዚእ ፡ ሐረያ** ።

፭ ፤ ቁንዳላዋ ፡ የተከፈከፈ ።
፮ ፤ የተጠቀለለ ፡ ነውና ። ብርንጉዋ ፡ የተፈተለ ፡ ነው ፤
፯ ፤ ዓይኖቿም ፡ እንደ ፡ ኢጥቢያ ፡ ኮከብ ፡ ናቸውና ።
፰ ፤ አንገቷም ፡ እንደብር ፡ ዘንግ ፡ ነው ።

**አምስተኛ ፡ ምዕራፍ ፡ ቁ ፡ ፱ ።**

፩ ፤ ሁለንተነዋ ፡ ያማረ ፡ ነው ።
፲ ፤ ከእግሯ ፡ እስከ ፡ ራሷ ፡ ድረስ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ የለባትም ።
፲፩ ፤ እሊህም ፡ ወታደሮች ፡ እንዲህ ፡ ያለች ፡ ሁና ፡ ባዩዋት ፡ ጊዜ ፡ በፍቅሯ ፡ ልቡናቸው ነደደ ።
፲፪ ፤ አንዱ ፡ እኔ ፡ እጠብቃታለሁ ፡ ይላል ።
፲፫ ፤ አንዱም ፡ እሸከማታለሁ ፡ ይላል ።
፲፬ ፤ በበቅሎየ ፡ አስቀምጣታለሁ ፡ የሚል ፡ አለ ።
፲፭ ፤ አንዱም ፡ እኔ ፡ ልብሴን ፡ አለብሳታለሁ ፡ ይላል ።
፲፮ ፤ እሊህ ፡ ሁሉ ፡ በፈቃዳቸው ፡ እየራሳቸው ፡ ይፈካከራሉ ።
፲፯ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ የሚጠብቃት ፡ **ቅ/ ሚካኤል** ፡ ክብርት ፡ እሷን ፡ እንዳያረክሷት ፡ ይከለክላቸዋል ።
፲፰ ፤ ሄደው ፡ ለሞተለሚ ፡ ነገሩት ።
፲፱ ፤ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ የምሥራች ፡ ምሳሌ ፡ የሌላት ፡ ሴት ፡ አገኘንልህ ።
፳ ፤ በቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሁሉ ፡ እንደሷ ፡ ያለ፡ አይገኝም ።
፳፩ ፤ እሷን ፡ ብታገባ ፡ ዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ ይሰግድልሃል ።
፳፪ ፤ ደስ ፡ ብሎት ፡ ከወዴት ፡ አገኛችኋት ፡ አላቸው ።
፳፫ ፤ ዛሬ ፡ ከሀገሩ ፡ ሰው ፡ ጋራ ፡ ማረክናት ።
፳፬ ፤ እጅግ ፡ መልከ ፡ መልካም ፡ እንደሆነች ፡ አይተን ፡ ወደ ፡ አንተ ፡ አመጣናት ።
፳፭ ፤ ሚስት ፡ ታደርጋት ፡ ዘንድ ።
፳፮ ፤ አክብራችሁ ፡ ጠብቁልኝ ።
፳፯ ፤ ከደኅና ፡ ቦታ ፡ አሳድሩዋት ።
፳፰ ፤ ከሰው ፡ ወገን ፡ ማንም ፡ እንዳያያት ።
፳፱ ፤ በነጭ ፡ ሐር ፡ የተሠራ ።
፴ ፤ አረንጓዴ ።
፴፩ ፤ አበባ ፡ ግምጃ ።
፴፪ ፤ በወርቅ ፡ በብር ፡ የተሠራ ፡ ልብስ ፡ አልብሷት ፡ ብሎ ፡ ሰጣቸው ።
፴፫ ፤ በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጌጽ ፡ አስጊጣችሁ ፡ ነገ ፡ ወደኔ ፡ አምጧት ፡ አላቸው ።
፴፬ ፤ ወታደሮቹም ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ ከንጉሡ ፡ ታዘው ፡ ወደክብርት ፡ **እግዚእ ፡ ሐረያ** ፡ ሄዱ ።

፴፭ ፤ ወበጺሖሙ ፡ ኀቤሃ ፡ ይቤልዋ ፡ በሐ ፡ ይቤለኪ ፡ ንጉሥ ።
፴፮ ፤ ወሀብዋ ፡ አሎንተ ፡ አልባሳተ ።
፴፯ ፤ ወአሰርገውዋ ፡ ቦቱ ።
፴፰ ፤ ወአዕነቅዋ ፡ ባዝግና ፡ ወርቅ ።
፴፱ ፤ ወወደዩ ፡ አውቃፋተ ፡ ወርቅ ፡ ውስተ ፡ እዕዳዊሃ ።
፵ ፤ ወኀልቀታተ ፡ ወርቅ ፡ ውስተ ፡ አፃብኢሃ።
፵፩ ፤ ወአሳዕነ ፡ ወርቅ ፡ ውስተ ፡ አዕጋሪሃ ።
፵፪ ፤ ወአስተሰረይዋ ፡ በኵሉ ፡ ዕበይ ፡ ወክብር ፡ በከመ ፡ ሕጎን ፡ ለንግሥታት ።
፵፫ ፤ ወይእቲሰ ፡ ኮነት ፡ ትቴክዝ ፡ ወአንብዐ ፡ ታንጠበጥብ ፡ ዲበ ፡ ምድር ።
፵፬ ፤ ወኢታነሥእ ፡ አዕይንቲሃ ፡ ላዕለ ።
፵፭ ፤ ዳዕሙ ፡ ኵሎ ፡ ጊዜ ፡ ድንንት ፡ ውስተ ፡ ምድር ።
፵፮ ፤ ወሕሊናሃ ፡ እንቅዕድው ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ፤
፵፯ ፤ ወሶበ ፡ ርእይዋ ፡ ሐራ ፡ እንዘ ፡ ትቴክዝ ፡ ጥቀ ።
፵፰ ፤ ይቤልዋ ፡ አ ፡ ብእሲቶ ፡ ምንተ ፡ ያበክየኪ ፤
፵፱ ፤ እስመ ፡ ናሁ ፡ ኮንኪ ፡ ንግሥተ ።
፶ ፤ ወዘንተ ፡ ብሂሎሙ ፡ ነሥእዋ ፡ ወወሰድዋ፡ ወአብዕዋ ፡ ውስተ ፡ ርሱይ ፡ ቤት ፡ ከመ ፡ ያኀድርዋ ።
፶፩ ፤ ወአምጽኡ ፡ ላቲ ፡ መባልዕተ ፡ ጥዑማተ ፡ ዘዘዚአሆሙ ፡ ግዕዞሙ ።
፶፪ ፤ ወዘዘዚአሆሙ ፡ ጣዕሞሙ ።
፶፫ ፤ ወይቤልዋ ፡ ንሥኢ ፡ ብልዒ ፡ ይቤለኪ ፡ ንጉሥ ።
፶፬ ፤ ወይእቲሰ ፡ ኢተወክፈቶሙ ፡ ወኢበልዓት ፡ እማዕዶሙ ።
፶፭ ፤ ባሕቱ ፡ ኮነት ፡ ትግዕር ፡ ኀበ ፡ እምላክ ፡ እንዘ ፡ ትብል ፤
፶፮ ፤ አ ፡ እግዚእየ ፡ ወአምላኪየ ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለምንት ፡ ርኢከ ፡ ዕበድየ ።
፶፯ ፤ ወኢተዘከርከ ፡ ለጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ገብርከ ፡ ዘይትለአክ ፡ በቅድሜከ ፡ በንጹሕ ።
፶፰ ፤ መጠውከኒ ፡ ውስተ ፡ እደዊሆሙ ፡ ለፀርከ ፡ ኃጥኣን ፡ ወኢላውያን ።
፶፱ ፤ እለ ፡ ርኁቃን ፡ ወግሑሳን ፡ እምኔከ ።
፷ ፤ ወአንተኒ ፡ ርኁቅ ፡ ወግሑስ ፡ እምኔሆሙ፤
፷፩ ፤ አንሰ ፡ ሰአልኩከ ፡ ተሀበኒ ፡ ወልደ ፡ እምንጹሕ ፡ ካህን ፡ ወልደ ፡ ንጹሐን ፡ ካህናት ፡ እለ ፡ ሎሙ ፡ ሕግ ፡ ወሎሙ ፡ ሥርዓት ።
፷፪ ፤ ትፈቅድኑ ፡ ተሀበኒ ፡ ወልደ ፡ እምገብር ፡ ጽዩዕ ፡ ዘኢየአምር ፡ ሕገከ ፡ ወሥርዓተከ።
፷፫ ፤ ኀድግሰ ፡ እምዝንቱ ፡ ገብር ፡ ርኩስ ፡ እምውእቱ ፡ ካህን ፡ ቅዱስ ፡ እመ ፡ ኮነ ፡ ወልድ ፡ ዘኢያሠምረከ ፡ ዕጹ ፡ ማኅፀንየ ፡ እቤለከ ።

፴፭ ፤ ከዚ ፡ ዘንድ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሥ ፡ እንዴት ፡ ውለሻል ፡ አለሽ ፡ ብለው ።
፴፮ ፤ ይኸን ፡ ሁሉ ፡ ልብስ ፡ ሰጧት ።
፴፯ ፤ በሱ ፡ አስጌጧት ።
፴፰ ፤ የወርቅ ፡ ማርዳ ፡ አደረጉላት ።
፴፱ ፤ ለእጆቿም ፤ የወርቅ ፡ አምባር ።
፵ ፤ ለጣቶቿ ፡ የወርቅ ፡ ቀለበት ።
፵፩ ፤ ለእግሯም ፡ የወርቅ ፡ ጫማ ፡ አደረጉላት ።
፵፪ ፤ ንግሥታቶቹ ፡ እንደሚያጌጡት ፡ ማዕርግ ፡ በዚህ ፡ ሁሉ ፡ ጌጽ ፡ አስጌጿት ።
፵፫ ፤ እሷ ፡ ግን ፡ ታዝን ፡ ዕንባዋንም ፡ ከምድር ፡ ታንጠበጥብ ፡ ነበር ።
፵፬ ፤ ቀናም ፡ ብላ ፡ አታስተውል ።
፵፭ ፤ አንገቷን ፡ ደፍታ ፡ ምድር ፡ ትቆረቊር ፡ ነበር ፡ እንጂ ።
፵፮ ፤ በሕሊናዋ ፡ ግን ፡ ወደሰማይ ፡ ታመለክት ፡ ነበር ።
፵፯ ፤ ወታደሮቹም ፡ እጅግ ፡ ስታዝን ፡ ባዩዋት ፡ ጊዜ ።
፵፰ ፤ አንቺ ፡ ሆይ ፡ ምን ፡ ያስለቅስሻል ፡ እሷት።
፵፱ ፤ ንግሥት ፡ ሆነሻልና ።
፶ ፤ ይህን ፡ ብለው ፡ ወደተዘጋጀ ፡ ቤት ፡ ወስደው ፡ አገቧት ፡ ያሳድሯት ፡ ዘንድ ።
፶፩ ፤ ሥራው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ፡ ምግብ ፡ አቀረቡላት ።
፶፪ ፤ ጣዕማቸው ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ የሆነ ።
፶፫ ፤ ንጉሥ ፡ ብዪ ፡ ጠጪ ፡ ብሎሻል ፡ እሷት ።
፶፬ ፤ እሷ ፡ ግን ፡ አልተቀበለቻቸውም ፡ ከምግቡም ፡ አልተመገበች ።
፶፭ ፤ እሷ ፡ ግን ፡ ወደፈጣሪዋ ፡ እንደዚህ ፡ እያለች ፡ ታመለክት ፡ ነበር ።
፶፮ ፤ ጌታዬ ፡ ፈጣሪዬ ፡ ኢየሱስ ፡ ስንፍናዬን ፡ ለምን ፡ ተመለከትክ ።
፶፯ ፤ በንጹሕ ፡ ሆኖ ፡ የሚያገለግል ፡ ባሪያህ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብን ፡ ለምን ፡ አላሰብከውም ።
፶፰ ፤ አንተን ፡ ለሚክዱ ፡ ኃጥአን ፡ ለሚሆኑ ፡ ጠላቶች ፡ አሳልፈህ ፡ ለምን ፡ ሰጠኸኝ ።
፶፱ ፤ ካንተ ፡ አንድነት ፡ የተለዩ ።
፷ ፤ አንተም ፡ ከነሱ ፡ የተለየህ ፡ ነህ ።
፷፩ ፤ እኔስ ፡ ሥራት ፡ ያላቸው ፡ ሥራት ፡ የተሠራላቸው ፡ ከንጹሐን ፡ ካህናት ፡ ልጅ ፡ ከንጹሕ ፡ አገልጋይህ ፡ ልጅ ፡ ስጠኝ ፡ ብዬ ፡ ለምኜህ ፡ ነበር ።
፷፪ ፤ ሕግህን ፡ ሥርዓትህን ፡ ከማያውቅ ፡ ከሚያጸይፍ ፡ ባሪያ ፡ ልጅ ፡ ትሰጠኝ ፡ ዘንድ ፡ ወደድከን ።
፷፫ ፤ ከዚህ ፡ ከርኩስ ፡ ባሪያ ፡ ይቅርና ፡ ከዚያም ፡ ከንጹሕ ፡ አገልጋይህም ፡ ቢሆን ፡ አንተን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ፡ ልጅ ፡ ካልሆነ ፡ ማኅፀኔን ፡ ዝጋው ፡ እልሃለሁ ።

፳፬ ፤ አ ፡ እግዚእ ፡ አምላከ ፡ አድኅኖ ፡ አርኢ ፡ አድኅኖተከ ፡ በላዕሌየ ፡ የዮም ።

፳፭ ፤ አ ፡ እግዚእ ፡ አምላከ ፡ ሣህል ፡ አርኢ ፡ ሣህለከ ፡ በላዕሌየ ፡ የዮም ።

፳፮ ፤ ወዘንተ ፡ እንዘ ፡ ትጼሊ ፡ በልዑ ፡ ወጸግቡ ።

፳፯ ፤ ወይቤልዋ ፡ በሐኪ ፡ አ ፡ ንግሥትነ ።

፳፰ ፤ ጌሠመ ፡ ንወስደኪ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ ወይሬስየኪ ፡ ብእሲቶ ።

፳፱ ፤ ወይሰግዱ ፡ ለኪ ፡ ኵሎሙ ፡ እለ ፡ ውስተ ፡ መንግሥቱ ።

፴ ፤ አ ፡ እግዝእትነ ፡ በሊዓሰ ፡ አበይኪ ፡ ወንዋመኒ ፡ ኢትነውሚን ።

፴፩ ፤ ወትቤሎሙ ፡ እግዚእ ፡ ሐረያ ።

፴፪ ፤ በሉ ፡ ኑሙ ፡ አንትሙ ።

፴፫ ፤ ደቀሱ ፡ ኵሎሙ ፡ ወኖሙ ፡ ከቢቦሙ ፡ ኪያሃ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፪ ።

፩ ፤ ወለይእቲ ፡ ሰዓታ ፡ ተንሥአት ፡ ቅድስት ፡ ወአወፅአት ፡ አልባሳተ ፡ ሰርጕ ፡ እምላዕሌሃ ።

፪ ፤ እንዘ ፡ ትብል ፡ ለእመ ፡ ጸለይኩ ፤ ምስለ ፡ ዝንቱ ፡ ልብሰ ፡ ርኩስ ፡ ኢይሰምዓኒ ፡ አምላኪየ ።

፫ ፤ ወለብሰት ፡ አልባሲሃ ፡ ዘቀዳሚ ።

፬ ፤ ወሰገደት ፡ ብዙኃ ፡ እስከ ፡ ተሐፉ ።

፭ ፤ ወቆመት ፡ ቅድመ ፡ ገጸ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወሰፍሐት ፡ እደዊሃ ፡ ወጸለየት ፡ ከመዝ ፡ እንዘ ፡ ትብል ።

፮ ፤ እግዚኦ ፡ አምላከ ፡ ኵሉ ፡ ፍጥረት ።

፯ ፤ ዘኵሎ ፡ ትክል ፡ ወአልቦ ፡ ዘይሰአነከ ።

፰ ፤ ቀቲለሂ ፡ ትክል ፡ ወአኀይዎ ።

፱ ፤ ወአልቦ ፡ አመ ፡ ኢሀሎከ ።

፲ ፤ ወአልቦ ፡ ኀበ ፡ ኢሀሎከ ።

፲፩ ፤ ውስተ ፡ ኵሉ ፡ በሐውርት ፡ ምሉእ ፡ ውእቱ፡ መለኮትከ ።

፲፪ ፤ መዝ ፡ ፫ ፡ ፪ ፡ ቀ ፡ ፳፪ ፡ አንተ ፡ ውእቱ ፡ ዘአድኃንካ ፡ ለሣራ ፡ እምእደ ፡ አቤሜሌክ ንጉሠ ፡ ጌራራ ።

፲፫ ፤ አንተ ፡ ውእቱ ፡ ዘአድኃንኮ ፡ ለዳንኤል ፡ እምአፈ ፡ አናብስት ፡ ርኁባን ።

፲፬ ፤ አንተ ፡ ውእቱ ፡ ዘአድኃንካ ፡ ለሦስና ፡ እምእደ ፡ ረበናት ፡ እኩያን ።

፲፭ ፤ አንተ ፡ ውእቱ ፡ ዘአድኃንኮሙ ፡ ለሠለስቱ ፡ ደቂቅ ፡ እምእቶን ፡ እሳት ፡ ዘባቢሎን ።

፲፮ ፤ ቀዳሚኒ ፡ አንተ ፡ ወይእዚኒ ፡ አንተ ።

፲፯ ፤ ያስተርኢ ፡ ኃይለ ፡ አድኅኖትከ ፡ በላዕሌየ ።

፳፬ ፤ አቤቱ ፡ የትድግና ፡ ባለቤት ፡ ዛሬ ፡ በኔ ላይ ፡ ትድግናህን ፡ ግለጽ ።

፳፭ ፤ አቤቱ ፡ የይቅርታ ፡ ባለቤት ፡ ዛሬ ፡ በኔ ላይ ፡ ይቅርታህን ፡ ግለጽ ።

፳፮ ፤ እንዲህ ፡ እያለች ፡ ስትጸልይ ፡ እሊህ ፡ ወታደሮች ፡ በልተው ፡ ጸገቡ ።

፳፯ ፤ ንግሥት ፡ ሆይ፡ጤ ና፡ይስጥልን ፡ አሏት ።

፳፰ ፤ ነገ ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ እንወስድሻለን ፡ ሚስት ያደርግሻል ።

፳፱ ፤ በግዛቱ ፡ ውስጥ ፡ ያለ ፡ ሁሉ ፡ ይሰግድልሻል ።

፴ ፤ መብሉንስ ፡ እምቢ ፡ አልሽ ፡ መኝታውን ፡ ስንኳ ፡ አትተኚምን ።

፴፩ ፤ እግዚእ፡ሐረያም ፡ እንዲህ ፡ አለቻቸው ።

፴፪ ፤ እኔንስ ፡ እንቅልፍ ፡ እምቢ ፡ አለኝ ፡ እናንተ ፡ በሉ ፡ ተኙ ፡ አለቻቸው ።

፴፫ ፤ ሁሉም ፡ እሷን ፡ ከበው ፡ ተኙ ።

## ፀሥራ ፡ ሁለት ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ ቅድስት ፡ እግዚእ ፡ ሐረያም ፡ በዚያች ፡ ሰዓት ፡ ተነሥታ ፡ ያለበሷትን ፡ ልብስ ፡ አውጥታ ፡ አኖረች ።

፪ ፤ ይህን ፡ የርኩስ ፡ ልብስ ፡ ለብሸ ፡ ብጸልይ ፡ ፈጣሪዬ ፡ አይሰማኝም ፡ ብላ ።

፫ ፤ የቀድሞ ፡ ልብሷን ፡ ለብሳ ።

፬ ፤ ወዚ ፡ እስኪፈስ ፡ ድረስ ፡ ብዙ ፡ ሰገደች ።

፭ ፊቷን ፡ ወደ ምሥራቅ ፡ መልሳ ፡ ቆመች ፡ እጆቿን ፡ ዘርግታ ፡ እንዲህ ፡ እያለች ፡ ለመነች ።

፮ ፤ የፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ጌታ ።

፯ ፤ ሁሉ ፡ ይቻልሃል ፡ እንጂ ፡ የሚሳንህ ፡ የለም ።

፰ ፤ መግደልም ፡ ማዳንም ፡ ይቻልሃልና ።

፱ ፤ የሌለህበት ፡ ጊዜ ፡ የለም ።

፲ ፤ አንተም ፡ የሌለህበት ፡ ቦታ ፡ የለም ።

፲፩ ፤ ግዛትህ ፡ ጽንፍ ፡ እስከ ፡ ጽንፍ ፡ ነው ፡ እንጂ ።

፲፪ ፤ ሣራን ፡ ከጌራራ ፡ ንጉሥና ፡ ከፈርዖን ፡ እጅ ያዳንኻት ፡ አንተ ፡ ነህ ።

፲፫ ፤ ዳንኤልንም ፡ ከአናብስት ፡ አፍ ፡ ያዳንከው ፡ አንተ ፡ ነህ ።

፲፬ ፤ ሦስናንም ፡ ከረበናት ፡ እጅ ፡ ያወጣኸ ፡ አንተ ፡ ነህ ።

፲፭ ፤ ሠለስቱ ፡ ደቂቅንም ፡ ከባቢሎን ፡ እቶን ፡ እሳት ፡ ያዳንካቸው ፡ አንተ ፡ ነህ ።

፲፮ ፤ ቀድሞም ፡ አንተ ፡ ነህ ፡ ዛሬም ፡ አንተ ፡ ነህ ።

፲፯ ፤ በኔ ፡ የትድግናህ ፡ ኃይል ፡ ይገለጽ ።

፲፰ ፤ ሀብ ፡ ስብሐተ ፡ ለስምከ ፡ እግዚኦ ።
፲፱ ፤ ወኢትግድፍኒ ፡ ለአመትከ ፡ ግይርት ፡ ውስተ ፡ አፉሁ ፡ ለተኩላ ።
፳ ፤ ወአንተሂ ፡ አ፡ ሚካኤል ፡ ምንትኑ ፡ አርምሞትከ ።
፳፩ ፤ ወምንትኑ ፡ ተጸምሞትከ ።
፳፪ ፤ እንዘ ፡ ይወፅእ ፡ ላዕለ ፡ አመትከ ፡ ዝ ፡ ኵሉ ፡ ምንዳቤ ።
፳፫ ፤ ረሳእከኑ ፡ ኪዳነ ፡ ዘተካየድኩ ፡ ምስሌከ ፡ ከመ ፡ እግበር ፡ ተዝካረከ ።
፳፬ ፤ ወበዕለተ ፡ እገብር ፡ ተዝካረከ ፡ በጽሐኒ ፡ ኵሉ ፡ ምንዳቤ ።
፳፭ ፤ እምታከብረኒኑ ፡ አኅሠርከኒ ።
፳፮ ፤ እምታስተፍሥሐኒ ፡ አኅዘንከኒ ።
፳፯ ፤ ሐሰ ፡ ለከ ፡ አ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ትግበር ፡ ዘንተ ።
፳፰ ፤ ርድአኒ ፡ ረዳኤ ፡ ምንዱባን ።
፳፱ ፤ ሱቀኒ ፡ ሰዋቄ ፡ ትንቱናን ።
፴ ፤ ወዘንተ ፡ እንዘ ፡ ትጼሊ ፡ አስተርአያ ፡ ሚካኤል ፡ ገሃደ ።
፴፩ ፤ ወይቤላ ፡ ሰላም ፡ ለኪ ፡ አ ፡ ቅድስት ።
፴፪ ፤ አኮ ፡ ከመ ፡ አንጉልኪ ፡ ዘኮነ ፡ ዝ ፡ ነገር ።
፴፫ ፤ አላ ፡ ከመ ፡ አርኢ ፡ ጽንዓ ፡ ፍቅርየ ፡ በላዕሌኪ ።
፴፬ ፤ አኮ ፡ በእንቲአኪ ፡ ባሕቲቱ ፡ ዘትድኅኒ ፡ እምንዳቤ ።
፴፭ ፤ አላ ፡ በእንተ ፡ ወልድ ፡ ዘሀሎ ፡ ይትወለድ ፡ እምኔኪ ።
፴፮ ፤ ዘኢይከውን ፡ ኵሉ ፡ ዓለም ፡ ሤጠ ፡ አሐቲ ፡ ሥእርተ ፡ ርእሱ ።
፴፯ ፤ ክብረ ፡ ነገሥት ፡ ወብዕለ ፡ አሕዛብ ፡ ኢይከውን ፡ መጠነ ፡ አሐቲ ፡ ጸበለ ፡ ምድር ፡ ዘይከይድ ፡ በእግሩ ።
፴፰ ፤ ሕይወተ ፡ ብዙኃን ፡ ውእቱ ።
፴፱ ፤ ወፈውስ ፡ ድውያን ፡ ሀሎ ፡ ውስተ ፡ እዴሁ ።
፵ ፤ ወበእንቲአሁ ፡ ትድኅኒ ፡ እመንሱት ።
፵፩ ፤ ወትቤሎ ፡ እግዚእ ፡ ሐረያ ፡ ማዕዜኑ ፡ እድኅን ፡ እግዚእየ ።
፵፪ ፤ ወይቤላ ፡ በእንተ ፡ ዘፈቀደ እግዚአብሔር ፡
፵፫ ፤ ወዘንተ ፡ ብሂሎ ፡ ተሰወረ ፡ እምኔሃ ።
፵፬ ፤ ወይእቲስ ፡ ኃደረት ፡ ቀዊማ ፡ ኵሎ ፡ ኑኃ ፡ ሌሊት ።
፵፭ ፤ ወጸቢሖ ፡ ለብሰት ፡ አልባሳተ ፡ ሰርጉ ፡ እምቅድመ ፡ ይትነሥኡ ፡ ሠገራት ።
፵፮ ፤ ወወሰድዋ ፡ ኀበ ፡ ንጉሥ ፡ አሰርጊዎሙ ፡ በወርቅ ፡ ወበብሩር ፡ በከመ ፡ አዘዞሙ ፡ ትማልም ።

፲፰ ፤ አቤቱ ፡ አድነኝና ፡ ስምህን ፡ እንዳመሰግን ፡ አድርገኝ ።
፲፱ ፤ እኔ ፡ ድኀ ፡ ባሪያህን ፡ በዚህ ፡ በተኩላ ፡ አፍ ፡ አትጣለኝ ።
፳ ፤ አንተም ፡ ሚካኤል ፡ ዝምታህ ፡ ምንድነው ።
፳፩ ፤ ቸልታህ ፡ ምንድነው ።
፳፪ ፤ በባሪያህ ፡ ላይ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ መከራ ፡ ሲመጣባት ።
፳፫ ፤ በወር ፡ በወሩ ፡ ዝክርህን ፡ አዘክራለሁ ፡ ብየ ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ የተማማልኩትን ፡ መሐላ ፡ ዘነጋኸውን ።
፳፬ ፤ ዝክርህን ፡ በማደርግበት ፡ ቀን ፡ ይህ ፡ ሁሉ መከራ ፡ ደረሰብኝ ።
፳፭ ፤ ስታከብረኝ ፡ አዋረድኸኝ ።
፳፮ ፤ ደስ ፡ ስታሰኘኝ ፡ አሳዘንከኝ ።
፳፯ ፤ ሚካኤል ፡ ይህን ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ላንተ ፡ አይደለም ።
፳፰ ፤ በመከራ ፡ የተጨነቁትን ፡ የምትረዳቸው ፡ ርዳኝ ፡ እንጂ ።
፳፱ ፤ ለመውደቅ ፡ የሚፍገመገሙትን ፡ የምትደግፋቸው ፡ ደግፈኝ ፡ እንጂ ።
፴ ፤ እንዲህ ፡ እያለች ፡ ስትጸልይ ፡ ሚካኤል ፡ ተገልጾ ፡ ታያት ።
፴፩ ፤ ቅደስት ፡ ሆይ ፡ ቸር ፡ አለሽ ፡ አላት ።
፴፪ ፤ ይህ ፡ ነገር ፡ የተደረገው ፡ ላጠፋሽ ፡ አይደለም ።
፴፫ ፤ የፍቅሬን ፡ ጽናት ፡ ባንቺ ፡ እገልጽ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እንጂ ።
፴፬ ፤ ከዚህ ፡ መከራ ፡ የምትድኚው ፡ ስላንቺ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ።
፴፭ ፤ ካንቺ ፡ ስለሚወለደውም ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ እንጂ ።
፴፮ ፤ ዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ ላንዲት ፡ ራስ ፡ ጸጉሩ ፡ ዋጋው ፡ የማይሆን ።
፴፯ ፤ የአሕዛብ ፡ ብዕልና ፡ የነገሥታት ፡ ክብር ፡ በእግሩ ፡ ለሚረግጣት ፡ ላንዲት ፡ ምድር ፡ ትቢያ ፡ ዋጋዋ ፡ የማይሆን ።
፴፰ ፤ የብዙ ፡ ሰዎች ፡ ድኅነት ፡ ነው ።
፴፱ ፤ የሕሙማንም ፡ ድኅነት ፡ ከእጁ ፡ የሚገኝ ፡ ነው ።
፵ ፤ ስለሱ ፡ ከመከራው ፡ ትድኛለሽ ።
፵፩ ፤ እግዚእ ፡ ሐረያም ፡ ጌታዬ ፡ መቸ ፡ ነው ፡ የምድነው ፡ አለችው ።
፵፪ ፤ እግዚአብሔር ፡ በወደደው ፡ ቀን ።
፵፫ ፤ ይኸን ፡ ብሏት ፡ ተሰወረ ።
፵፬ ፤ እሷ ፡ ግን ፡ ሌሊቱን ፡ ሁሉ ፡ ቁማ ፡ ስትጸልይ ፡ አደረች ።
፵፭ ፤ ዘበኞቹ ፡ ሳይነሡ ፡ ጌጸኛውን ፡ ልብስ ፡ ለብሳ ፡ ተቀመጠች ።
፵፮ ፤ ነገ ፡ እንድታመጧት ፡ ብሎ ፡ እንዳዘዛቸው ፡ በወርቅና ፡ በብር ፡ አስጊጠው ፡ ወደንጉሡ ፡ ወሰዷት ።

፹፯ ፤ ወአብዕዋ ፡ ወአቀምዋ ፡ ቅድሜሁ ።

፹፰ ፤ ወሶበ ፡ ርእያ ፡ ንጉሥ ፡ ተፈሥሐ ፡ ጥቀ ።

፹፱ ፤ ወተንሥአ ፡ ሶቤሃ ፡ ወፈቀደ ፡ ይስዓማ ።

፺ ፤ ወኃደጋ ፡ እምፍርሃተ ፡ ሰብእ ፡ ወተመይጠ ፡ ወነበረ ፡ ዲበ ፡ መንበሩ ።

፺፩ ፤ ወኀለየ ፡ እንዘ ፡ ይብል ።

፺፪ ፤ ሶበ ፡ አውሰብክዋ ፡ ለዛቲ ፡ በዝየ ፡ ከመ ፡ ባዕዳት ፡ አንስት ፡ ኢይከውና ፡ ክብረ ።

፺፫ ፤ ወሊተሂ ፡ ኀሣር ፡ ውእቱ ።

፺፬ ፤ ወለዛቲሰ ፡ አንጊሥየ ፡ ላዕለ ፡ ኵሎን ፡ አንስቲያየ ፡ አውስባ ፡ በማልበረዱ ፡ ቤተ ፡ መንግሥትየ ።

፺፭ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ለሐራሁ ።

፺፮ ፤ አማን ፡ መዓድምተ ፡ ብእሲተ ፡ አምጻእክሙ ፡ ሊተ ።

፺፯ ፤ አነ ፡ ወልደ ፡ እስለንደኤ ፡ እሁበክሙ ፡ ሢመተ ፡ ዘየአክለክሙ ፡ ወለውሉድክሙ ።

፺፰ ፤ ወለዛቲሰ ፡ ብእሲት ፡ ዕቅብዋ ፡ በሠናይ ፡ ዕቅበት ።

፺፱ ፤ ወኵሎ ፡ ዘፈቀደት ፡ ግበሩ ፡ ላቲ ፡ እስከ ፡ ትከውን ፡ ንግሥተ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ዘአጥረይኩ ።

፻ ፤ ወእንዘ ፡ ነሐውርሂ ፡ ፍኖተ ፡ አጽንዕዋ ፡ በበቅል ፡ ዘእጼዓን ፡ ቦቱ ፡ አነ ።

፻፩ ፤ ወኢታርኅቅዋ ፡ እምኔየ ፡ መዓልተ ፡ ወሌሊተ ።

፻፪ ፤ ወገልብብዋ ፡ ተቢሰ ፡ ዘእኑም ፡ በወርቅ ።

፻፫ ፤ ከመ ፡ ኢይርአያ ፡ ገጻ ፡ ፀሐይ ፡ ወኢይርከባ ፡ ቍረ ፡ ሌሊት ።

፻፬ ፤ ወበጺሐነ ፡ ማልበረዲ ፡ ቤተ ፡ መንግሥትየ ፡ ህየ ፡ ታስተዋስቡኒ ፡ በሕገ ፡ አማልክትየ ።

፻፭ ፤ ወዘንተ ፡ ብሂሎ ፡ ተንሥአ ፡ ፍጡነ ፡ በጕጕዓ ፡ ወሖረ ።

፻፮ ፤ ወለቅድስትሰ ፡ እግዚእ ፡ ሐረያ ፡ ገብሩ ፡ ላቲ ፡ ሐራ ፡ በከመ ፡ አዘዘ ፡ ውእቱ ።

፻፯ ፤ ወአትለውዋ ፡ ድኅሬሁ ።

፻፰ ፤ እስመ ፡ ይቤሎሙ ፡ ኢታርኅቅዋ ፡ እምኔየ ።

፻፱ ፤ ወይእቲሰ ፡ ትበኪ ፡ ብካየ ፡ ዕጹበ ፡ በውስተ ፡ ልባ ።

፻፲ ፤ ወትብል ፡ አ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡ ማዕዜኑ ፡ ታድኅነኒ ፡ ቀርበ ፡ ዕለተ ፡ ኀጕል ።

፻፲፩ ፤ ዘንተ ፡ ትብል ፡ ኵሎ ፡ ጊዜ ፤

፻፲፪ ፤ ወእምዝ ፡ ፈነወ ፡ ሞተሎሚ ፡ ውስተ ፡ ሀገሩ ፡ ላዕካነ ፡ እንዘ ፡ ይብል ።

፻፲፫ ፤ ናሁ ፡ በጻሕኩ ፡ በዳኅና ፡ ወበፍሥሐ ።

፻፲፬ ፤ አስተጋብኡ ፡ ኵሎ ፡ ሰብአ ሰገል ፡ ወሰብአ ፡ ሐረስ ።

፻፲፭ ፤ ወኵሎ ፡ ማርያነ ።

፻፲፮ ፤ ወጥብሑ ፡ ፲ተ ፡ ፻ ፡ መቁዓለ ፡ አልሕምት ።

፹፯ ፤ አግብተው ፡ ከፊቱ ፡ አቆሟት ።

፹፰ ፤ ንጉሡም ፡ ባያት ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አለው ።

፹፱ ፡ ሊስማት ፡ ወዶ ፡ ፈጥኖ ፡ ተነሣ ።

፺ ፤ ሰውን ፡ ስላፈረ ፡ ትቷት ፡ ተመልሶ ፡ ተቀመጠ ።

፺፩ ፤ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አሰበ ።

፺፪ ፤ እንደሌሎቹ ፡ ሴቶች ፡ በዚህ ፡ በጕዳና ፡ ባገባት ፡ ክብር ፡ አይሆናትም ።

፺፫ ፤ ለኔም ፡ ተዋርዶ ፡ ነው ።

፺፬ ፤ ይችንስ፡በሚስቶቼ ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ አንግሼ ፡ በቤተ፡ መንግሥ ቴ ፡ በማልበረዱ ፡ አገባታለሁ ፡ ብሎ ፡ አሰበ ።

፺፭ ፤ ጭፍሮቹንም ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ።

፺፮ ፤ እውነት ፡ ያማረች ፡ የተወደደች ፡ ሴት ፡ አምጥታችሁልኛል ።

፺፯ ፤ እኔም ፡ የእስለንደኢ ፡ ልጅ ፡ ለልጅ ፡ ልጃችሁ ፡ የሚበቃ ፡ ሹመት ፡ እሰጣችኋለሁ ።

፺፰ ፤ ይችንም ፡ ሴት ፡ አክብራችሁ ፡ ጠብቋት ።

፺፱ ፤ በገንዘቤ ፡ ሁሉ ፡ እስካሠለጥናት ፡ ድረስ ፡ የወደደችውን ፡ ሁሉ ፡ አድርጉላት ።

፻ ፤ ጉዞም ፡ ስንሄድ ፡ እኔ ፡ በምቀመጥበት ፡ በቅሎ ፡ አስቀምጧት ።

፻፩ ፤ በመዓልትም ፡ በሌሊትም ፡ ከኔ ፡ አታርቋት ።

፻፪ ፤ በወርቅ ፡ በተሠራ ፡ ዓይነ ፡ ርግብ ፡ ሸፍኗት ።

፻፫ ፤ ቀን ፡ ፀሐይ ፡ እንዳያያት ፡ ሌት ፡ ቍር ፡ እንዳያገኛት ፤

፻፬ ፤ ከከተማው ፡ ቤተ ፡ መንግሥቴ ፡ በደረስን ፡ ጊዜ ፡ በጣዖቶቼ ፡ ሥርዓት ፡ ከዚያ ፡ ታጋቡኛላችሁ ፤

፻፭ ፤ ይህን ፡ ብሎ ፡ ተነሥቶ ፡ ቸኩሎ ፡ ሔደ ።

፻፮ ፤ ለእግዚእ ፡ ሐረያም ፡ እሱ ፡ እንዳዘዛቸው ፡ አደረጉላት ።

፻፯ ፤ በኋላ ፡ በኋላው ፡ እያስከተሉ ፡ ይዘዋት ፡ ሄዱ ።

፻፰ ፤ ከኔ ፡ አታርቋት ፡ ብሏቸዋልና ።

፻፱ ፤ እሷ ፡ ግን ፡ በልቡናዋ ፡ ጽኑ ፡ ኀዘን ፡ ታዝናለች ።

፻፲ ፤ እነሆ ፡ የጥፋት ፡ ቀን ፡ ቀረበ ፡ ሚካኤል ፡ መቼ ፡ ታድነኛለህ ።

፻፲፩ ፤ ሁሉ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ እያለች ፡ ታለቅሳለች

፻፲፪ ፤ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሞተለሚ ፡ መልክተኞችን ፡ ወደ ፡ ሀገሩ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ሰደደ ፤

፻፲፫ ፤ እነሆ ፡ ደስ ፡ ብሎኝ ፡ በደህና ፡ ተመለስኩ ፤

፻፲፬ ፤ የሚያማርቱትን ፡ ሁሉ ፡ በማልበረዲ ፡ ሰብስባችሁ ፡ ቆዩኝ ።

፻፲፭ ፤ ጠንቋዮችን ።

፻፲፮ ፤ ሽህ ፡ ሰንጋ ።

፷፯ ፤ ፲ተ ፡ ፻ተ ፡ አሕሩጋነ ፡ ዐቢያነ ፡ እለ ፡ ስርግዋነ ፡ አቅርንት ፡ በወርቅ ፡ ወበብሩር ።
፷፰ ፤ ፲ተ ፡ ፻ተ ፡ እለ ፡ ኢተሰርገው ።
፷፱ ፤ ፲ተ ፡ ፻ተ ፡ አባሕኮ ፡ አባግዕ ።
፸ ፤ ወ፲ተ ፡ ፻ተ ፡ መቁዓለ ፡ ጠሊ ።
፸፩ ፡ ወ፪ተ ፡ ፻ ፡ ደዋርኃ ።
፸፪ ፤ ከመዝ ፡ በልዎሙ ፡ ለጋላት ።
፸፫ ፤ ወለገዛዕትሂ ፡ በልዎሙ ፡ አስተዳልዉ ፡ ፰ ፡ ፻ ፡ በመሥፈርተ ፡ ኔባል ፡ ሜስ ።
፸፬ ፤ ምዝርስ ፡ ይኩን ፡ ከመ ፡ ማይ ።
፸፭ ፤ ወለኃባዝያንሂ ፡ በልዎሙ ፡ አስተዳልው ፡ ኅብስተ ፡ ወዳፍንተ ፡ ተብሲለ ፡ ወጻብሐ ፡ ዘአልቦ ፡ ኍልቍ ።
፸፮ ፤ ወለአንስቲያየ ፡ ዐሠርቲሆን ፡ በልዎን ፡ አስተዳልዋ ፡ በቤትክን ፡ ማዕዳተ ፡ ብዙኃ ፡ ዘአልቦ ፡ ኍልቍ ።
፸፯ ፤ ወለኵሎሙ ፡ ሰብአ ፡ ዳሞት ፡ በልዎሙ ፡ ጽንሁኒ ፡ በማልበረዲ ፡ አስተዳሊወክሙ ፡ ጸባሕተ ፡ መንግሥትየ ።
፸፰ ፤ ወለእመ ፡ ኢገበርክሙ ፡ ዘንተ ፡ ኵሎ ፡ ዘአዘዝኩክሙ ፡ እመትር ፡ አርእስቲክሙ ፡ በሰይፍ ።
፸፱ ፤ ወአወድየክሙ ፡ ውስተ ፡ ጠማረ ፡ ግራር ፡ በልዎሙ ።
፹ ፤ ወአንትሙኒ ፡ ለእመ ፡ ኢነገርክሙ ፡ ዘንተ ፡ ቃለ ፡ መልእክትየ ፡ መክፈልትክሙ ፡ ከመዝ ፡ ሑሩ ፡ አፍጥኑ ፡ ተጽኢነክሙ ፡ በአፍራስ ፡ ረዋጽያን ።
፹፩ ፤ ወሀበ ፡ በጻሕክሙ ፡ ሀገረ ፡ አስተባርዩ ፡ አፍራሰ ፡ በዲበ ፡ አፍራስ ።
፹፪ ፤ ከመ ፡ ትብጽሑ ፡ ለጌሠም ።
፹፫ ፤ ወአንዘ ፡ ኢበጽሐ ፡ እስከ ፡ ሰሙን ፡ መዋዕል ።
፹፬ ፤ ወእምዝ ፡ ሖሩ ፡ ላዕካን ፡ እምኀቤሁ ።
፹፭ ፤ ወበጽሑ ፡ ውስተ ፡ ሀገር ፡ በሳኒታ ።
፹፮ ፤ ወነገሩ ፡ ቃሎ ፡ በከመ ፡ አዘዞሙ ።
፹፯ ፤ ወእሉሂ ፡ ሰሚዖሙ ፡ አስተዳለዉ ፡ ኵሎ ፡ ዘከመ ፡ ይቤሎሙ ።
፹፰ ፤ ወተንሥአ ፡ ሞተለሚ ፡ እንዘ ፡ ይትልዎሙ ፡ ወበጽሐ ፡ ባልበረዲ ፡ በሰሙን ፡ መዋዕል ።
፹፱ ፤ በከመ ፡ ተአደሙ ፡ ተቀበልዎ ፡ ሰብአ ፡ ሀገሩ ፡ በፍሥሐ ፡ ወበይባቤ ።
፺ ፤ እሉሂ ፡ ልኡካን ፡ ተቀበልዎ ፡ ምስሌሆሙ ።
፺፩ ፤ ወቀጸቦሙ ፡ ለእሙንቱ ፡ ልኡካን ።
፺፪ ፤ ወይቤሎሙ ፡ አስተዳለውክሙኑ ፡ ኵሎ ፡ ዘአዘዝኩክሙ ።
፺፫ ፤ ወይቤልዎ ፡ እወ ፡ ንጉሥ ።
፺፬ ፤ ወይቤሎሙ ፡ ማርያኒ ፡ ወሰብአ ፡ ሰገልሂ ፡ ወኵሎሙ ፡ ሰብአ ፡ ኪነት ፡ ተጋብኡኑ ።
፺፭ ፤ ወይቤልዎ ፡ እወ ።

፷፯ ፤ ሺህ ፡ ጊደር ፡ ታላላቆች ፡ ቀንዳቸው ፡ በወርቅ ፡ በብር ፡ የተሻበ ።
፷፰ ፤ ሺህ ፡ ያልተሻቡ ።
፷፱ ፤ ሺህ ፡ የበግ ፡ ሙክት ።
፸ ፤ ሺህ ፡ የፍየል ፡ ሙክት ።
፸፩ ፤ ሁለት ፡ እልፍ ፡ ዶሮ ።
፸፪ ፤ ሻለቆቹን ፡ ይህን ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ አዘጋጅታችሁ ፡ ቆዩኝ ፡ በሏቸው ።
፸፫ ፤ ጠጅ ፡ አሳላፎቹንም ፡ ሰባ ፡ እልፍ ፡ ማድጋ ፡ ጠጅ ፡ አዘጋጁ ።
፸፬ ፤ ጠላ ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ውኃ ፡ ይሁን ፡ አለ ።
፸፭ ፤ አዛገሮችንም ፡ እንጀራውን ፡ አምባሻውን ፡ ወጡን ፡ አብዝታችሁ ፡ አዘጋጁ ፡ በሏቸው ።
፸፮ ፤ ዐሥሩ ፡ ሚስቶቼንም ፡ በየቤታችሁ ፡ ብዙ ፡ ምግብ ፡ አዘጋጁ ፡ በሏቸው ፡ አለ ።
፸፯ ፤ የዳሞትንም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ በማልበረዲ ፡ ግብሬን ፡ አዘጋጅታችሁ ፡ ቆዩኝ ፡ በሏቸው ።
፸፰ ፤ ይህንን ፡ ያዘዝኋችሁን ፡ ሁሉ ፡ ያላደረጋችሁ ፡ እንደሆነ ፡ በሰይፍ ፡ እቀጣችኋለሁ ።
፸፱ ፤ ገደል ፡ እጥላችኋለሁ ፡ በእሳት ፡ አቃጥላችኋለሁ ።
፹ ፤ እናንተም ፡ ይኸን ፡ የላኳችሁን ፡ ያላደረጋችሁ ፡ እንደሆነ ፡ ቅጣታችሁ ፡ እንደነሱ ፡ ነው ፡ በፈጣናች ፡ ፈረሶች ፡ ሆናችሁ ፡ ሂዱ ።
፹፩ ፤ በየደረሳችሁበትም ፡ አገር ፡ ፈረስ ፡ እያፈራረቃችሁ ፡ ሂዱ ።
፹፪ ፤ ነገ ፡ እንድትገቡ ።
፹፫ ፤ እኔም ፡ እስከስምንት ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ እገባለሁ ።
፹፬ ፤ መልክተኞቹም ፡ ታዘው ፡ ሄዱ ።
፹፭ ፤ በነጋው ፡ ከከተማው ፡ ደረሱ ።
፹፮ ፤ እንደላካቸው ፡ ነገሩ ።
፹፯ ፤ እነሱም ፡ የላከባቸውን ፡ ሰምተው ፡ እንዳዘዛቸው ፡ አዘጋጁ ።
፹፰ ፤ ሞተለሚም ፡ ተነሥቶ ፡ እየተከተላቸው ፡ በስምንት ፡ ቀን ፡ ከከተማው ፡ ደረሰ ።
፹፱ ፤ የሀገሩም ፡ ሰዎች ፡ እንደቀጠራቸው ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ በዕልልታ ፡ በግርግርታ ፡ ተቀበሉት ።
፺ ፤ እሊህም ፡ መልክተኞች ፡ ከሕዝቡ ፡ ጋራ ፡ መጥተው ፡ ተቀበሉት ።
፺፩ ፤ መልክተኞቹን ፡ ጠቀሳቸው ።
፺፪ ፤ ያዘዝኋችሁን ፡ ሁሉ ፡ አዘጋጃችሁን ፡ አላቸው ።
፺፫ ፤ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ አዎን ፡ አሉት ።
፺፬ ፤ ጠንቋዮችም ፡ ጥበብ ፡ ያላቸው ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ተሰብሰቡ ፡ አላቸው ።
፺፭ ፤ አዎን ፡ አሉት ።

፻፮ ፤ ወይቤሎሙ ይእዜኒ ፡ በልዎሙ ፡ ለኵሎሙ ፡ ተደለዉ ፡ ለጌሠም ።

፻፯ ፤ ከመ ፡ ንሰግድ ፡ ለአማልክቲነ ፡ ወንገብር ፡ ሎሙ ፡ በዓለ ፡ ዓቢየ ።

፻፰ ፤ እስመ ፡ እሙንቱ ፡ ያቀንቱነ ፡ ኃይለ ፡ በውስተ ፡ ጸብእ ።

፻፱ ፤ ወይቤልዎ ፡ አሆ ፡ ንገብር ፡ በከመ፡ትቤለነ።

፻፲ ፤ ወቦአ ፡ ውስተ ፡ ቤተ መንግሥቱ ፡ ማልበረዲ ።

፻፲፩ ፤ ወለእግዚእ ፡ ሐረያስ ፡ አዘዘ ፡ ያብዕዋ ፡ ውስተ ፡ ካልዕ ፡ ቤት ፡ እስከ ፡ ጌሠም ።

፻፲፪ ፤ ወውእቱሰ ፡ ኀደረ ፡ ኵላ ፡ ይእተ ፡ ሌሊተ ፡ እንዘ ፡ ይሠርእ ፡ ኵሎ ፡ ሥርዓተ ፡ መንግሥት ።

፻፲፫ ፤ ወሐራሁኒ ፡ ኢኖሙ ፡ እንዘ ፡ ያስተዳልዉ፡ ማዕዳተ ፡ ወይጠብሑ ፡ መጋዝዕተ ።

፻፲፬ ፤ ወኮነ ፡ ኍልቆሙ ፡ ለእለ ፡ ተጠብሑ ፡ በይእቲ ፡ ዕለት ፡ ፳፻ ወ፫፻ተ ።

፻፲፭ ፤ ወመባልዕትሰ ፡ ዘተገብረ ፡ በይእቲ ፡ ሌሊት ኢይትኄለቍ ፡ ብዝኆ ።

፻፲፮ ፤ ወለ ፡ እግዚእ ፡ ሐረያስ ፡ ሶበ ፡ አብእየ ፡ ውስተ ፡ ቤት ፡ ካልዕ ፡ ሐራሁ ፡ ለንጉሥ ፡ ይቤልዋ ፡ አ ፡ እግዝእትነ ፡ ዮምሰ ፡ ብልዒ ፡ ወስትዪ ፡ ወተፈሥሒ ፡ ለነ ።

፻፲፯ ፤ ጌሠመ ፡ ለእመ ፡ ርእየኪ ፡ ንጉሥ ፡ ድግድግተኪ ፡ ይኴንነነ ፡ ርእሰነ ።

፻፲፰ ፤ እስመ ፡ እምአመ ፡ ተጸወወት ፡ እስከ ፡ ይእቲ ፡ ዕለት ፡ ኢበልዓት ፡ እክለ ፡ ወኢስትየት ፡ ማየ ።

፻፲፱ ፤ ወባሕቱ ፡ እንተ ፡ ጸብሐት ፡ ይጌይስ ፡ ነፍስታ ፡ እምእለ ፡ በልዑ ፡ ወሰትዩ ።

፻፳ ፤ በከመ ፡ ሐየሰ ፡ ነፍስቶሙ ፡ ለ፫ ፡ ደቂቅ ፡ በባቢሎን ፡ እንዘ ፡ ኢይበልዑ ፡ እክለ ።

፻፳፩ ፤ ወትቤሎሙ ፡ ቅድስት ፡ እግዚእ ፡ ሐረያ ፡ ለእሙንቱ ፡ ሐራ ።

፻፳፪ ፤ አንሰ ፡ ኢይበልዕ ፡ ወኢይሰቲ ፡ እስከ ፡ እሰምዕ ፡ ፍትሐ ፡ እምእምላኪየ ።

፻፳፫ ፤ ወዘንተ ፡ ብሂላ ፡ ዓበየቶሙ ።

፻፳፬ ፤ ወቤተት ፡ ኵላ ፡ ይእተ ፡ ሌሊተ ፡ በስብሐት ፡ ወበጸሎት ።

፻፳፭ ፤ እንዘ ፡ ትብል ፡ አ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመዝኑ ፡ ረሰይከኒ ።

፻፳፮ ፤ ቀዳሚኒ ፡ ተወሰብኩ ፡ በሕግከ ፡ ለ፩ ፡ ምት ፡ ንጹሕ ።

፻፳፯ ፤ ወዮምሰ ፡ አስተዳለውከኒ ፡ እኩን ፡ ብእሲተ ፡ ለከሃዴ ፡ ሕግከ ፡ በሕገ ፡ አማልክት ፡ ርኩሳን ።

፻፳፰ ፤ ሐሰ ፡ ለከ ፡ እግዚኦ ፡ ትግበር ፡ ዘንተ ።

፻፮ ፤ አሁንም ፡ ሄዳችሁ ፡ ለነገ ፡ ተዘጋጁ ፡ በሏቸው ።

፻፯ ፤ ለጣዖቶቻችን ፡ እንሰግድ ፡ ዘንድ ፡ በዓልም፡ እናደርግላቸው ፡ ዘንድ ።

፻፰ ፤ በሰልፍ ፡ ጊዜ ፡ ድል ፡ እንድናደርግ ፡ የሚያደርጉን ፡ እነሱ ፡ ናቸውና ።

፻፱ ፤ እሺ ፡ እንዳዘዝከን ፡ እናደርጋለን ።

፻፲ ፤ በማልበረዲ ፡ ወዳለ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ገባ ።

፻፲፩ ፤ እግዚእ ፡ ሐረያን ፡ እስከ ፡ ነገ ፡ ከሌላ ፡ ቤት ፡ አሳርፏት ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ።

፻፲፪ ፤ እሱ ፡ ግን ፡ ሌሊቱን ፡ ሁሉ ፡ ሥርዓተ ፡ መንግሥት ፡ ሲሠራ ፡ አደረ ።

፻፲፫ ፤ አሽከሮቹም ፡ ሰንጋውን ፡ ሲያርዱ ፡ ማዕዱን ፡ ሲያዘጋጁ ፡ አልተገኙም ።

፻፲፬ ፤ በዚችም ፡ ቀን ፡ የታረደው ፡ ዕርድ ፡ ቍጥር ሃያ ፡ እልፍ ፡ ስምንት ፡ መቶ ፡ ሆነ ፤

፻፲፭ ፤ በዚያችም ፡ ሌሊት ፡ የተሠራው ፡ ምግብ ፡ ግን ፡ ሥፍር ፡ ቍጥር ፡ የለውም ።

፻፲፮ ፤ የንጉሡ ፡ ዘበኞች ፡ እግዚእ ፡ ሐረያን ከሌላው ፡ ቤት ፡ ባገቧት ፡ ጊዜ ፡ ዛሬ ፡ ስንኳ ፡ ለኛ ፡ ብለሽ ፡ ብዪ ፡ ጠጭ ፡ ደስ ፡ ይበልሽ ።

፻፲፯ ፤ ነገ ፡ ንጉሥ ፡ ከስተሽ ፡ ጠቍረሽ ፡ ያየሽ ። እንደሆነ ፡ እኛን ፡ ይቀጣናል ፡ አሏት ፤

፻፲፰ ፤ ከተማረከች ፡ ጀምሮ ፡ እስከዚያች ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ እህል ፡ ውኃም ፡ አልቀመሰችም ፡ ነበርና ።

፻፲፱ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ከበሉት ፡ ከጠጡት ፡ ይልቅ ፡ ሰውነቷ ፡ እየነጋ ፡ ያምር ፡ ነበር ።

፻፳ ፤ የ፫ ፡ ደቂቅ ፡ ሰውነት ፡ እህል ፡ ሳይበሉ ፡ ያምር ፡ እንደነበረ ።

፻፳፩ ፤ እግዚእ ፡ ሐረያም ፡ ዘበኞቹን ፡ እንዲህ ፡ አለቻቸው ።

፻፳፪ ፤ እኔስ ፡ ከፈጣሪየ ፡ ፍርድ ፡ እስክሰማ ፡ ድረስ ፡ አልበላም ፡ አልጠጣም ።

፻፳፫ ፤ ይህን ፡ ብላ ፡ እምቢ ፡ አለቻቸው ።

፻፳፬ ፤ ሌሊቱን ፡ ሁሉ ፡ ፈጣሪዋን ፡ እየለመነች ፡ እያመሰገነች ፡ አደረች ፤

፻፳፭ ፤ ጌታዬ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲህ ፡ አደረከኝ ፡ እያለች ።

፻፳፮ ፤ ቀድሞ ፡ በሕግህ ፡ ላንድ ፡ ለንጹሕ ፡ ባል ፡ ታጨሁ ።

፻፳፯ ፤ ዛሬ ፡ ግን ፡ በርኩሳን ፡ በጣዖት ፡ ሥርዓት ፡ ለሕግ ፡ አፍራሽህ ፡ ሚስት ፡ እሆን ፡ ዘንድ ፡ አዘጋጀኸኝ ።

፻፳፰ ፤ አቤቱ ፡ ጌታዬ ፡ ይህን ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ ለአንተ ፡ አይገባህም ።

፻፴፩ ፤ ወውእቱሰ ፡ እልው ፡ ኮነ ፡ ቦቱ ፡ ኑኃ ፡ ይእቲ ሌሊት ፡ ከመ ፡ ፲ቱ ፡ ፻ት ፡ ዓመት ፡ እምብዝኃ ፡ ጕጕዓሁ ፡ ወንዴተ ፡ ፍቅሩ ፡ በእንተ ፡ እግዚእ ፡ ሐረያ ።

፻፴፪ ፤ ወሶበ ፡ ጸብሐ ፡ አዘዘ ፡ ያምጽእዋ ፡ ለእግዚእ ፡ ሐረያ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ አማልክት ፡ ወአምጽእዋ ።

፻፴፫ ፤ ወተንሥአ ፡ ወሖረ ፡ ምስለ ፡ ኵሎሙ ፡ መኳንንቲሁ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ አማልክት ፡ ወተለውዎ ፡ ኵሎሙ ፡ ሠራዊቱ ።

፻፴፬ ፤ ወበጺሖ ፡ ውስተ ፡ ቤተ ፡ አማልክት ፡ ቆመ ፡ ውእቱ ፡ ቅድመ ፡ ኵሎሙ ፡ ጉቡአን ፡ ከመ ፡ ይስግድ ፡ ለአማልክት ።

፻፴፭ ፤ ወከመ ፡ ያስግዳ ፡ ለእግዚእ ፡ ሐረያ ፡ ወያንግሣ ፡ ላዕለ ፡ ኵሉ ፡ ምኵናኑ ።

፻፴፮ ፤ ወሶቤሃ ፡ ግብተ ፡ በረቀ ፡ መብረቅ ፡ እምሰማይ ።

፻፴፯ ፤ ወኮነ ፡ ጸአዕ ፡ ወነጐድጓድ ።

፻፴፰ ፤ ወተከውሰ ፡ ኵሉ ፡ ኃይለ ፡ ሰማያት ፡ ወምድር ።

፻፴፱ ፤ ወወረደ ፡ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ሊቀ ፡ መላእክት ፡ ወነሥኣ ፡ ለእግዚእ ፡ ሐርያ ፡ እማእከሎሙ ፡ ወአኃዛ ፡ በክነፊሁ ፡ ወጸራ ፡ በእንግድዓሁ ።

፻፵ ፤ ወአብጽሐ ፡ እምድረ ፡ ዳሞት ፡ ምድረ ፡ ዞረሬ ፡ ጊዜ ፡ ፫ ፡ ሰዓት ፡ ዘዕለት ።

፻፵፩ ፤ አመ ፡ ፳ወ፪ ፡ ለወርኃ ፡ መጋቢት ፡ እንዘ ፡ የዓጥን ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ወይትመሐለል ፡ በእንቲአሃ ።

፻፵፪ ፤ ወአቀማ ፡ ኀበ ፡ ዐረፍተ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ወኀደጋ ፡ ህየ ፡ ወዐርገ ፡ ሰማየ ።

፻፵፫ ፤ ወሞተለሚሰ ፡ ደንገፀ ፡ እምፍርሃተ ፡ መባርቅት ፡ ወነጐድጓድ ፡ ወአንበበት ፡ ነፍሱ ።

፻፵፬ ፤ ወእምሠራዊቱሂ ፡ ሞቱ ፡ እምግርማ ፡ ውእቱ ፡ መብረቅ ፡ ፲ቱ ፡ ፻ት ።

፻፵፭ ፤ ወእምነ ፡ ማ፫ያን ፡ ፫ቱ ፡ ፻ት ።

፻፵፮ ፤ መኑ ፡ ይክል ፡ ነጊረ ፡ ግርማ ፡ ዘኮነ ፡ በይእቲ ፡ ዕለት ፡ ላዕለ ፡ ውእቱ ፡ ዕልው ፡ ወላዕለ ፡ ሠራዊቱ ።

፻፵፯ ፤ በከመ ፡ ተዓርወየ ፡ ልበ ፡ ናቡከደነጾር ፡ ፯ተ ፡ ዓመተ ፡ በእንተ ፡ ትዕቢቱ ፡ ከማሁ ፡ ተአንበዘ ፡ ልበ ፡ ሞተለሚ ፡ ፳ወ፭ ፡ ዓመተ በእንተ ኃጢአቱ ።

፻፵፰ ፤ ወኢያአምር ፡ ዘተናገረ ።

፻፵፱ ፤ ምዕረ ፡ ይቤ ፡ ቅትሉ ፡ ወካዕበ ፡ ይቤ ፡ አምጽኡ ፡ ሕያዎ ፡ ዘአዘዘ ፡ ይቅትልዎ ።

፻፶ ፤ ወዓዲ ፡ ይቤ ፡ ሕንጹ ፡ ሊተ ፡ አብያተ ፡ መልዕልተ ፡ አየራት ።

፻፶፩ ፤ ወመኳንንቲሁ ፡ የሐይጥዎ ፡ እንዘ ፡ ይብሉ አሆ ።

፻፴፩ ፤ ለዚህ ፡ ከሃዲ ፡ ግን ፡ እግዚእ ፡ ሐረያን ፡ ከመውደዱና ፡ ከመቸኮሉ ፡ የተነሣ ፡ ይቺ ሌሊት ፡ እንደ ፡ ሽህ ፡ ዘመን ፡ ሆናበት ፡ አደረ ።

፻፴፪ ፤ በነጋ ፡ ጊዜ ፡ እስከ ፡ ቤተ ፡ ጣዖት ፡ ድረስ አምጧት ፡ ብሎ ፡ አዘዘ ፡ አመጧት ።

፻፴፫ ፤ ተነሥቶ ፡ ሠራዊቱንም ፡ መኳንንቱንም ፡ አስከትሎ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ጣዖት ፡ ሔደ ።

፻፴፬ ፤ ከጣዖት ፡ ቤት ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ለጣዖት ፡ ይሰግድ ፡ ዘንድ ፡ ከተሰበሰቡት ፡ መካከል ። ቆመ ።

፻፴፭ ፤ እግዚእ ፡ ሐረያንም ፡ ለጣዖት ፡ አሰግዶ ፡ በግዞቱ ፡ ሁሉ ፡ ያነግሣት ፡ ዘንድ ።

፻፴፮ ፤ ያን ፡ ጊዜ ፡ ድንገት ፡ ከሰማይ ፡ መብረቅ ፡ በረቀ ።

፻፴፯ ፤ ብልጭልጭታ ፡ ሆነ ፡ ነጐድጓድ ፡ ተሰማ ።

፻፴፰ ፤ ዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ ተነዋወጠ ።

፻፴፱ ፤ ቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡ ወርዶ ፡ ከመካከላቸው ፡ አንሥቶ ፡ በክንፉ ፡ ታቅፎ ፡ ወሰዳት ።

፻፵ ፤ ከዳሞት ፡ ዞረሬም ፡ በሦስት ፡ ሰዓት ፡ አደረሳት ።

፻፵፩ ፤ በመጋቢት ፡ በሃያ ፡ ሁለት ፡ ቀን ፡ ጸጋ ፡ አብ ፡ ከቤተ ፡ መቅደስ ፡ ገብቶ ፡ ሲያጥን ፡ ለሷም ፡ ሲለምን ።

፻፵፪ ፤ ከቤተ ፡ መቅደስ ፡ አግብቶ ፡ ከዚያ ፡ ትቷት ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ዐረገ ።

፻፵፫ ፤ ከነጐድጓዱና ፡ ከመብረቁ ፡ ፍርሃት ፡ የተነሣ ፡ ሞተለሚ ፡ ግን ፡ ደነገፀ ፡ አእምሮውን ፡ አጣ ።

፻፵፬ ፤ ከመብረቁ ፡ ግርማ ፡ የተነሣ ፡ ከሠራዊቱ ፡ ሽህ ፡ ሰው ፡ ሞቱ ።

፻፵፭ ፤ ከጠንቋዮቹም ፡ ከካህናት ፡ ጣዖቱም ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሞቱ ።

፻፵፮ ፤ በሠራዊቱና ፡ በዚህ ፡ ከሀዲ ፡ ላይ ፡ በዚያች ቀን ፡ የተደረገውን ፡ ግርማ ፡ ለመናገር ፡ ማን ይችላል ።

፻፵፯ ፤ ናቡከደነጾር ፡ በትዕቢቱ ፡ ሰባት ፡ ዓመት ፡ አውሬ ፡ እንደሆነ ፡ ሞተለሚም ፡ በኀጢአቱ ፡ ሃያ ፡ አምስት ፡ ዘመን ፡ አእምሮውን ፡ አጥቶ ፡ ኖረ ።

፻፵፰ ፤ የሚናገረውን ፡ ሳያውቅ ።

፻፵፱ ፤ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ግደሉ ፡ ይላል ፡ ሁለተኛ ፡ ግደሉ ፡ ብሎ ፡ ያዘዘውን ፡ አድናችሁ ፡ አምጡ ፡ ይላል ።

፻፶ ፤ ዳግመኛም ፡ በሰማይ ፡ ላይ ፡ ቤት ፡ ሥሩልኝ ይላል ።

፻፶፩ ፤ መኳንንቱም ፡ እሺ ፡ እያሉ ፡ ያታልሉታል ።

፪፻፪ ፤ እስመ ፡ በከመ ፡ ግእዙ ፡ ለመልአከ ፡ ሀገር
ይገብሩ ፡ እለ ፡ ይነብሩ ፡ ውስቴታ ።

## ምዕራፍ ፡ ፲፫ ።

፩ ፤ ወእግዚእ ፡ ሐረያሰ፡ እንዘ ፡ ትጼሊ ፡ ቀዊማ
ኀበ ፡ ምቅዋማ ፡ ዘዘልፍ ።
፪ ፤ ወተአኰቶ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በእንተ ፡
ኵሎ ፡ ዘገብረ ፡ ላቲ ።
፫ ፤ ወፅአ ፡ አቡነ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ እምቤተ ፡
መቅደስ ፡ ከመ ፡ ይዑድ ፡ በማዕጠንት ።
፬ ፤ ወርእየ ፡ ብእሲተ ፡ በአልባሰ ፡ ወርቅ ፡
ዑጽፍት ፡ ወኍብርት፡ እንዘ ፡ ትጼሊ፡ደንገፀ።
፭ ፤ ወሀለየ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ እምአይቴ ፡ መጽ
አት ፡ ዘዘመጠነዝ ፡ ብእሲት ፡ ዘአልባቲ ፡
አግብርት ፡ ወአዕማት ።
፮ ፤ ወእንዘ ፡ ያነክር ፡ ከመዝ ፡ የዐ ፡ ቤተ ፡
ክርስቲያን ፡ ወቦአ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ።
፯ ፤ ወፈጸመ ፡ ጸሎተ ፡ ዕጣን ፡ ወወፅአ ፡ ኀቤሃ ፡
ወባረካ ፡ እንዘ ፡ ግልብብት ፡ ይእቲ ።
፰ ፤ ወኢታርእየ ፡ ገጻ ፡ ወወፅኡ ፡ እምቤተ ፡
ክርስቲያን ፡ ኅቡረ ፡ ወነበሩ ፡ አሐተኔ ።
፱ ፤ ወይቤላ ፡ ዳህንኑ ፡ እግዝእትየ ።
፲ ፤ ወትቤሎ ፡ ዳህን ።
፲፩ ፤ ወይቤላ ፡ እምአይቴ ፡ አንቲ ፡ እርእየኪ ፡
በዘመጠነዝ ፡ ዕበይ ፡ ወክብር ።
፲፪ ፤ አግብርት ፡ ወአዕማት ፡ ዘአልብኪ ፡ ለም
ንት ፡ ተሐውሪ ፡ ባሕቲተኪ ፡ እግዝእተ ፡
ዘ ት መ ስ ሊ ፡ ከ መ ፡ አ ዋ ል ደ ፡ ንግ
ሥት ።
፲፫ ፤ ወትቤሎ ፡ አማን ፡ እምአዋልደ ፡ ነገሥት ፡
አነ ።
፲፬ ፤ ወእንዘ ፡ ነሐውር ፡ በፍኖት ፡ ምስለ ፡ አግ
ብርትየ ፡ ወአዕማትየ ፡ ምስለ ፡ ኵሉ ፡ዘብየ።
ረከበኒ ፡ ሞተለሚ ፡ ወነሥአኒ ፡ ኵሎ ።
፲፭ ፤ ወሊተሰ ፡ ባሕቱ ፡ አንገፈኒ ፡ እግዚአብሔር
እምእዴሁ ።
፲፮ ፤ ወሶበ ፡ ሰማዕኩ ፡ በእንተ ፡ ፩ ፡ ብእሲ ፡
ዘስሙ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ ከመ ፡ ተጼወወት ፡
ብእሲቱ ፡ መጻእኩ ፡ ዝየ ፡ ከመ ፡ እኩኖ ፡
ብእሲተ ፡ ህየንቴሃ ።
፲፯ ፤ ወይቤላ ፡ ለምንት ፡ ዘንተ ፡ ሀለይኪ ።
፲፰ ፤ እስመ ፡ ኢይከውኖ ፡ ለካህን ፡ ይሰዓር ፡
ክህነቶ ።
፲፱ ፤ ወዓዲ ፡ አንቲ ፡ ክብርት ፡ ብእሲት ።
፳ ፤ ወውእቱ ፡ ግዩር ፡ ዘአልቦቱ ፡ ምንተ ፡ ለእመ
አውሰብኪ ፡ ኪያሁ ፡ ውእቱ ፡ ይከውነኪ ፡
ኃሣረ ።
፳፩ ፤ ወነገረሂ ፡ እንዘ ፡ ይብል ፡ ሰማዕክዎ ፡ ለው
እቱ ፡ ብእሲ ።

፪፻፪ ፤ የሀገሩ ፡ ሰዎችም ፡ ያገሩ ፡ ገዥ ፡ ያዘዛቸ
ውን ፡ ያደርጉ ፡ ነበርና ።

## ዐሥራ ፡ ሦስት ፡ ምዕራፍ ።

፩ ፤ እግዚእ ፡ ሐረያ ፡ ግን ፡ ወትሮ ፡ ከምትቆ
ምበት ፡ ቦታ ፡ ቁማ ፡ ስትጸልይ ።
፪ ፤ ይኸንን ፡ ሁሉ ፡ ስላደረገላት ፡ እግዚአብ
ሔርን ፡ ስታመሰግን ።
፫ ፤ እያጠነ ፡ ሊዞር ፡ ከቤተ ፡ መቅደስ ፡ ወጣ ።
፬ ፤ አንድ ፡ ሴት ፡ ልብሰ ፡ መንግሥት ፡ ለብሳ ፡
ስትጸልይ ፡ አይቶ ፡ ደነገፀ ።
፭ ፤ ወንድ ፡ ባርያ ፡ ሴት ፡ ደንገጡር ፡ የሌላት ፡
እንዲህ ፡ ያለች ፡ ሴት ፡ ከየት ፡ መጣች ፡
እያለ ፡ አሰበ ።
፮ ፤ እንዲህ ፡ እያደነቀ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡
እያጠነ ፡ ዞሮ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ገባ ።
፯ ፤ ጸሎተ ፡ ዕጣኑን ፡ ሲጨርስ ፡ ወደሷ ፡ ወጥቶ
እንደተከናነበች ፡ ባረካት ።
፰ ፤ ፊቷን ፡ አላሳየችውም ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን
ወጥተው ፡ ባንድነት ፡ ተቀመጡ ።
፱ ፤ እመቤቴ ፡ ደህና ፡ መጣሽን ፡ አላት ።
፲ ፤ ደህና ፡ ነኝ ፡ አለችው ።
፲፩ ፤ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ክብር ፡ አይሻለሁ ፡ ከወ
ዴት ፡ መጣሽ ።
፲፪ ፤ ከቤተ ፡ መንግሥት ፡ ወገን ፡ የምትመስዪ፡
ወንድ ፡ አሽከር ፡ ሴት ፡ አሽከር ፡ ሳታስከ
ትዪ ፡ ብቻሽን ፡ ለምን ፡ ትሄጃለሽ ።
፲፫ ፤ እውነት ፡ ነው ፡ ከመንግሥት ፡ ወገን ፡ ነኝ ።
፲፬ ፤ አሽከሮቼን ፡ አስከትዬ ፡ ያለኝንም ፡ ሁሉ
ይዤ ፡ ስሸሽ ፡ ሞተለሚ ፡ አገኘኝ ፡ ሁሉንም፡
ወሰደብኝ ።
፲፭ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ እኔን ፡ ከሱ ፡ እጅ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ አዳነኝ ።
፲፮ ፤ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ የሚባል ፡ አንድ ፡ ሰው ፡
ሚስቱ ፡ ተማረከች ፡ ሲሉ ፡ ሰምቼ ፡ ስለሷ
ሚስት ፡ ልሁነው ፡ ብየ ፡ መጥቻለሁ ፡
አለችው ።
፲፯ ፤ ይኸንን ፡ ለምን ፡ አሰብሽ ፡ አላት ።
፲፰ ፤ ለካህን ፡ ሕጉን ፡ ክህነቱን ፡ ማፍረስ ፡ አይ
ገባውምና ።
፲፱ ፤ ዳግመኛም ፡ አንቺ ፡ የከበርሽ ፡ ሴት ፡ ነሽ ።
፳ ፤ እሱ ፡ ምንም ፡ የሌለው ፡ ደኃ ፡ ነው ፡ እሱ
ንም ፡ ብታገቢ ፡ ላንቺ ፡ ተዋርዶ ፡ ነው ።
፳፩ ፤ እሱም ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ሲል ፡ ሰም
ቼዋለሁ ።

፳፪ ፤ ለእመ ፡ ኢያግብአ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብእሲ
ትየ ፡ ኢያውስብ ፡ ካልዕተ ፡ ብእሲተ ፡ መሐ
ልኩ ፡ አንሰ ፡ በስሙ ፡ ቅዱስ ።

፳፫ ፤ ወትቤሎ ፡ እምዔዋዌኑ ፡ ያገብእ ፡ ሎቱ ።

፳፬ ፤ ወይቤላ ፡ ኀድጊሰ ፡ እምዔዋዌ ፡ እምድ
ኅረ ፡ ሞተትኒ ፡ እምክህለ ፡ አንስአታ ፡
እግዚአብሔር ።

፳፭ ፤ ወካዕበ ፡ ይቤ ።
፳፮ ፤ ቃልኪሰ ፡ ይመስል ፡ ቃለ ፡ ዚአሃ ።

፳፯ ፤ ወአክሞሰሰት ፡ ወትቤሎ ፡ አኮ ፡ በቃል፡
ባሕቲቱ ፡ ዘይትማሰል ፡ ሰብእ ፡ ዓዲ ፡
በመልክእኒ ፡ ይትማሰል ።
፳፰ ፤ ወካዕበ ፡ ትቤሎ ፡ አንተኑ ፡ ብእሲሃ ፡ ለይ
እቲ ብእሲት ።
፳፱ ፤ ወይቤላ ፡ እወ ፡ አነ ፡ ውእቱ ፡ ወትቤሎ ፡
አንሰ ፡ ሰማዕኩ ፡ በእንቲአሃ ፡ ከመ ፡ አው
ሰባ ፡ ንጉሥ ፡ ወረሰያ ፡ ንግሥተ ።

፴ ፤ ኢትትኃዘብኪ ፡ ከመ ፡ ትግባእ ፡ ለከ ፡
እምዝ ፡ ዳግመ ።
፴፩ ፤ ወባሕቱ ፡ ሐሊ ፡ ዘትገብር ።
፴፪ ፤ ወእምድኅረዝ ፡ ተምዓ ፡ ላዕሌሃ ።
፴፫ ፤ ወይቤላ ፡ ብእሲት ፡ እኪተ ፡ መዋዕል ፡
አንቲ ፡ ለምንተ ፡ ኢተኀፍሪ ፡ እንዘ ፡ ትት
ናገሪ ፡ ዘከመዝ ፡ ነገረ ።
፴፬ ፤ እግዚአብሔር ፡ ያሰስል ፡ ለኪ ፡ ዘንተ ፤
ዝሙተኪ ።
፴፭ ፤ እስመ ፡ ነፍሱ ፡ ለዘማዊ ፡ ርኩስ ፡ ውእቱ
ከመ ፡ ደመ ፡ ከልብ ፡ ወጽዩዕ ፡ ውእቱ
ከመ ኩስሕ ።

፴፮ ፤ እግዚአብሔርሰ ፡ ወመላእክቲሁ ፡ ያፈቅሩ
ንጽሐ ።
፴፯ ፤ ወሶበ ፡ ርእየት ፡ ጽንዓ ፡ ሃይማኖቱ ፡ ከመ፡
ጥቀ ፡ መንክር ፡ ወተንሥአት ፡ ፍጡነ ፡
ወቆመት ፡ ቅድሜሁ ፡ ወከሠተት ፡ ግል
ባቤ ፡ ገጻ ።
፴፰ ፤ ወትቤሎ ፡ እግዚእየ ፡ ነጽረኒ ፡ ጥዩቀ ፡
አነ ይእቲ ፡ ብእሲትከ ፡ እግዚእ ፡ ሐረያ ።
፴፱ ፤ ወደንገፀ ፡ ወተንሥአ ፡ ወሐቀፋ ፡ ክሣዳ ፡
ወሰዓማ ፡ ርእሳ ።
፵ ፤ ወወድቀ ፡ ውስተ ፡ ምድር ፡ ወሰዓመ፡ አእ
ጋሪሃ ፡ ወአብራኪሃ ።

፵፩ ፤ ወይቤላ ፡ አ ፡ እኅትየ ፡ እፎ፡እንጋ፡ ኮንኪ ፡
ወበምንትኑ ፡ ግብር ፡ በጻሕኪ ፡ ዝየ ።
፵፪ ፤ ወትቤሎ ፡ በጥበበ ፡ እግዚአብሔር፡ በጻ
ሕኩ ።
፵፫ ፤ እምአመ ፡ ተፈለጥኩ ፡ እምኔከ ፡ ኢረከበኒ፡
እኩይ ፡ ለግሙራ ፡ በእንበለ ፡ ሠናይ ።

፳፪ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሚስቴን ፡ ካልመለሰልኝ፡
ሌላ ፡ ሴት ፡ አላገባም ፡ ብሎ ፡ ስመ እግ
ዚአብሔር ፡ ጠርቶ ፡ ሲምል ፡ ሰምቼዋ
ለሁ ፡ አላት ፡
፳፫ ፤ ከተማረከች ፡ በኋላ ፡ ይመልስለታልን ፡
አለችው ።
፳፬ ፤ ስንኳን ፡ ከተማረከችበት ፡ ይቅርና ፡
ከሞተችም ፡ በኋላ ፡ አሥነሥቶ፡ መስጠት፡
ለእግዚአብሔር ፡ በተቻለው፡
ነበር ፡ አላት ።
፳፭ ፤ ዳግመኛም ፡ እንዲህ ፡ አላት ።
፳፮ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ ቃልሽ ፡ የሷን ፡ ቃል ፡ ይመስ
ላል ፡ አለ ።
፳፯ ፤ ፈገግ ፡ ፈገግ ፡ ብላ ፡ ሰው ፡ የሚመስለው፡
በቃል ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ በመልክም ፡
ይመስላል ፡ እንጂ ፡ አለችው ።
፳፰ ፤ ዳግመኛም ፡ ለዚያች ፡ ሴት ፡ ባሏ ፡ አንተ ፡
ነህን ፡ አለችው ።
፳፱ ፤ አዎን ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ አላት ። እኔ ፡ የሷን ፡
ነገር ፡ ንጉሥ ፡ አግብቶ ፡ አነገሣት ፡ ሲሉ ፡
ሰምቻለሁ ፡ አለችው ።

፴ ፤ ከእንግዲህ ፡ ወዲያ ፡ ትመለስልኛለች ፡
ብለህ ፡ አትጠራጠር ።
፴፩ ፤ የምታደርገውን ፡ አስብ ፡ እንጂ ፡ አለችው ።
፴፪ ፤ ከዚህ ፡በኋላ ፡ ተቆጣት ።
፴፫ ፤ አንቺ ፡ ወራት ፡ የባሰሽ ፡ እንዲህ ፡ ያለ፡
ነገር ፡ ስትናገሪ ፡ ለምን ፡፡ አታፍሪም ።

፴፬ ፤ እግዚአብሔር ፡ ይህን ፡ የዝሙት ፡ አነጋ
ገርሽን ፡ ያርቅልሽ ።
፴፭ ፤ የዘማዊ ፡ ሰውነት ፡ እንደውሻ ፡ ደም ፡
እርኩስ ፡ ነውና ፡ እንደ ፡ ኩስም የሚያ
ጸይፍ ፡ ነውና ።

፴፮ ፤ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ መላእክትም ፡ ንጽ
ሕናን ፡ ይወዳሉ ።
፴፯ ፤ ሃይማኖቱ ፡ እጅግ ፡ እንደጸና ፡ ባየችው፡
ጊዜ ፡ ፈጥና ፡ ተነሥታ ፡ ከፊቱ ፡ ቁማ ፡
ክንብንቧን ፡ ገልጻ ፡ ታየችው ።

፴፰ ፤ ጌታዬ ፡ ፈጽመህ ፡ ዕወቀኝ ፡ እኔ ፡ ሚስ
ትህ ፡እግዚእ ፡ ሐረያ ፡ ነኝ ፡ አለችው ።
፴፱ ፤ ደንግጦ ፡ ተነሥቶ ፡ አንገቷን ፡ ይዞ ፡
ራሷን ፡ ሳማት ።
፵ ፤ ከጫማዋ ፡ ወድቆ ፡ እግሯን ፡ ጉልበቷን ፡
ሳማት ።

፵፩ ፤ እኅቴ ፡ ሆይ ፡ እንደምን ፡ ሆነሽ ፡ ከዚህስ፡
እንደምን ፡ ደረስሽ ፡ አላት ።
፵፪ ፤ እግዚአብሔር ፡ በጥበቡ ፡ አደረሰኝ ፡
አለችው ።
፵፫ ፤ ካንተ ፡ ከተለየሁ ፡ ጀምሮ ፡ በጎ ፡ ነገር ፡
እንጂ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አላገኘኝም ።

፵፩ ፤ እስመ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈነወ ፡ መልአኮ፡ ወአድኃነኒ ።

**ዳንኤል ፡ ፮ ፡ ቍ ፡ ፳፪ ።**

፵፪ ፤ ወነገረቶ ፡ ኵሎ ፡ ዘገብረ ፡ ላቲ ፡ እምጥንቱ ፡ እስከ ፡ ተፍጻሜቱ ።
፵፫ ፤ ወሰሚዖ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ እምኔሃ ፡ አንሥአ፡ አዕይንቲሁ ፡ ላዕለ ፡ ውስተ ፡ ሰማይ ።
፵፬ ፤ ወይቤ ፡ ይትባረክ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላከ ፡ እስራኤል ፡ ዘገብረ ፡ መንክረ፡ባሕቲቱ።

**መዝ ፡ ፸፩ ፡ ቍ ፡ ፲፰ ።**

፵፰ ፤ ወይትባረክ ፡ ስመ ፡ ስብሐቲሁ ፡ ወይምላእ ስብሐቲሁ ፡ ኵሎ ፡ ምድረ ፡ ለይኩን ፡ ለይኩን ።
፵፱ ፤ ወጸውዖሙ ፡ ለሰብአ ፡ ሀገሩ ፡ ወይቤሎሙ፡ ንዑ ፡ ትርአዩ ፡ ግብሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘገብረ ፡ መንክረ ፡ በዲበ ፡ ምድር ።
፶ ፤ አርአየ ፡ ኃይሎ ፡ በላዕሌየ ፡ ወጸገወኒ ፡ ሠናይቶ ።
፶፩ ፤ ወበከመ ፡ በዝኃ ፡ አበሳየ ፡ በዝኃ ፡ ሣህሉ፡ ለአምላኪየ ።
፶፪ ፤ ወተጋብኡ ፡ ኵሎሙ ፡ ሰብአ ፡ ሀገር ፡ ንኡሶሙ ፡ ወዐቢዮሙ ።
፶፫ ፤ ርእይዋ ፡ ለእግዚእ ፡ ሐረያ ፡ እንዘ ፡ ስርጉት ፡ በአልባሰ ፡ ወርቅ ፡ ወተአምኅዋ ።
፶፬ ፤ ወይቤልዋ ፡ መኑ ፡ አምጽአኪ ፡ ዝየ ፡ በዘመጠንዝ ፡ ዕበይ ።
፶፭ ፡ ወነገረቶሙ ፡ ኵሎ ፡ ዘኮነ ፡ ላዕሌሃ ።
፶፮ ፤ ወአዕኰትዎ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ዘይገብር መንክረ ፡ በላዕለ ፡ ቅዱሳኒሁ ።

**መዝሙር ፡ ፳፯ ፡ ቍ ፡ ፵፭ ።**

፶፯ ፤ ወቦ ፡ እለ ፡ በከዩ ፡ በእንተ ፡ እለ ፡ ተርፉ ፡ ዔውዋን ።
፶፰ ፤ ወወአሉ ፡ ይእተ ፡ ዕለተ ፡ እንዘ ፡ ይትናገሩ ፡ ዕበያተ ፡ እግዚአብሔር ።
፶፱ ፤ ወተመጢዎሙ ፡ ቍርባነ ፡ አተው ፡ ውስተ ማኅደሪሆሙ ፡ በፍሥሐ ፡ ወበሐሤት ።
፷ ፤ ወአቅረቡ ፡ ማዕደ ፡ ወእንዘ ፡ ይበልዑ ፡ ትቤሎ ፡ እግዚእ ፡ ሐረያ ፡ ለጸጋ፡ዘአብ ፡ አንሰ ፡ እምአመ ፡ ተፈለጥኩ ፡ ኅምኔከ ፡ ኢበላዕኩ ፡ እክለ ፡ ወኢሰተይኩ ፡ ማየ ።
፷፩ ፤ ጥበቡ ፡ ለአምላኪየ ፡ አብጽሐኒ ፡ እስከ ፡ ዮም ።
፷፪ ፤ ወሰሚዖ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብ ፡ አንከረ ፡ ወተደመ።
፷፫ ፤ ወነገራ ፡ ውእቱ ፡ ኵሎ ፡ ዘበጽሐ ፡ ላዕሌሁ፡ እምጥንቱ ፡ እስከ ፡ ተፍጻሜቱ ።
፷፬ ፤ ወፈጺሞሙ ፡ ማዕዶሙ ፡ ኃደሩ ፡ ኵላ ፡ ሌሊተ ፡ እንዘ ፡ ይዜውዑ ፡ በነገራተ ፡ አምላክ ፡ ወበነገረ ፡ መላእክት ።
፷፭ ፤ ነፍጸ ፡ ንዋም ፡ እምአዕይንቲሆሙ ፡ በእንተ ፍሥሐሆሙ ።

፵፩ ፤ እግዚአብሔር ፡ መልአኩን ፡ ወደኔ ፡ ልኮ አድኖኛልና ።

**ዳንኤል ፡ ፮ ፡ ቍ ፡ ፳፪ ።**

፵፪ ፤ ያደረገላትን ፡ ሁሉ ፡ ከመጀመሪያው ፡ እስከ መጨረሻው ፡ ድረስ ፡ ነገረችው ።
፵፫ ፤ ጸጋ ፡ ዘአብም ፡ ይኸንን ፡ ሰምቶ ፡ ወደሰማይ ተመለከተ ።
፵፬ ፤ ብቻውን ፡ ይህን ፡ ታላቅ ፡ ተአምር ፡ ያደረገልኝ ፡ የእስራኤል ፡ ፈጣሪ ፡ ይክበር ፡ ይመስገን ።

**መዝ ፡ ፸፩ ፡ ቍ ፡ ፲፰ ።**

፵፰ ፤ የጌትነቱም ፡ ስም ፡ ይክበር ፡ ምስጋናውም ፡ ለዓለሙ ፡ ሁሉ ፡ ምሉእ ፡ ይሁን ።
፵፱ ፤ ያገሩን ፡ ሰዎች፡ ጠርቶ ፡ እግዚአብሔር ፡ በምድር፡ ያደረገልኝን፡ ተአምራት፡ ታዩ፡ ዘንድ ፡ ኑ ፡ አላቸው ።
፶ ፤ ኃይሉን ፡ በኔ ፡ ላይ ፡ ገለጸ ፡ ቸርነቱን ፡ አደረገልኝ ።
፶፩ ፤ እንደ ፡ ኃጢአቴ ፡ ብዛት ፡ መጠን ፡ ይቅርታው ፡ በዝቶ ፡ ተደረገልኝ ።
፶፪ ፤ ሳይማረኩ ፡ የቀሩ ፡ የሀገሩ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ትንሹም ፡ ትልቁም ፡ ተሰብስበው ።
፶፫ ፤ እግዚእ ፡ ሐረያን ፡ በወርቅ ፡ ልብስ ፡ ተሸልማ ፡ አይዋት ።
፶፬ ፤ ተገናኝዋት ፡ እጅ ፡ ነሷት ፡ በይህናህል ፡ ክብር ፡ ገናንነት ፡ ማን ፡ አመጣሽ ፡ አሏት።
፶፭ ፤ በሷ ፡ የተደረገውን ፡ ሁሉ ፡ ነገረቻቸው ።
፶፮ ፤ በወዳጆቹ ፡ አድሮ ፡ ተአምራት ፡ የሚያደርግ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገኑ ።

**መዝ ፡ ፳፯ ፡ ቍ ፡ ፵፭ ።**

፶፯ ፤ ተማርከው ፡ ስለቀሩትም ፡ ያለቀሱ ፡ አሉ ።
፶፰ ፤ የእግዚአብሔርን ፡ ሥራ ፡ ሲነጋገሩ ፡ ዋሉ።
፶፱ ፤ ሥጋ ፡ ወደሙ ፡ ተቀብለው ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ ወደቤታቸው ፡ ገቡ ።
፷ ፤ ማዕድ ፡ አቀረቡ ፡ እግዚእ ፡ ሐረያ ፡ ጸጋ ፡ ዘአብን ፡ እኔ ፡ ካንተ ፡ ከተለየሁ ፡ ጀምሬ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ እህል ፡ ውኃ ፡ አልቀመስኩም ።
፷፩ ፤ ፈጣሪዬ ፡ በጥበቡ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ አደረሰኝ ፡ አለችው ።
፷፪ ፤ ጸጋ ፡ ዘአብም ፡ ነገሯን ፡ ሰምቶ ፡ አደነቀ ።
፷፫ ፤ እሱም ፡ ያገኘውን ፡ መከራ ፡ ሁሉ ፡ ከመጀመሪያው ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ነገራት ።
፷፬ ፤ ከተመገቡም፡ በኋላ ፡ ፈጣሪያቸው ፡ ያደረገላቸውን ፡ ነገር ፡ መልአኩም ፡ የሠራላቸውን ፡ ሥራ ፡ ሲጨዋቱ ፡ አደሩ ።
፷፭ ፤ ስለደስታቸው ፡ ብዛት ፡ ዕንቅልፍ ፡ ከዓይናቸው ፡ ሸሸ ፡ (አላዩም) ።